# በፍርድ ቤቶች የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት

**በአስማማው አዳነ (ዶ/ር)**

**ሄኖክ ጌታቸው (ዶ/ር)**

**ገበየሁ ገዝሙ**

**ግንቦት፤2014**

**አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ**

| | ማውጫ | |
|---|---|---|
| ተ.ቁ | ርዕስ | ገፅ |
| | የጥናቱ አጭር ማጠቃለያ | |
| | ክፍል አንድ | 2 |
| 1 | መግቢያ | 2 |
| 1.1 | የጥናቱ ዳራ/Background of the Study/ | 3 |
| 1.2 | የጥናት ችግር ማብራሪያ /Statement of the Problem/ | 4 |
| 1.3 | የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study) | 5 |
| 1.4 | የጥናቱ አስፈላጊነት (Significance of the Study) | 5 |
| 1.5 | የጥናቱ ወሰን (Scope of the Study) | 6 |
| 1.6 | ከጥናቱ የሚጠበቅ ውጤት (Outcomes of the Study) | 7 |
| 1.7 | የጥናቱ ውስንነት /መሰናክሎች እና ተግዳሮቶች/(Limitations of the study) | 7 |
| 1.8 | የቃላት ፍች /Operational Definition | 8 |
| | ክፍል ሁለት | 10 |
| 2 | የጥናቱ ስልት (Methodology of the Study) | 10 |
| 2.1 | የጥናቱ ቦታዎች | 10 |
| 2.2 | የጥናቱ ተሳታፊዎችና የተሳታፊ አመራረጥ | 10 |
| 2.3 | የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Methods of Data Collection) እና ምንጮች (Data Sources) | 11 |
| 2.4 | የመረጃ አተናተን ዘዴ /Methods of Data Analysis/ | 13 |
| 2.5 | ስነምግባር | 14 |
| | ክፍል ሦስት | 15 |
| | የሙስና ስጋት ትንተና | 16 |
| 3.1 | መግቢያ | 16 |
| 3.2 | በፍርድ ቤት ላይ የሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶች | 16 |
| 3.3 | የሙስና ስጋት ምክንያቶች | 20 |
| 3.4 | ፍርድ ቤቶች ከሙስና ተጋላጭነት አንጻር | 22 |
| 3.4.1 | ሙስና ለመከላከል የሚረዱ አሰራሮችና መመሪያዎች | 22 |
| 3.4.2 | የመረጃ ግልጽነት ደረጃ ስጋት | 26 |
| 3.4.3 | የተቋሙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አቅምና ብቃት ስለማሳደግና ማጎልበት | 29 |

| | | |
|---|---|---|
| 3.4.4 | የተቋሙ የሙስና ተጋላጭነት ሥጋት የመቀነስና የግልጽነት ዕድገት ደረጃ፤ | 30 |
| 3.4.5 | በተቋሙ የሙስና እና ብልሹ ተግባራትን መረጃ የማመንጨት አቅመና ብቃት | 33 |
| 3.4.6 | በዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ዉስጥ የሚሰተዋሉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት | 37 |
| 3.4.7 | በፍርድ አፈጻጸም አገልግሎት ዉስጥ የሚሰተዋሉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት | 41 |
| 3.4.8 | በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት | 43 |
| 3.4.9 | በሬጂስትረር ዳይሬክቶሬት ስጋት ተጋላጭነት | 45 |
| | ክፍል አራት | 47 |
| | የሙስና ስጋት ምዘናና ግምገማ | |
| 4.1 | በፍርድ ቤቱ ሰራተኞች የሚፈጸሙ የሙስና ወንጀሎች/ስጋቶች በደረጃ | |
| 4.2 | ችግሮቹ ሊያመጡ የሚችሉት ተጽእኖ | |
| | ክፍል አምስት | |
| | ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳብ | |
| 5.1 | ማጠቃለያ | |
| 5.2 | የመፍትሄ ሃሳብ | |
| | አባሪዎች | |
| | አባሪ አንድ፡ የድርጊት መርሀ ግብር | |
| | አባሪ ሁለት፡ የጥናት መረጃ ለሚሰበሰቡ ቡድኖች የሚያስፈልግ ግምታዉ ወጪዎች | |
| | አባሪ ሶስት፡ የሙስና ስጋት ጥናት የሚካሄድባቸዉ የፌደራል ፍርድ ቤቶች እና በክልሎች ያሉ ፍርድ ቤቶች ዝርዝር እና መረጃ የሚሰበስቡ ቡድኖች | |
| | አባሪ አራት፡ የፍርድ ቤት አጠቃላይ መረጃ | |
| | አባሪ አምስት፡ የጽሁፍ መጠይቅ | 22 |
| | አባሪ ስድስት፡ ቃለ መጠይቅ | 31 |
| | ማጣቀሻ ጽሁፎች | 36 |

**ክፍል አንድ**

# 1. መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

አሁን ባለንበት ነባራዊ ሁኔታ ሙስና ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ባለፈ የደህንነትና የፖለቲካ እንድምታ የሚያመጣ መሆኑ መግባባት ላይ ተደርሷል። እየወጡ ያሉ ሪፖርቶች እንደሚያመላክቱት ሙስና ሃገራት ለእድገት የሚያደርጉትን ጉዞ በማሽመድመድ ዜጎች ለእንግልት ለሰላም ማጣትና ለስደት እንዲዳረጉ መንስኤ ይሆናል(World Bank, 2014)። በተጨማሪም ምንም እንኳን ዜጎች የሃገራቸው የኢኮኖሚ እድገት ያመጣውን ትሩፋት የመጋራትና በመንግስት ገንዘብ ድጋፍ የሚሰጡ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን የማግኘት መብት እንዳላቸው በተለያዩ ሃገራት የሚደነገጉ ህጎችና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው የሰብአዊ መብት ድንጋጌ ስምምነቶች ቢጠቀስም፤ ሙስና ለነዚህ መብቶች ተግባራዊነት እንቅፋት በመፍጠር ላይ ይገኛል።

ጥናቶች እንደሚያሳዩት በአገር አቀፍ እና በተለያዩ እርከኖች የሚገኙ መንግስታዊና የልማት ተቋማት ለሙስና ተጋላጭነታቸው እየጨመረ ይገኛል (Transparency International, 2021)። ይሄም የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት አካታች፤ ሁሉን አሳታፊና ብቃት ያላቸውን ተቋማት እንዳይገነቡ እንቅፋት ይፈጥራል።በዚህም የተነሳ ዘርፈ-ብዙ መዘዞችን በማስከተል ላይ ይገኛል። ከዚህም ጋር ተያይዞም ችግሩ አገራት መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣጥ ለሚያደርጉት ጥረት አሉታዊ ጫና ያሳድራል። ሙስና በሃገር ላይ ሁለንተናዊ እድገት አሉታዊ ተፅእኖ በማስከተል ሃገር እንደሃገር በማይቀጥልበት ደረጃ ለማድረስ የሚያስችል ወይም የማፍረስ አደጋ የሚያስከትል ተለዋዋጭነት ባህሪ ያለው አደገኛ የሆነ የወንጀል አይነት ነው። ሙስና የሚያስከትለውን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት የአፍሪካ ሕብረት እ.ኤ.አ በ2003 ባደረገው ሁለተኛው የመሪዎች ጉባኤ ሙስናን የመከላከልና የመዋግያ ስምምነት አጽድቋል (African Union, 2003)። በተመሳሳይ አመት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ የጸረ-ሙስና ስምምነት አጽድቋል (United Nations, 2003)። በተጨማሪም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እ.ኤ.አ በ2015 ባደረገው ጠቅላላ ጉባኤ 2030 አጀንዳ ለዘላቂ ልማት የሚል አጽድቋል።[1] ጉባኤውም ሙስናን አለም አቀፍ ችግር በመሆኑ ዋነኛ የዘላቂ ልማት ስጋት ብሎ ወስዶታል (United Nations Office on Drugs and Crime, 2004)።

[1] የዘላቂ ልማት ትኩረት ከሚሰጣቸውዋነኞቹ ግቦች፡ ድህነትንና ርሃብን ማስወገድ፤ የተሟላ የጤና አጠባበቅ፤ የጾታ እኩልነት፤ ንጹህ ውሃና መጸዳጃ አቅርቦትና፤ የአካባቢን ጥበቃ ማእከል ያደረገ የሃይል ምንጭ፤ የስራ እድልና የኢኮኖሚ እድገት፤ ልዩነቶችን መቀነስ፤ ዘላቂ ከተሞችና ማህበረሰቦች፤ ሰላም፤ ፍትህና ጠንካራ ተቋማትና ተያያዥ ሁኔታዎች ላይ የሚያጠነጥነ ው፡

ችግሩን በመረዳት ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ ሃገራት ይህን ተለዋዋጭነት ያለውን የወንጀል ዓይነት ሊመጥን የሚችል የመከላከያ ስልት በመንደፍ ለመከላከል ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ኢትዮጵያም በ1993 ዓ/ም ይህን የሀገር ዕድገት የሚያቀጭጨውንና ዘርፈ ብዙ ችግር የሚያስከትለው የሙስና ወንጀል ለመከላከልና ለመዋጋት የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽንን በአዋጅ ቁጥር 235/1993 በማቋቋም ሥነምግባር ለማስተማር፤ ሙስናን ለመከላከልና

ሙስና ወንጀል በመመርመና በመክሰስ የተመዘበረ ሀብት ለማስመለስ የሚያስችል ስልጣን በመስጠት አቋቁማለች። የፌደራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን እንደገና በተሻሻለው የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት በመንግስት መ/ቤቶች ፤ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እንዲሁም በህዝባዊ ድርጅቶች ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ላይ የተመሠረተ ሃላፊነቶች ተሰጥቶታል። ለባለፉት ሁለት አስርት አመታት ኮሚሽኑ በተለይ ለሙስናና ብልሹ አሰራር የመጋለጥ ዕድላቸው ከፍተኛ ናቸው በሚባሉና ጉልህ ጉዳዮች ላይ ይበልጥ በማተኮር በሥነምግባር ግንዛቤ የማስጨበጥ፤ የሙስና ተጋላጭነት ሥጋት መከላከል ጥናቶችን የማጥናትና የመንግስት ኃላፊዎችና ሠራተኞችን ሃብት የመመዝገብ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል። ከዚህ ጋር ተያይዞም በባለፉት ሶስት አመታት የተለያዩ የፖሊሲ መሻሻያዎች በመንግስት እየተወሰዱ ይገኛሉ።[2]

ኮሚሽኑ በአሁኑ ጊዜ የተቋቋመለትን ግብ ለማሳካት ለሃገር ዕድገት ጠቀሜታ ባላቸውና ለሙስና ችግር በይበልጥ ተጋላጭ በሆኑ ኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊ፤ አስተዳደርና ፍትህ ዘርፎች ላይ የሙስና ሥጋቶችን ከመከላከል አንፃር ሃገር አቀፍ ጥናት እያከናወነ ይገኛል። በተለይም በአስተዳደርና በፍትህ ዘርፍ ሥር የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ለሙስናና ብልሹ አሰራር ያላቸውን የሙስና ሥጋት እና የሥጋት ደረጃ በጥናት ላይ ተመስርቶ ለመለየትና በቀጣይ በቅደምተከተል ሙስናን መከላከል የሚያስችሉ ሥራዎችን በማከናወን የሚታዩ ችግሮች እንዲቀረፉ ለማድረግ የሚያስችሉ የመፍትሄ ሃሳቦች ለማመንጨትና እንዲተገበሩ በማድረግ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ይሄም ፍርድ ቤቶችና ዳኝነት አስተዳደር ለሙስና ስጋት ተጋላጭ መሆን አገሪቷ የልማት ግብ ለማሳካት በምታደርገው ጥረት ዋና ጋሬጣ መሆኑ ይስተዋላል። ስለዚህም ይህ ጥናት የሚያተኩረው በፍርድ ቤቶች የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ላይ ነው።

## 1.2 የጥናቱ ችግር ማብራሪያ

በአለም አቀፍ ደረጃ የማህበረ-ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን ከሚያስከትሉት አንዱ ሙስና ነው። ችግሩ እንደየሁኔታው ተለዋዋጭ ባህሪ ስለሚያሳይ ችግሩን ለመቅረፍ የሚደረግ ጥረት አዳጋች ያደርገዋል። የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ የተለያዩ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ከጊዜ ወደ ጊዜ ለሙስና ስጋት ተጋላጭነታቸው እየጨመረ እየሄደ ይገኛል። ሌሎች ጥናቶች እንደሚያሳዩትም የሙስና ችግር ገፊ-ምክንያት፤

[2] ከፖሊሲ ማሻሻያዎች መካከል አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አንዱ ተጠቃሽ ነው፡፡ ይሄም ማሻሻያ ኢትዮጵያ አሁን ካለችበት እርሻ መር ዝቅተኛ ገቢ ሃገር ወደ ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ሃገር በ2030 ለማስገባት ያልማል፡፡ ይሄም የፖሊሲ ማሻሻያ የተሳካ እንዲሆን ሙስናን ለመቅረፍ፤ ለመግታትና ለመከላከል የሚረዱ የህግ ማዕቀፎችና የሙስና ስጋት ዳሰሳዎች ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል፡፡

መጠንና ግዝፈት እንደየሃገራቱ ነባራዊ ሁኔታ ስለሚለያይ ችግሩን ለማከም የሚከተሉት ስትራቴጂ የተለያየ ነው። በተጨማሪም ጥናቶቹ የተለያየ ዘዴዎችን በመጠቀም በተለይ እንደ አመቺነቱ ሴክተሮችን፤ ተቋማትንና በውስጡ ያሉትን የስራ ሂደቶችን ትኩረት ያደርጋሉ። በኢትዮጵያ እስከአሁን አዲስ ጅማሮ ያለ ቢሆንም በአገር ውስጥና በውጭ ባሉ ተቋማት በተለይ በጸረ-ሙስና ኮሚሽን (Gedion, 2019)፤ በእንባ ጠባቂ (Ethiopian Ombudsman Authority, 2021)እና በዓለም አቀፍ ተቋማት የተወሰነ በሙስና ላይ የዳሰሳ ጥናቶች ተካሂዷል (Institute of African Economic Studies, 2008; Transparency International, 2007; World Bank, 2012)። በአጠቃላይ እስከ አሁን ድረስ እየተደረጉ ያሉት ጥናቶች ምንም እንኳን በሌሎች ተቋማት ላይ ያለውን የሙስና ምክንያትና ተጽእኖ ቢያሳዩም፤ የሙስና ስጋት ዘዴን በመከተል በአገር ውስጥ ያሉ ተቋማትን በተለይ የፍርድ ቤቶች በፌደራል እና በክልል ደረጃ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ላይ ያተኮሩ ዳሰሳዎች አይስተዋሉም። ከችግሩ ግዝፈት በተለይም ፍርድ ቤቶች ለሙስና ስጋት ተጋላጭነት ከፍተኛ መሆኑ ከግምት ውስጥ በማስገባት፤ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ ጥናት ይጋብዛል። ስለሆነም የትኞቹ የፍርድ ቤቶች አሰራርና የስራ ክፍሎች ናቸው የሙስና ስጋት ተጋላጭነት የሚስተዋልበትና ደረጃዎቹስ ምን ይመስላል? የሚለውን መመርመር የጥናቱ ዋና ጉዳይ ነው።

### 1.3 የጥናቱ ዓላማ (Objective of the Study)

#### 1.3.1 አጠቃላይ ዓላማ (General Objective of the Study)

የጥናቱ አጠቃላይ አላማ በፍ/ቤቶች የሚታዩ የሙስና ስጋቶችን ማጥናት ነው።

#### 1.3.2 ዝርዝር ዓላማዎች (Specific Objectives of the study)

- በፍርድ ቤቶች የሚስተዋሉ የሙስና ስጋት በዝርዝር መለየት፤
- በፍርድ ቤቶች የሙስና አደጋ ምክንያቶችን መለየትና መተንተን፤
- በፍርድ ቤቶች የሙስና ስጋት መገምገምና ደረጃ መስጠት ፤
- በፍርድ ቤቶች በተሰጠዉ የደረጃ ቅደም ተከተል መሠረት የሙስና መከላከል ምክረሀሳቦችን ማቅረብ።

### 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

ሙስና በሀገሪቱ ላይ እያስከተለ ያለዉ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ኪሳራዎች እጅግ ከፍተኛ ነዉ። በመሆኑም በፌዴራል ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የታሰበዉ የሙስና ሥጋት ጥናት ማድረግ በአይነቱ የመጀመሪያ ሲሆን፤የሚከተሉት ፋይዳዎች ይኖሩታል። የጥናቱ ግኝት ኮሚሽኑ በፍርድ ቤቶች ያለውን የሙስና አይነት፣ የስጋት ሁኔታ፤ የአሰራር እና የመዋቅር ተጋላጭነትና የተጋላጭነት ደረጃ የሚስተዋልባቸውን የስራ ክፍሎች እንዲለይ፤ ያለው ተጽእኖ መረዳት እንዲኖር፤መረጃ እንዲያደራጅና እንዲተነተን ይረዳዋል።ከዚህም ጋር ተያይዞ

ትኩረት የተሰጣቸው ተቋማት የሙስና ሥጋት ተጋላጭነት በዝርዝር በመለየት የተጋላጭነት ስጋት ደረጃ በመስጠት የተቋማት ተጋላጭነት ፕሮፋይል እንዲዘጋጅ አጋዥ ይሆናል፡፡

ሌላኛው የጥናቱ ፋይዳ ጥናቱ ከሚደረግባቸው ፍርድ ቤቶች አንጻር ማየት ይቻላል፡፡ የሙስና ስጋት የሚስተዋልባቸው አሰራሮችና ህጎች ለመከላከልና ለመቅረፍ ምን አይነት የመከላከያ እቅድ፤ እስትራቴጂ፤የሕግ ማዕቀፎች ፤ ፖሊሲ ፣ ደንብና መመሪያ ይወሰድ የሚለውን እንዲለዩ እና እንዲያዘጋጁ ይረዳቸዋል፡፡ የሙስና ተጋላጭነት ዳሰሳ ጥናት ውጤት በፍርድ ቤቶች የሚታዩ የአራር ክፍተቶችን ከማሳየት ባሻገር የትኞቹ ተቋማትና አሰራሮች በብቃትና በታማኝነት እንደሚሰሩና እንዴት ይህ አስቻይ ሁኔታ እንደተፈጠረ እንድናውቅ ይረዳናል፡፡ ከሌላው ተመሳሳይ ተቋም ጋር ሲነጻጸሩ የተሻለ አሰራርና መዋቅር ያሳዩ ለሌሎች በነሱ ደረጃ ላልደረሱ ምሳሌ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ እርከን ላይ ያሉ የመንግስት አካላት በፍርድ ቤቶች ለሙስና ስጋት ተጋላጭነትን በማስወገድ ተቋማቸው ብቃት ያለው አካታችና ተወደዳሪ የሆነ እንዲሆን ይረዳል፡፡ የሙስና ወንጀልን ለመከላከል ፈቃደኛ ባልሆነ ተቋም ፤ አመራሮችና ሠራተኞች ላይ መንግስት የፖለቲካ፤የህግ እና አስተዳደራዊ ዉሳኔ ለመስጠትም ይረዳል፡፡ በተጨማሪም የጥናቱ አስፈላጊነት ለሌሎች ጥናቶች እንደ መነሻ በመሆን በፍርድ ቤቶች ውስጥ ወደፊት ሊስተዋሉ የሚችሉ የሙስና ስጋቶችን ልየታ ያደርጋል፤ በቀጣይ ጊዜ የስነምግባር ግንባታ ሥራና ስልጠናዎችን በተለያየ ደረጃ ለህብረተሰቡ ለመስጠት የተለያዩ የመንግስትና የግል መገናኛ ብዙሃን የጥናቱን ውጤት በመረጃነት በመጠቀም የሙስና ወንጀልን ለመከላከል ይረዳል፡፡ ሌላኛው የጥናቱ አስፈላጊነት የዘላቂ ልማት ግብን ለማሳካት ኢትዮጵያ ከገባችው ዓለምአቀፍ ግዴታ አንጻር ሲታይ ትልቅ አገራዊ ፋይዳ ይኖረዋል ፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን (Scope of the Study)

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በፍርድ ቤቶች የሚስተዋለውን የሙስና ሥጋት ነው፡፡ ምንም እንኳን ሙስናን በተለያየ መልክ ትርጓሜ ቢሰጠውም፤ ለዚህ ጥናት ሙስና ማለት ቀደም ሲል በፍትህ ስርአት ውስጥ የተከሰተ ወይም እየተከሰተ ያለ የሙስና ወንጀል ነው፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ በይበልጥ እንዲረዳ የሙስና ስጋት ዳሰሳ በማድረግ በፍርድ ቤቶች ውስጥ ያሉ የሙስና ስጋቶችን መለየት፤ የስጋት ትንታኔ፤ ግምገማና ምክረ-ሃሳብ በመስጠት እነዚያን የሙስና ስጋቶችን ለመቅረፍ ውሏል፡፡

ጥናቱ ያካለለው 1 የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣1 የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት (ልደታ ምድብ )፣ 1 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት (ልደታ ምድብ ) እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ነው፡፡ በክልል ደረጃ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት 1 የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት (አዲሰ አባባ) ፤3 ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ማለትም ምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት (አዳማ)፤ ምእራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት (ሻሸመኔ) እና ጅማ

ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት (ጅማ) ሲሆን የምስራቀ ሸዋ ዞን ሞጆ ወረዳ ፍርድ ቤት ፤የምዕራብ አርሲ ዞን ሻሸመኔ ወረዳ ፍርድ ቤት፤ የጅማ ዞን ሰቃ ጨቆርሳ ወረዳ ፍርድ ቤትን ጨምሯል ፡፡

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሰት ደግሞ 1 የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት (ሃዋሳ) ሲሆን በስሩ ያሉ ሶስት ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች ማለትም ጉራጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት (ወልቂጤ) ፤ ጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት (አርባ ምንጭ) እና ወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት (ሶዶ) እና በስራቸዉ ያሉ አበሽጊ ወረዳ ፍርድ ቤት፤ ካምባ ወረዳ ፍርድ ቤት ወላይታ ሶዶ ዙሪያ ወረዳ ፍርድ ቤትን አካቷል፡፡

እነዚህ ላይ ብቻ ለማተኮር ገፊ ምክንያት የሆነው የጊዜ እና የሀብት ውስንነት ነው፡፡ ጥናቱ ያጠነጠነው የሙስና ስጋት ሁኔታዎች ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቶቹ የተቋቋሙለትን አላማ ለማስፈጸም በሚያከናውኑት አሰራርና ስርዓትና ሂደት ምን ያህል የሙስና ስጋት ተጋላጭነት እንዳላቸውና ተጽእኖው ምን እንደሆነ ትኩረት ሰቷል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውጤት (Outcome of the Study)

ከሙስና ስጋት ጥናት የሚጠበቀዉ ውጤት

- የተጠናከረ የፍርድ ቤቶች የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ጥናት ሪፖርት
- እንደየፍርድቤቶቹና የስራ ክፍሎች የተጋላጭነት ደረጃ መስጠት
- የእያንዳንዳቸውን የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ፕሮፋይል ማዘጋጀት
- የጥናት ውጤቱ ለፍርድ ቤት ሃላፊዎች እንዲደርስ ማድረግ
- በጥናቱ ውጤት ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ማካሄድ

## 1.7 **የጥናቱ ውስንነት**

የሙስና ወንጀል ውስብስብነት በዘርፉ የሚደረግን ጥናት አዳጋች ያደርገዋል፡፡ የተለመደዉ እና ልዩ ባህሪ የሆነዉ የሙስና *ሥጋት ጥናት ዉስንነት የሚያጋጥመው እና* በዚህ ጥናት ላይ የተስተዋለው ጉዳይ አንዳንድ ጥናቱ በተደረገባቸው የፍርድ ቤት አመራሮችና ሠራተኞች ለጥናቱ ገለልተኛ አለመሆን እና መረጃዎችን በተጨባጭ ማስረጃ ላይ ተደግፎ አለመስጠት ተስተውሏል፡፡ ይሄም የመጣው የተቋሙ የበላይ ሃላፊዎች ጥናቱ የተቋማቸውን የሙስና ሁኔታ ያጋልጣል ብለው ከማሰብ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ጥናቱ ትክክለኛ ማስረጃ ማግኘት አዳጋች አድርጎት ነበር፡፡ በተጨማሪም መጠይቁን አንዳንድ መልስ ሰጪዎች አለመረዳትና በዚህም ምክንያት ትክክለኛዉን መልስ ለመስጠት መቸገር ተስተውሏል፡፡ ከዚህ ጋርና መረጃ ሰጪዎች በሚፈለገው ፍጥነት ማግኘት ካለመቻል ጋር በተያያዘ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ መረጃ መሰብሰብ፤ ማጠናከርና መተንተን አዳጋች ሆኖ ነበር፡፡ ከናሙና አወሳሰድ ጋር

በተያያዘ የሚጠበቀው የጥናቱ ግኝቶች በሃገሪቷና በክልሎቹ ውስጥ ያለውን የፍርድ ቤቶች ለሙስና ያላቸው ተጋላጭነት ሙሉ ስእል ሊያሳዩ አይችሉም፡፡ ከዛ ይልቅ የጥናቱ ግኝት ሊያሳይ የሚችለው ትኩረት በተሰጠባቸው በታዎች ብቻ ነው፡፡

*የመፍትሄ አቅጣጫ*

1. ለመልስ ሰጪወች ስለጥናቱ አጠቃላይ አላማ ግንዛቤ ማሳደግ እንዲሁም የተቋሙን ሙስና ተጋላጭነት ሥጋት ለማጥናት እንጂ ለመመርመር፣ ለመክሰስና ጥቆማ ለማድረግ ሳይሆን ተቋማትን በተሻለ ደረጃ ለመገንባት ህብረተሰቡ በተቋማት ላይ አመኔታን ለማምጣት እንዲያስችል የሚደረግ ጥናት መሆኑን ማስረዳት ተችሏል፣
2. የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መጠቀም ተችሏል፤
3. *ግልጽና የማያሻማ ፤ ቀላልና ተገቢነት ያለዉ መጠይቅ* ተተግብሯል፡፡

**1.8 የቃላት ፍቺ**

ሙስና ማለት በኢትዮጵያ ፌደራል ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር በ881/2007; በተባበሩት መንግስታት የጸረ ሙስና ስምምነት (2003) እና በአፍሪካ ህብረት ሙስናን ስለመከላከል እና ስለ መዋጋት በወጣዉ ስምምነት (2003) ውስጥ የተካተቱ የሙስና ወንጀሎች ማለት ነው፡፡

**ስጋት ማለት፡-** የፍትህ ስርአቱ አላማ ግቡን እንዳይመታ የሚያደርግና አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር ክስተት ነው፡፡

**የስጋት ምንጭ፡-** ማለት በተቋም ወይም በሴክተር የሚገኝ ለሙስና ተጋላጭ የሚያደርግ ሂደት ወይም ባህሪይ /መገለጫ፡፡

**የሙስና ስጋት፡-** ማለት በቀጣይ የሙስና ወንጀል መከሰቱን አመላካች ነው፡፡

**የሙስና ተጋላጭነት፡-** የሙስና ወንጀል ለመፈጸም የሚያመች ውስጣዊ ወይም ውጫዊ የአሰራር ድክመት ነው፡፡

**የሙስና ስጋት ተጋላጭነትን ግምገማ፡-** በፍትህ ስርአት ውስጥ ያሉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቶችን ለመለየትና እነዚያን የሙስና ተጋላጭነት ስጋቶችን ለመቅረፍ ውጤታማና የተሻለ ስልቶችን ማስቀመጥ የሚያስችል ስልታዊ ዘዴ ነው፡፡

**ፍርድ ቤቶች ማለት፡-** በፌዴራልና ሮሚያ አና በደቡብ በክልል መንግስታት የሚገኙ ፍርድ ቤቶችን ያጠቃልላል፡፡

**የፍርድ ቤት ሰራተኞች ማለት**፦ በፍርድ ቤት ውስጥ በዳኝነት፤በሬጅስትራርነትና በድጋፍ ሰጪ አገልግሎት ላይ የሚሳተፉትን ነው፡፡

**ክፍል ሁለት**

## 2. የጥናቱ ስልት

ይህ የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት የተደረገው በፍርድ ቤቶች አሰራር ላይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የጥናቱ ስልትም የፍርድ ቤቶችን አሰራር ያማከለ የሙስና ስጋት ዳሰሳን የተከተለ ተደርጓል፡፡ ሙስናና ብልሹ አሠራር በጥናቱ ቦታ የሚያደርሰውን የሙስና ሥጋት ተጋላጭነት ዓይነታዊና መጠናዊ ዘዴ ተጠቅሟል፡፡

በፍርድ ቤቶች ውስጥ ባሉ አሠራሮች ውስጥ ለሙስና ሥጋት ተጋላጭነት የሚሆኑ የአሠራር ክፍተቶችን Value chain analysis ዘዴን በመከተል ከሚመለከታቸው ከፍርድ ቤቶች አመራሮች፣ ከውስጥ ኦዲት፣ ከፋይናንስ፣ ከሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች፣ ከሚቀርቡ አቤቱታዎች በጽሁፍ መጠይቅ፣በውይይት እና ሰነዶችን በመፈተሽ መረጃ ተሰብስቧል፡፡

## 2.1 የጥናቱ ቦታዎች

ጥናቱ የፌደራል ፍርድ ቤቶች እና የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የስራ ቦታ የሆነዉ አዲስ አበባ ከተማ ትኩረት ሰጥቶ የኦሮሚያና ደቡብ ክልሎች ውስጥ ያሉትን የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ፤የተመረጡ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችን እና ወረዳ ፍርድ ቤቶችን አካሏል። በዚህም መሰረት አዲስ አበባ ኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስራ ቦታ በመሆኑ ሌላዉ የጥናቱ ቦታ ነዉ ። እንዲሁም በስሩ ያሉ 3 ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እና 3 የወረዳ ፍርድ ቤቶች የስራ ቦታ የሆኑት አዳማ፤ሞጆ፣ ሻሸመኔ እና ጅማ ከተሞችንም ጨምሯል ። ሃዋሳ ከተማ የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስራ ቦታ ስለሆነ በጥናቱ ውስጥ የተካተተ ሲሆን በስሩ ያሉ 3 ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እና 3 የወረዳ ፍርድ ቤቶች የስራ ቦታ የሆኑት ወልቂጤ፣ ሶዶ፣ አርባ ምንጭ የጥናቱ ቦታ ተደርገዋል ። ያለው የጊዜና የሀብት ውስንነቶች፤ ጥናቱ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ ብቻ እንዲያተኩር አድርጎታል።

## 2.2 የጥናቱ ተሳታፊዎችና የተሳታፊ አመራረጥ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኮሚሽኑ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ባለባቸው ዘርፎች ላይ ጥናት አድርጓል። ከዚህ ውስጥ ይሄ ጥናት የሚያተኩረው የአስተዳደርና የፍትህ ዘርፉን ሲሆን። በጠቅላላው የአስተዳደርና የፍትህ ዘርፍ የሚይዘው 40 የፌደራልና ተጠሪ ተቋማትን ነው። ለዚህ ጥናት እንዲያመች ለሙስና ስጋት በይበልጥ ተጋላጭ የሆነውን የፍትህ ዘርፍ በተለይ በስሩ የሚገኙትን ፍርድ ቤቶችን አሰራር ትኩረት በመስጠት ለጥናቱ መረጣ አድርጎ ጥናቱን አካሂዷል። በዚሁ መሰረት በፌዴራል ደረጃ አንድ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፤ በአዲስ አበባ በልደታ ክፍለ ከተማ በሚገኙ ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፌደራል ፍርድ ቤቶች ተመርጠዋል ። በተጨማሪም የፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት እና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል። እንዲሁም በደቡብና ኦሮሚያ ክልሎች በእያንዳንዱ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፤በሶስት ዞኖች ውስጥ ያሉ ሶስት የከፍተኛ እና የወረዳ ደረጃ ፍርድ ቤቶችን አጣቃልሏል።

የመላሾች መረጣ የተደረገው ወሳኝ ንሞና አካል የሆነውን የዓላማ ተኮር ንሞና በመጠቀም ነው። ይሄም የሆነበት መረጃ ለመሰብሰብ የምንመርጣቸው ግለሰቦች ለችግሩ ቅርበት ያላቸውና የጥናቱን ዓላማ ለመመለስ ስለሚያስችል ነው። በዚህም መሰረት የተቋማቱ የበላይ አመራሮች፤ ዳኞች፤ ድጋፍ ሰጪ አመራሮችና ሰራተኞች፤ በተለያየ ደረጃ የሚሰሩ ባለሙያዎችና የስነ-ምግባር መኮንኖችን ተካተዋል። ይህንንም መጠይቅ ለማሟላት 8 ግለሰቦች በፌዴራል ደረጃ ካሉ ፍርድ ቤቶች ከአዲስ አበባ፤በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች እያንዳንዳቸው 14 ግለሰቦች፤ በጠቅላላው 28 ግለሰቦች ተመርጠዋል።በጠቅላላው 36 ግለሰቦች በሁሉም የጥናት ቦታዎች መጠይቅ ተደርጎላቸዋል። መጠይቅን ለመሙላት ለፌደራል ፍርድ ቤቶች 70 የጽሁፍ መጠይቆች ተሰራጭቷል። ለያንዳንዱ ክልሎች 142 መጠይቆች

ተሞልቷል። በጠቅላላው ለሁለቱ ክልሎች 284 መጠይቆች ተሞልቷል።ባጠቃላይ 354 መጠይቆች በሁሉም የጥናት ቦታዎች እንዲሞሉ ተደርጓል።

## 2.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Methods of Data Collection) እና ምንጮች (Data Sources)

### 2.3.1 የመረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴ

ለጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች የጥናቱን አላማ ሊያሳካ በሚችል መልኩ በመለየት በቁጥር የሚለኩ (Quantitative) እና በዓይነት (Qualitative) የሚለኩ የመረጃ መሰብሰቢያ አይነቶችን ተካቷል።

እነዚህ የሙስና ተጋላጭ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ፍርድ ቤቶች ለሙስና ያላቸውን ተጋላጭነትን አሳይተዋል። ይህንን ጥናት ለማካሄድ የመጀመሪያ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ስራ ላይ ውለዋል። እነዚህንም ለማግኘት የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ስራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል። እነሱም፡-

1. **የጽሁፍ መጠይቅ (Questionnaires)**

የጽሁፍ መጠይቁ የሙስና ስጋት ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎችንና አሰራሮችን ለመለየት መረጃ ለመሰብሰብ ጠቃሚ ሆኗል፡ ፡ በዝርዝር ለተነሱት የጥናቱ ዓላማዎች መልስ ለመስጠት በአባሪ የተያያዘ ዝርዝር ጥያቄዎች መረጃ ለመሰብሰብ በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅቶ በተግባር ላይ ውሏል።እነዚህም የጽሁፍ ጥያቄዎች ዝግና መጠን አመላካች ሆነው ተዘጋጅተው ለ354 መጠይቅ ሞይዎች እንዲደርስ ተደርጓል። መጠይቁን በሚሞሉ አካላት ያለውን ያለመመለስ እድል ለመቀነስ ሲባል በየተቋሙ በአንድ ጊዜ እንዲሞላና ከዚህ በታች ያሉ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎችን በተጨማሪ ተከትሏል። በተጨማሪም በግልጽ ስለ አለው ችግር በሀቀኝነት ለመመለስ በመላሾች ዘንድ ሊያስተዋል የሚችለውን ሁኔታ የጽሁፍ መጠይቅ ይቀርፍልናል ብለን በመታመኑ ቃለመጠይቅ በተግባር ላይ ውሏል።

2. **ቃለ መጠይቅ (Interviews)**

የጽሁፍ መጠይቅ የመላሾችን ነጻ ሃሳብ በችግሩ ዙሪያ ከማግኘት አንጻር የራሱ የሆነ ውስንነቶች ስለሚኖረው በዚህ ምርምር ስራ ቃለ መጠይቅ ትግበራ ላይ ይውላል። ከተወሰኑ ግለሰቦች ጋር የሚደረገው ቃለ መጠይቅ በችግሩ ላይ ጥልቅ የሆነ መረጃ እንዲገኝ ያስችላል። ጥናቱን ለመመለስ የሚረዱ ከፊል ነጻ ቃለ መጠይቅ በማዘጋጀት፤ በዘርፉ ካሉ 36 ባለሙያዎችና የበላይ ሃላፊዎች ጋር ቃለ-መጠይቅ በማድረግ ስለ ሙስና ወንጀል ስጋት ጥልቅ መረጃ ተሰብስቧል፡ ፡ እነዚህ ከጉዳዩ ጋር ቅርርቦሽ ያላቸውን ባለሙያዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ ማካተት፤ የፍርድ ቤቶችን የሙስና ስጋት በጥልቅ ለመረዳት አስችሏል። የፍርድ ስርአት ውስብስብነት በዘርፉ የሚሰሩትን ባለሙያዎች በመቅረብ ስለመረጃ ፍሰትና የፍርድ አሰራሩን በይበልጥ ለመገንዘብ ረድቷል። በዚህም የተነሳ ነው ቃለ መጠይቅ የጽሁፍ መጠይቅ ከማረግ በፊት ማድረግ በሙስና ተጋላጭነት ጥናት የሚመከረው።

3. **የሰነዶች (Documents) ዳሰሳ ናቸው።**

ጥናቱ ልዩ ልዩ አዋጆችን፤ ደንቦችን መመሪያወችን በተለይም የኢፍዲሪ ሕገመንግሰት፤የኢፍዲሪ ስነምግባርና ጸረ-ሙስና አዋጅና በኮሚሽኑ የተዘጋጁ ሪፖርቶች ፤ የፌደራል የፍ/ ቤት የዳኛች ስነምግባር ድንብ ፤የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ ቤት የስራ ክፍል ሀላፊወችና የሰራተኞች ስነምግባር መተዳደሪያ ድንብ ፤ ፤የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሰት ፍርድ ቤቶች የዳኛች ስነምግባር ድንብ፤ የተሻሻለዉ የደቡብ ክልል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ፤ የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ፤ የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አሰራር ለማተናከር የወጣ መመሪያ ፤ አንደገና የሻሻለዉ የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ዳኞችና በጉባኤ የሚተተዳደሩ ባለሙያወች የተፈላጊ ችሎታ ፤የምልመላና መረጣ ኮሚቴ ማቋቋሚያ ፤የአሰራር ስርአትና የስራ መዘርዘር መመሪያ የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች የዳኛች የስነምግባርና ዲሲሊን ድንብ ፤ የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤት ሙስና መከላከል ስትራቴጂ ሰነድ ዳሰሳ ተደርጓል። በተጨማሪም በፍርድ ቤቶች አሰራር ላይ የቀረቡ ቅሬታዎች፤ የዲሲፐሊን ጉዳዮች ፤ የኦዲት ሪፖርቶችና ተዛማጅ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ሰነዶችን ወይም ሪፖርቶች አግኝቶች ምርመራ አደርጓል።

**2.3.2 የመረጃ ምንጮች**

ለጥናቱ እንዲያመች አግባብነት ያለው መረጃ ከሁለት የተለያዩ ምንጮች ተገኝቷል። እነዚህም የመጀመሪያ እና ሁለተኛ መረጃ ምንጮች ናቸው።

**የመጀመሪያ ደረጃ መረጃምንጮች (Primary Data Sources) ምንጮች**

**ሀ) የጽሑፍ መጠይቅ**

የሙስና ተጋላጭነት ሥጋትን የሚመለከቱ ሁለት ዓይነት የጽሁፍ መጠይቅ በማዘጋጀት አሀዛዊና አሀዛዊ ያልሆኑ መረጃዎች ተሰብስቧል። ከዚህ ንድፈ-ሃሳብ ጋር በአባሪ ጋር የተያያዘውን ለመመልከት እንደሚቻለው በፍርድ ቤቱ አሠራር ውስጥ በይበልጥ ለሙስና ሥጋት ተጋላጭነት ያለውን አሠራር መለየት በሚያስችል መልኩ የመረጃ ማሰባሰብያ የጽሁፍ መጠይቆች ዝግ (closed ended) ተደርጎ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። በተጨማሪም መጠይቆቹ የፍርድ ቤቶችን አሰራር ሂደት በሚያመች መልኩ ተዘጋጅተው መረጃ የተሰበሰበው።

**ለ) ቃለ መጠይቅ**

ይህ ቃለ መጠይቅ ያተኮረው በየደረጃው ካሉ የሥራ ኃላፊዎች ጋር በመወያየት ነበር። ወደ አጠቃላይ አንድ ለአንድ መጠይቅ ከመግባት በፊት የሙከራ መጠይቅ በተወሰኑ ፍርድ ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች ጋር በማድረግ ጥያቄው ተፈትሿል። ከዚያም ከሚገኙ ግብአቶች ተመርኩዘን ፍቃድ በማግኘት ወደስራ ተገብቷል። ፍርድቤቶችን በመለየት

ስለአሰራራቸው የተሻለ ግንዛቤ ያላቸውና ምላሽ መስጠት የሚችሉ የተመረጡ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ጋር አስቀድሞ የተዘጋጀን የመወያያ ጥያቄ መሠረት በማድረግ በማወያየት መረጃ ማሰባሰብ ተችሏል ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ከበላይ አመራሮች ጋር ቃለ-መጠይቅ ከመደረጉ በፊት በታችኛው እርከን ላይ የሚሰሩትን አመራሮች ቃለመጠይቅ ማድረግ እና አስቀድሞ ጥያቄ ባለመስጠት በመጠይቁ ሂደት እና ውጤት ላይ የሚያሳድሩ አሉታዊ ተጽእኖችን ለመቅረፍ ጥረት ተደርጓል ።

### ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች (Secondary Data Sources)

ከመጀመሪያ ደረጃ መረጃ በተጨማሪ የሁለተኛ ደረጃ መረጃ ምንጭ ማሰባሰብ ሌላው ለጥናቱ ግብአት የሚሆን ተግባር ነበር። ይህ ተግባር የሚመለከታቸው የስራ ሂደቶች ያሏቸውን የአሰራር ሂደት ማሳያ ቼክሊስቶች፣ መዛግብቶች፣ የተቋሙ ውስጣዊ አደረጃጀታዊ መዋቅርና አስተዳደር፤ ዓመታዊ ሪፖርቶች፣ አዋጆች፣ መመሪያዎች፣ ደንቦች እና ማንዋሎች፤ የኦዲት (የውስጥና የውጭ) ሪፖርቶችና ሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ሰነዶች አካቷል። በተጨማሪም የፍርድ ቤቶችን አሰራር ሊወስኑ የሚችሉ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ዳራዎች እንደ መረጃ ምንጭነት ሊያገለግሉ ችለዋል። ባጠቃላይ እነዚህ መረጃዎች አጠቃላይ የአገሪቷንና የፍርድ ቤቶችን አውድና ቅድሚያ የምንሰጣቸውን የስጋት ቦታዎች እንድንለይ ረድቶናል።በልዩ ሁኔታ በስር ፍርድ ቤት ይግባኝ የተጠየቀባቸው የመዝገቦች ብዛት፤ ከነዚህ ውስጥ በይግባኝ እንዲጸናየተወሰነባቸው መዝገቦች ቁጥርና በይግባኝ የተሻሩ የመዝገቦች ቁጥር ተገምግሟል።

## 2.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ (Methods of Data Analysis)

በተለያዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች የተገኙት መረጃዎች ተጠናቅረው በአይነታዊና አሃዛዊ ተተንትነው ተተርጉመዋል። በመጀመሪያ ደረጃ ይሄንን ለማድረግ አስቀድሞ እንደተገለጸው ለጥናቱ የሚያግዙ መረጃዎች ከተለያዩ ቦታዎች በተለያየ መንገድ እንዲሰበሰቡ ተደርገዋል። እነዚህም መረጃዎች ዝርዝር የሙስና አደጋዎችና መንስኤዎቻቸው ጠቋሚ መረጃ ሆነው አገልግለዋል ። ለዚህም እንዲረዳ የፍርድ ቤቶች ሰራተኞችና ከፍርድ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ሰነዶችን መረጃ በማደራጀት በቃላትና በቁጥር ቀርቧል። በመጠይቅ የተሰጠውን መረጃ በሠነድ ከተገኘው መረጃ ጋር በማመሳከር፣ የተገኙትን ችግሮች ከሙስና ተጋላጭነት ሥጋት አንፃር ተቃኝቷሉ ። በቁጥር የሚቀርቡት ፐርሰንቴጅ በመጠቀም ነው። ከዚያም የመረጃ ቅነሳ ይደረጋል። SPSS በመታገዝ/በመጠቀም የተሰበሰቡ መረጃዎችን በጥልቀት ትንተና ተደርጓጋል። ይሄም ትንተና ለተነሱ የጥናቱ አላማዎች መልስ ለመስጠት ረድቷል።

ባጠቃላይ የሙስና ስጋት ዳሰሳ የሚከተለው አምስቱን ደረጃዎችን ያካተተ የትንተና ስልት ነው። ይሄም የሚያጠቃልለው፡ የዝግጅት ምእራፍ፤ የሙስና ስጋት ልየታ፤ የሙስና ስጋት ትንተና፤ ግምገማና የምክረ-ሃሳብን

ያጠቃልላል፡፡ በዚህም መሰረት የተሰበሰቡትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ እና ከዚህ ቀጥሎ የተገለጹትን ሁለት ጥቅል መመዘኛዎችን (የሙስና ተጋላጭነት ደረጃ እና ሙስና ቢፈጸም ሊደርስ የሚችለው ጉዳት) በመጠቀም በተቋማት ውስጥ ያለ እያንዳንዱን ተግባር የሙስና ተጋላጭነት ደረጃና የጉዳት መጠን ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ መሆኑን በመለየትና ውጤቱን በሪስክ ሜትሪክስ ውስጥ በማስገባት ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ የሙስና ተጋላጭነት ሥጋት ያለባቸው አሠራሮች/ ተቋማት የሚለዩ ይሆናል፡፡ ዝርዝር መመዘኛ መስፈርቱም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሀ/ የሙስና ተጋላጭነት ደረጃ

- ✓ ከስራው ባህሪ አንጻር፣
- ✓ በሚንቀሳቀሰው የገንዘብ መጠን፣
- ✓ በተዘረጋው የቁጥጥር ስርዓት፣

ለ/ ሙስና ቢፈጸም ሊደርስ የሚችለው ጉዳት

- ✓ ገንዘብ ነክ እና
- ✓ ገንዘብ ነክ ያልሆኑ ጉዳቶች፣

በመጨረሻም በስጋት ትንተና ሂደት በተገኘው ውጤት መሠረት እና ተዛማጅ አስተያየቶችን በማካተት እንደ የፍርድ ቤቶቹ አሰራር የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ቅደም ተከተል እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገቡ ጉዳዮች በምን ዘዴ/ስልት መፈታት እንዳለበት ከጉዳዩ ባህሪ አንፃር ሥልቶችን በመምረጥና በመወሰን የማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳብ ቀርቧል፡፡

## 2.5 ስነምግባር

ጥናቱ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ድረስ በስነምግባር መርሆች የታገዘ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ከችግር ልየታ፤ መረጃ አሰባሰብና ትንተና፤ሪፖርቱን መጻፍና ማቅረብ ሂደቶች የስነምግባር ሂደቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሆኗል፡፡ ጥናቱ በሚደረግበት ጊዜ ሀላፊነት በተሞላበት  የመረጃ ሰጪዎችን ፍቃደኝነት በማግኘት፤ እነሱን ባከበረና ጉዳት በማያደርስ መልኩ ተካሂዷል፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ ምን አይነት ጥቅም እንዳለው፤ ጥናቱን ማን እያሰራው እንደሆነና ለምን አላማ እንደሚካሄድ፤ የጥናቱ ውጤት አገላለጽ፤ የሚሰጡት መረጃ ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ መሆኑ ገለጻ ተደርጓል፡፡ ጥናቱ የሚያተኩረው የሙስና ተጋላጭነትና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ስለሆነ፤ ቃለ-መጠይቅ የሚያደርጉት ግለሰቦች ማንነታቸው እንዳይታወቅ የፈለጉትን፡፡ በዚህም የተነሳ ተለዋጭ ስም ወይም በቁጥር ማንነታቸው ተገጻል፡፡ በተለያየ ዘዴ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በትክክለኛው ሂደት በመከተልና እውነታውን በሚያንጸባርቅ መልኩ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ የመረጃ ትንታኔዎችም ትክክለኛውን ሳይንሳዊ መንገድ በመከተል ተካሂዷል፡፡ ጥናቱ ከአድሎ የጸዳና፤ መረጃዎችን ለአላግባብ አላማ ከመጠቀም ሂደቶች የሚያስችለውን እርምጃዎች

ወስዷል። በመጨረሻም የማጠቃለያ የሙስና ስጋት ዳሰሳ ሪፖርቱ ስነ-ምግባርን ባማከለ እና ማካተት ያለበትን በጠበቀ መልኩ ለስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን እንዲቀርብ ሆኗል።

# ምዕራፍ ሶስት

## የሙስና ስጋት ትንተና

### 3.1 መግቢያ

በዚህ ክፍል ውስጥ በፍርድ ቤት ውስጥ እየታዩ ያሉ የሙስና ስጋቶች ትንተና ሪፖርት ይቀርብበታል። የሙስና ስጋት ትንተናው የተዋቀረው በተለያየ ክፍሎች ነው። መጀመሪያ ትኩረት የሚሰጠው በፍርድ ቤት ላይ የሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶች ነው። ከዚያም የሙስና ስጋት ምክንያቶች ትንተና ይደረግባቸዋል።

### 3.2 በፍርድ ቤት ላይ የሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶች (Corruption Risks)

በተለያየ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በመጠቀም በፍርድ ቤት ላይ የሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶች ለመለየት ተችሏል። ከዚህ ውስጥ ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቷል።መጠይቆቹ ያተኮረው የበላይ አመራሮችና ሰራተኞችን ነበር፡፡ የተሰበሰበው መረጃና ትንተና እንደሚያሳየው የበላይ አመራሩ በብዙ በፍርድ ቤቶች አሰራርም እነደታየዉ የሙስና ስጋቶች ሢታዩ ለመቅረፍ የቁርጠኝነት ችግር አለበት ፣ በብዙ ፍርድ ቤቶች አሰራር አመራሩ እና ሰራተኛዉ ለብልሹ አሰራር መገምገሚያ ስረዓት የላቸዉም፤ የሙስና ስጋት አለባቸዉ ተብሎ በተገመቱ ስራ ሂደቶች ላይ የክትትል እና የቁጥጥር ስራዉ በቂ አይደለም።ቢኖርም የላላ ነዉ፡ ፡የበላይ አመራሩ ጥቆማዎችን የሚቀበልና ዉሳኔ የሚሰጥ ቢሆንም ተግባራዊነቱ ላይ ወጥ የሆነ ቁርጠኝነት የለም። ቀድሞ ለተነሱ ቅሬታዎች ምላሽ ባለመሰጠታቸዉ ደጋግመዉ የሚነሱበት ሁኔታ አለ።

ሌላኛው የሚታየው የሙስና ስጋ ከፍትህ ተደራሽነት እና የፍርድ ተገማችነት ጋር የተያያዘ ነው። ፍትህ ለሁሉም ሰዉ ተደራሽና ተገማች መሆን እዳለበት በአለም ዙሪያ ያሉ አገሮች የተቀበሉት አለማቀፋዊ መርህ ነዉ ።የኢፌድሪ ሕገመንግሰት ማነኛዉም ሰዉ በፍርድ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ለፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ የማግኘት መብት አለዉ ይላል (አንቀጽ 37 የኢፌድሪ ሕገመንግሰት) ። ሆኖም በሁሉም ፍ/ቤቶች በሚባል ደረጃ የዉጭ አገር እና አገር ዉስጥ ቋንቋ ተናጋሪ ተገልጋዮች ትጉረም ወጭ ከፍተኛ በመሆኑ በዚህ የፍትህ ተደራሽነት ችግር ይታያል ። በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ በጣም የተለያየ ዉሳኔ መስጠት የተለመደ ችግር ነዉ ። በመሆኑም የፍትህ ስርአቱ ተገማች የማይሆንበት የአሰራር ስርአት ቀላል የሚባለ አደለም ።

አፋጣኝ ዉሳኔ መስጠት ችግር ሌላኛው በፍርድ ቤት የሚስተዋል ችግር ነው፡ ፡ የዘገየ ፍትህ እንደተከለከል ስለሚቆጠር ማነኛዉም ሰዉ አፋጣኝ ዉሳኔ የማግኘት መብት አለዉ ። ሆኖም በዚህ ጥናት የታየዉ ያለምክንያት ቀጠሮ መቀየር ፤ ረዘም ያለ ቀጠሮ መስጠት ፤ አንድ አንድ ዳኞች ብዙ ጊዜ ቀጠሮ በመስጠት ጉዳዮችን ያጓትታሉ።፣ዳኞችም ሰበብ እየፈለጉ ለምርመራ በሚል ምክንያት ቀጠሮ ማብዛት ፤የጉዳዮች ውስብስብነት፤በፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ምክንያት፤ የዳኖች ቁጥር ማነስ እና የሚቀርቡ መዝገቦች አለመጣጣም፤ የጉዳዮች ውስብስብነት እና በሌሎች ተመሳሳይ ችግሮች ምክንያት የፍረድ መዘግይትእና የተዛባ ዉሳኔ ሰጠት ታይቷል።

ያለአድሎ ትክክለኛና ህጋዊ ውሳኔ መስጠት ህገመንግስታዊ ግዴታ ቢሆንምን በዚህ ጥናት የታየዉ በአብዛኛዉ ፍ/ቤቶት ባለጉዳይን በግልፅ ችሎት ያለማሰተናገድ፤ የተከራካሪ ወገኖችን ማሰረጃ በኩል አይን ያለመስማት ወይም የምስክር ቃልን አለመመዝገብ ወይም መቆራረጥ ፤ እኩል አለመመዘን፤ ባለጉዳይን ማመናጨቅ ፤ለተከራካሪ ወገኖች እኩል የክርክር ሰአት አለመስጠት፤ በችሎት ላይ በኩል አይን ያለማየት፣ እኩል ቅደም ተከተላቸውን ጠብቆ ያለማሰተናገድ ፤የፍርድ ምርመራ አለመኖር፤ለቅሬታወች በወቅቱ ምላሽ የአለመስጠት ችግሮች አሉ ። እንድሙሁም ጥፋተኛ ሊባል የማይገባዉን ሰዉ ጥፋተኛ ማለት; ጥፋተኛ ሊባል የሚገባዉን ሰዉ ደግሞ ጥፋተኛ አለማለት አልፎ አልፎ አለ :: ጥፋተኛ በተባለ ሰዉ ላይ ያለአግባብ ቅጣት መቀነስ ወይም መጨመር የሚስተዋል ችግር አልፎአልፎ አለ ።

በፍ/ ቤቶች ፍርድ የሚያዛቡ የአድሎ አይነቶች የሚያያዙት ከዳኞች ግንዛቤ ችግር መኖር ወይም አቅም ማነስ፣ የሥነ-ምግባር ችግር መኖር፣ህግን ተከትሎ ያለመስራት፤ በብሄርተኝነት፤ በጓደኝነት፤ አካባቢያዊ ግንኙነት መስራት ፤ በወገንተኝነት፤ በዘመድ አዝማድ መስራት፤ በጥቅማ ጥቅምወይም በመደለያ ወይም ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት መስራት ፤ የፖለቲካጣልቃ ገብነት አለ።የምስክር ቃሎች በመቅረፅ ድምፅ ይቀዳሉ አንዳንዴ የተቀረፁ ድምፆች ጠፉ ይባላል::

በፍርድ ቤት ፍርድን የሚያዛቡ አሰራሮች በአጭሩ ሲታዩ ህግን ተከትሎ ያለመስራት፤ ወገንተኝነት ወይም ማዳላት በዘመድ አዝማድ መስራት፤በጥቅማ ጥቅም ወይም በመደለያ መስራት ያልተገባ ጥቅም በማግኘት ባለጉዳን ማጉላላት ይታያል ።

ሙስናን ለመከላከል የዳኝነት ነጻነት እና ተጠያቂነት አንዱ ህገመንግስታዊ መርህ ነዉ (አንቀጽ 78 (1) የኢፌድሪ ሕገመንግሰት) ። ሆኖም በሁሉም ፍ/ቤቶች በሚባል ደረጃ የዳኞች ነጻነት በተገቢዉ መንገድ እየተተገበረ አይደለም ። ዳኞች ነጻ አደሉም ። የሚታዩ ችግሮችም የፖለቲካና የመንግስት ፈላጎት ባለባቸው ጉዳዮች ላይ የዳኞእን ነጻነነት መጋፋት ዉሳኔ ማዛባት አለ ። አልፎአልፎ ዳኞች በበላይ አለቃ ትእዛዝ ዉሳኔ እንድሰጡ ይደረጋል። ከዉስጥም ከውጪም ተፅእኖ ስላለ ብዙም ነፃነቱ አይታይም።

በህግ ኦፊሰሮች (ሪጅስትራር) በኩል አልፎ የሚታዩ የሚታዩ ችግሮች ባለጉዳይን በቅደም ተከትል ያለማስተናገድ፣ ፤ በዳኛ እና በባለጉዳይ መካከል ደላላ ሆኖ መቅረብ፣ትእዛዞችን በአግባቡ አለመጻፍ እና በጊዜው ወጪ አለማድረግ፣ መዝገብ ቶሎ ያለማቅረብ፣ መዝገቦች ሲቀርቡ አቃቂር በማውጣት የተሟላ መዝገብ አይደለም ብሎ በመመለስ ጉቦ ተቀብሎ መዝገቡን ተቀብሎ ወዲያዉ መክፈት ፣ የቀጠሮ ሰዓት በትክክል ያለማሳወቅ፣በቅደም ተከትል ያለማስተናገድ፣ መዝገብ ሳይጠፉ ጠፍተዋል ተሸፍነዋል፣ለመፈለግ ጊዜ ይፈልጋል በማለት መዝገብ ማፈላለጊያ እጅ መንሻ አልፎ አልፎ የሚጠይቁ ባለሙያዎች አሉ።

ለዳኛነት አገልግሎት ክፍያ ተብሎ የተሰበሰበን ገንዘብ በሰዓቱ ገቢ አለማድረግ ; የዳኝነት ክፍያ ሲሰበስቡ ደረሰኝ ማበላለጥ፤ ደረሰኝ ሳይቆረጡ ክፍያ መቀበል ከባለ ጉዳዩ የተቀበሉት ክፍያ እና ቀሪ የተደረገው ደረሰኝ ላይ የተጠቀሰው ገንዘብ አንድ አለመሆን ፤

መዝገብ በችሎት በሚፈለግበት ጊዜ ወዲያውን አለማውጣት፤ ትዛዝ በተሰጠ ጊዜ አለማውጣት ወይም በታዘዘው መሰረት አለመጻፍ፤ ለሚያውቁት ሰው ቅድሚያ መስጠት፤ ይገባኝም የተባሉ ተሎ ገልብጦ አለመስጠት እና መሟላት የሚገቡ ጉዳዮች ሳይሟሉ መዝገብ መክፈትና ማዘዝ፤መዝገቦችን መጣል፤ ክፍያዎችን መፈለግ ፤የመዝገቦችን ቅደም ተከተል ማዛባት፤የተቀረጹ ድምጾችን ወሳኝ ቦታ ላይ እንዳይሰሙ እንዲሰረዙ ማድረግ ታይቷል።

በህግ ኦፊሰሮች በኩል የሚስተዋሉ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች ባለጉዳዮችን እንዳመጣጣቸዉ ቅደም ተከተል አለማስተናገድ፤ ያለአግባብ ማመላለስ ይታያል። አልፎ አልፎም መዝገብ መጣል፣ መደበቅ፣ጥቅም መጠየቅ አለ።

በፍርድ አፈጻጸም በኩልም የተለያዩ ችግሮች ይስተዋላሉ። እነዚህም የፍርድ አፈጻጸም ማዘግየት፤ የፍረድ ባለዳዉን ንብረት በጨረታ ሸጦ ገንዘቡን ለፍርድ ባለመብቱ በፍጥነት አለመክፈል ፤፡በጨረታ ሂደት ደላሎች ከፍርድ ቤት ኦፊሰሮች ጋርአ አሻጥር በመስራት የፍረድ ባለዳዉን ንብረት ከዋጋው በታች እንዲሸጥ ማድረግ ፤በገጠር ቀበሌዎች አካባቢ የሚፈጸም ፍርድን የሚያስፈጽሙ አካላት ከተለያየ መስሪያ ቤት የተሰባሰቡ ስለሆኑ ከፍርድ ቤት አንድ ባለሞያ /የህግ ኦፊሰር ተወክሎ ከሌሎች ኮሚቴዎች ጋር በመሆን ፍድንን አንዲያስፈጽሙ በሚደረግበት ጊዜ ለኮሚቴዎቹ የሚከፈለውን ወጪ ወይም የውሎ አበል ከባለጉዳዮች እንዲሸፈን መደረጉ የፍርድ ቤቱ ተወካይ ኦፊሰሩን ጨምሮ የኮሚቴው አባላት ከባለጉዳዩ ከአቅም በላይ የሆነ ክፍያ መቀበል ፤ አንድ አንደም ሌላውን /የፍርድ ባለ እዳውን ለመጥቀም ሲሉ ፍርዱ ከመፈጸም ይልቅ ነገሮችን በተለያየ ምክንያት ማመቻቸት እንደሚሰተዋል አና የቅሬታ ምንጭ እንደሆነ ለመግለጽ መኩሯል። ከከተማ ቦታዎች ጋር በተያያዘ ሌላኛው የሚስተዋሉ የሙስና ችግሮች ክርክር ያልተደረገባቸዉን የይዞታዎች አዋሳኞችን በመጥቀስ የሥም ሊኬት ተለዋዋጭ ቀጠሮ እስኪሰጥ ታግዶ እንዲቆይ ትዕዛዝ በመስጠት የዉሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት አለመከተል ይስተዋላል። ሌላኛው በፍትሀብሄር የክስ መልስ ላይ የሚስተዋል ችግር ማስረጃ ቀዶ በማጥፋት። በተጨማሪም በህገወጥ በሆነ መንገድ ከማዘጋጃ ቤት

የከተማ ቦታ አጭብብሮ ይዞ መገኘት አልፎ አልፎ በፍርድ ቤት የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው ። ይህም የዲስፕሊን ግድፈት ለበለጠ ችግር የፍትህ ስርአቱን እየዳረገ ይገኛል፡፡

በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በኩል የሚስተዋሉ ችግሮች የዳኞች ምልመላ ፤መረጣ ፤ሹመትና እድገት ግልጽነት የጎደለዉ ነዉ፡፡ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አሰራር ግልጥነት የጎደለዉ መሆኑ፤ብዙ ጉዳዮችን ለራሳቸው ደብቀው መያዝ ፡፡ በዳኞች ምልመላና መረጣ ላይ ተገቢዉን ሰው አለመጋበዝ፤ መረጣው ለፍ/ቤቱ ሰራተኞች እንኳን ግልጽ ያለመሆን ፤ በምልመላው ወቅት ሊፈተሽ የሚገባው ጉዳይ በደንብ እንዳይታይ፤ የህዝቡን አስተያየት በግልጽ አለመውሰድ፤ ጉባኤው የሚመራበት መመሪያ ችግር ነው: በዚህ የስራ ክፍል የዳኝነት ተጠያቂነት ስርአት በጣም ረጅምና የተንዛዛ መሆኑ ሌላዉ ትልቅ ችግር ነዉ ። ለሚቀረቡ ቅሬታወች በፍጥነት ምላሽ የማይሰጥበት ሁኔታ ወይም አቤቱታዎችን የማዘግየት ሁኔታ እየተፈጠረ ይገኛል፡፡ችግሮች አብዛኛዉን የተማከለ ስልጣን መኖሩ፡፡ ይበልጥ ስልጣን የሚኖረዉ የጉባዔዉ ሰብሳቢ በመሆኑ ዋናዉ ችግር ነዉ ።

በሰዉ ሃብት አስተዳደር በኩል የሚታዩ የሙስና ስጋቶች ቅጥር፤ዝውውር፤ የደረጃ እድገት በዝምድና ፤ በፎርጅድ ማስረጃ ፤ ፤በአካባቢነት ፤በብሄር፤ በጓደኝነት መስራት፡፡ ህገወጥ የሰራተኛ ቅጥር ሲፈጸም የበላይ አመራር እያወቀ በቸልተኝነት ማለፍ ይስተዋላል፡፡ ሌላዉ በሰዉ ሃብት አስተዳደር ለሙስና የሚያጋልጡ አሰራሮች ወጥነት ያለዉ የሰራተኞች ቁጥጥር ያለመኖር፣የፍቃድ አሰጣጥ ክፍተቶች መኖር፡፡በሪከርድና በማህደር ባለሙያ ሰራተኞች የሚስተዋለው የሙስና ችግር የዲስፕሊን አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 21/2011 አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ ቁጥር 12/14 መተላለፍ ነው፡፡ የፍርድ ቤት ሰነዶች እንደሚያሳዩት ከሆነ ሀሰተኛ ማስረጃ ለቅርብ ወገን ሆን ብሎ ለመጥቀም ሲባል በታማኝነት አገልግለዋል የሚለዉን የሰዉ ሀብት መረጃ አስተዳደር ስም ቲተርና የሥራ ሂደቱን ቲተር በመጠቀምና አስመስሎ በመፈረም ሥራ ልምድ መስጠት አልፎ አልፎ ይስተዋላል፡፡

በፍርድ ቤት ባሉት የአስተዳደር ሰራተኞች የሚስተዋሉ የሙስና ችግሮችና ለሙስና አጋላጭ የሆኑ ድርጊቶች የሚስተዋሉት በቸልተኝነት የስርቆት ወንጀል እንዲፈፀም እና ንብረቱ እንዲባክንና ላልተገባ ወገን እንዲተላለፍ ማድረግ አልፎ አልፎ የሚታይ የሙስና ስጋቶች ናቸው፡፡ አንዳንድ የፍርድ ቤት ሰነዶች እንደሚያሳዩት በጥበቃ ሥራ ላይ ያሉ ግለሰቦች ቸልተኝነት ማሳየት ከባድ ዲስፕሊን ችግር ሆኖ ይታያል፡፡

በግዥና በፋይናንስ አስተዳደር በኩል ለሙስና የሚያጋልጡ አሰራሮች ግዥ ሲከናወን የጨረታ አወጣጥ ሂደቶች በቅድም ተከተል ያለማካሄድ ችግር ፤ከአንድ ድርጅት ወይም ከአንድ ሰው ላይ ሶስት ፕሮፎርማ እንዲያቀርብ ይደረግና እሱ ራሱ አሸነፈ ተብሎ ግዥ የሚፈጸምበት አሰራር ቀላል የሚባል አደለም፤ ያመጣዉ ጉዳትም የሚፈጸሙ ግዥዎች ወይም የሚገዙ እቃዎች ከደረጃ በታች መሆን ወይምጥራ ያለው እቃ ያለ ገዛት ችግር

አምጥቷል፡፡በግዥና ክፍያ ኦፊሰር አብዛኛውን ጊዜ የሚቀርቡ የሙስና ስጋቶች የሚያጠቃልለው የገቢና ወጪ ሂሳብ ሲመዘን በተለያዩ ጊዚያት ብር ማጉደል፣አልፎ አልፎ ከስራ ገበታ መቅረት ናቸው፡፡

የሙስና ስጋቶችም በኦዲት ግኝቶች ላይ በደንብ የሚስተዋል ጉዳይ ነው፡፡ በጥናት ወቅት የተሰበሰቡ ሰነዶች እንደሚያመለክቱት በፍርድ ቤት የተለያዩ የኦዲት ግኝቶች ቀርበዋል፡፡ እነዚህም የኦዲት ግኝቶች የሚያያዙት ከጥሬ ገንዘብ ሂሳብ፤የገቢ ሂሳብ፤የወጪ ሂሳብ እና ከንብረት ጋር ነው፡፡ ከፍተኛ የኦዲት ግኝትም ባይባል የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ በተመለከተ ባንዳንድ ጥናቱ በተካሄደባቸው ፍርድ ቤቶች በበጀት አመቱ መጨረሻ የካዝና ጥሬ ገንዘብ ቆጠራ አለማካሄድ፤በበጀት አመት የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ አለማዘጋጀትና በባንክ ቼክ መክፈል ሲገባው ከካዝና በጥሬ ገንዘብ መክፈል ናቸው፡፡ የገቢ ሂሳብ በተመለከተ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ ቅድመ ገቢ ግብር ሂሳብ ግኝት ይስተዋላል፡፡

ሌላኛው የኦዲት ግኝት ከወጪ ሂሳብ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እዚህ ላይ የአላግባብ የተከፈለ የውሎ አበል ሂሳብ፤ ህጋዊ ባልሆነ የሽያጭ ደረሰኝ ግዥ መፈጸም፤ የዕቃ ወይም የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ያልተቆረጠለት የወጪ ሂሳብ ብር መኖር ናቸው፡፡ ሌላኛው የሽያጭ ደረሰኝ (ፋኩትር) ሳይቀርብለት የተወዳደቀ የወጪ ሂሳብ መኖር፤ ከቀረበው የወጪ ማስረጃ በብልጫ የተወራረደና ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ የወጪ ሂሳብ ግኝት፤ የክፍያ ትእዛዝ ደብዳቤ ሳይኖር ክፍያ የተፈጸመ የስልጠና ወጪ ሂሳብ ግኝት፤ የተሽከርካሪ ጌጅ ንባብ ሳይሞላ የተፈጸመ የነዳጅ ግዥ የወጪ ሂሳብ መኖርና በመብለጥ ሪፖርት የተደረገ የወጪ ሂሳብ ግኝቶች ናቸው፡፡ሌላኛው የኦዲት ግኝት ደግሞ የንብረት አያያዝና አስተዳደር በተመለከተ ነው፡፡እዚህ ላይ የተጋነነም ባይሆን የኦዲት ግኝቶች እንደሚያመለክቱት የንብረት አስተዳደር ለብልሹ አሰራ የተጋለጠ ነው፡፡

### 3.3 የሙስና ስጋት ምክንያቶች (Corruption Risk Factors)

በተለያየ ጊዜ በፍርድ ቤቶች ላይ በሚደረጉ ውይይቶች እነደሚጠቀሰዉ ለሙስናና ለብልሹ አሰራር መነሻ ተደርገው የሚጠቀሱ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ምንም እንኳን በራሳቸው እንደ ሙስና ችግር የሚቆጠሩ ባይሆኑም፤ ለብልሹ አሰራሮች ገፊ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ ለምሳሌ የሚነሱት፤ የፍርድ ስርአቱ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አለመሆኑ፤ አብዛኛው ዳኞች በችሎት ላይ ተዘጋጅተው አለመቅረብ፤ ባለጉዳይን በችሎት ማመናጨቅ፤ባለጉዳይን በግባቡ አለማስተናገድ፤ የችሎትን ሰአት አክብረው አለመሰየም፤ ተደራራቢ ቀጠሮ መስጠት፤አቅም ማነስ፤የተዘዋዋሪ ችሎት ጉዳይ፤ ማስረጃ ማዛባት እና ለአንድ ወገን መወገን ናቸው፡፡ በተጨማሪም ለችግሮች መከሰት ምክንያት የሆኑ አሰራሮች ስንመረምር እነደሚከተለዉ ተዘርዝረዉ ቀርበዋል ፡፡በቂ ደሞዝ እና ጥቅማጥቅም ያለማግኘት፣ ምቹ የስራ ሁኔታን ያለመፍጠር ለምሳሌ በቂ እና ምቹ የትራንስፖርት ሰርቪስ

አገልግሎት ያለማግኘት፣ መኖሪያ ቤት ያለመመቻቸት፡፡ በዚኅም ምክንትየሰራተኞች በየጊዜው ከስራ መልቀቅ /ፍልሰት መኖር ይስተዋላል፡፡

በአንዳንድ ፍርድ ቤቶች በቴክኖሎጂ የተደገፈ ስርአት ለመዘርጋት ቢሞከርም፤ ጥናቱ በተካሄደባቸው ባብዛኛው ፍርቤቶች አሰራሮቻቸውን ለማዘምን ብዙ እርቀት አለመሄዳቸው ባለጉዳዩን ለብልሹ አሰራሮች ተጋላጭ እንዲሆኑ እዳረጋቸው መሆኑ በብዙ ሰነዶች ላይ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ ፍርድ ቤቶች በዘመናዊ አገልግሎት መስጫ ቁሳቁስ ምቹ አለመሆን ለምሳሌ ያህል የቢሮ ጥበትና አገልግሎት መስጫ ቁሳቁሶች አለመሟላት ለብልሹ አሰራሮች አጋላጭነት ፈጥሯል፡፡በበጀት እጥረት ምክንያት የጽህፈት መሳሪያ እና ቴክኖሎጂ እጥረት ፎቶ ኮፒ ሲበላሽ የመጠባበቂያ ፎቶ ኮፒ አለመኖር የተገልጋይ መጉላላት ይግባኝ በቶሎ ሰርቶ ለመስጠት በመቸገር የተገልጋይ እርካታ መቀነስ ተስተውሏል፡፡

የተሰበሰቡ የተለያዩ ሰነዶች እንደሚያመላክቱት ህብረተሰቡ በሚፈለገው መጠን ፈጣንና ጥራት ያለው ተደራሽ የሆነ የፍትህ አገልግሎት አለማግኘት ይስተዋላል፡፡ፈጣንና ጥራት ያለው ተደራሽ የሆነ የፍትህ አገልግሎት ፍላጎት ማሟላት አዳጋች የሆነባቸው ሁኔታዎች ይስተዋላሉ ምንም እንኳ ተዘዋዋሪ ችሎት ቢኖርም ምክንያቱም የመጓጓዣ እጥረት፤ የበጀት እጥረት፤ የችሎት ማስችያ ምቹ ያለመሆንና ብዛታቸው ማነስ፤ መረጃዎች በወቅቱ ተዘጋጅተው ያለመቅረብ፤ ህብረተሰቡ ለህግ በቂ ግንዛቤ የሌለው ስለሆነ፤ አመራሩ ህብረተሰቡን አለመዋያየት ዘመናዊ የቢሮ ቁሳቁሶች አለመሟላት ናቸው፡፡

ሌላዉ ምክንያት ደግሞ ባለሙያዉ ኃላፊነት እና ግዴታዉን በአግባቡ ተግባራዊ ካለማድረግ ይመነጫል፡፡ ይሄዉም ያላግባብ የመበልጸግ ፍላጎት፤ የእንዳንድ ሰራተኞች ዳኞችን ጨምሮ ለተመደቡበት ሀላፊነት ብቃት ማነስ ወይም የእውቀት ማነስ ፤ አቅምን ለማጎልበት ለመጣር ችግር መኖር ፡ በተለይም የዳኞች የሙያ ብቃት ማነስ ምክንያት የዳኞች ምልመላና መረጣ ፤ ሹመት በጥናት ላይ ያልተመሰረተ ፤ ግልጥነት ዕና ተጠያቂነት የጎደለዉ የትምህረት ዝግጅት እና በሙያ ብቃትን በደንብ ያላገነዘበ በብሄር ተዋጽና በፖለቲካ ዉሳኔ መኖን ነዉ ፡፡

ሌላዉ ለችግር የግላዊ ጥቅም ለማግኘት መረሯሯጥ ፤ በአቋራጭ ለመክበር የመፈለግ ዝንባሌ ይዞ ወደ ፍርድ ቤት መምጣት ነው፡፡ በተጨማሪም የቁጥጥር ስርአት መላላት እና ተጠያቂነት መላላት ወይም ማነስ እንዳንዴም አለመኖር ሌላዉ ለችግር ነው፡፡

በዳኝነት ስርአቱ ላይ አሉታዊ ተጽኖ እያደረሰ ያለዉ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነዉ ፡፡ ፖለቲከኞች ስልክ በመደወል (using telepone justice ) በዳኞች ላይ ጫና በማሳደር እነርሱ የሚፈልጉት ፍርድ እንዲፈረድ ወይም ሌሎች ስራዎች እንዲሰሩ የማድረግ ሁኔታዎች ይታያሉ፡፡ በዚህም ምክንያት የፍትህ ተደራሽነት እና የፍርድ ተገማችነት እንዳይኖር ፤ ፍርድ እንዲዛባ ፤ አፋጣኝ ዉሳኔ አዳይስጥ ምክንያት ሆነዋል ፡፡ በሌላ በኩል ከዳኞች ነጻነት ጋር

ተያይዞ የሚታየዉ ችግር ዳኛ ነጻ ነው በሚለው መርህ ተሸሽገው ተጠያቂ አይደለሁም በሚል የተሳሳተ ግንዛቤ ችግሮችን ሲፈጽሙ ይታያል ፡፡

በፍርድ አፈፃጸም አገልግሎት በይበልጥ ለሙስና የሚጋልጠዉ አሰራር የጨረታ አወጣጡ እና አፈጻጸሙ ሂደት ነዉ፡፡ የሚከሰቱ የሙስና ዓይነቶችም በጥቅም መስራት፣ ጉቦ መቀበል፣ በዘመድ መስራት ይታያያሉ፡፡ ለችግሮቹ ምክንያት በአብዛኛው የግላዊ ጥቅም ለማግኘት መረሯሯጥ ነዉ፡፡

የፍታብሄር ጉዳዮች በአብዛኛው በድምጽ መቅረጫ ማሽን ስለማይቀረጽ አልፎ አልፎ ዳኞች የምስክር ቃልን አለመመዝገብ ወይም መቆራረጥ እና ፍርድ ማዛባት አለ ፡፡

በአብዛኛው ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስራዎችና የሰው ሃብት መረጃዎችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ያለመደገፍ ይስተዋላል፡፡ ከሰው ሃብት ጋር በተያያዘ ንኡስ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤቶች በቂ የሰው ሃይል አለመሟላት **እና** ለፍርድ ቤቶች የቋንቀዋ አስተርጓሚ መደብ ቢቀረጽም ባለሙያ አለመመደብ ሌላኛው ችግር ነው፡፡ በተጨማሪም ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ አለመሟላት የሚያሳየው ፍርድ ቤቶች በፌደራልና ክልል ህግጋት ላይ በተደነነገገው መሰረት የሰው ሃይላቸውንና በጀታቸውን ሙሉ በሙሉ ማስተዳደር አለመቻላቸውና በመዋቅር መሰረት የሰው ሃይል ለማሟላት በቂ በጀት አለመመደብ ነው፡፡ ያሉትም የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች አቅም ውስንነቶች ይስተዋላል፡፡ እነዚህም የአቅም ውስንነቶች የሚያያዙት ከትምህርት፤ ስልጠናና የልምድ እጥረት ጋር ነው፡፡ ባጠቃላይ ሰነዶች እንደሚያሳዩት የሰው ሀይል እጥረትና የአቅም ውስንነቶች መኖር ጥናቱ በተካሄደባቸው ፍርድ ቤቶች ይስተዋላል፡፡

ሌላኛው ጉዳይ ደግሞ አስቀድሞ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ዳኞች በያዙት ጉዳይ ላይ ተዘጋጅቶ ባለመቅረባቸው በሰጡት ቀጠሮ መሰረት ተገቢውን ተግባር ሰርተው አለመምጣት ይስተዋላል፡፡ በዚህም የተነሳ ሰነዶች እንደሚያመለክቱት ስላልተመረመሩ በሚል ቀጠሮ ማብዛት ይሰተዋላል፡፡ ከዚህም አልፎ በተወሰኑ ዳኞች በመዝገብ ውይይት ያለመገኘት ወይም ማርፈድ እና በሰአት አልፎ አልፎ ቢሆን ያለፈቃድ መቅረት እና በራስ መወሰን እየተስተዋለ ያሉ ችግሮች ናቸው፡፡ ይህም ሁኔታ ባለጉዳዮችን ማጉላላት እና የፍ/ቤቱን አገልጋይነት ጥያቄ ላይ እየጣለ ያለ የአሰራር ችግር ነው፡፡በተጨማሪም በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የሚሻሩውስኔዎች አለመቀነሳቸው ጥናቱ በተደረገባቸው ፍርድ ቤቶች የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው፡፡

### 3.4 ፍርድ ቤቶች አሰራር ከሙስና ስጋት ተጋላጭነት አንጻር ሲታይ

#### 3.4.1 ሙስናን ለመከላል የሚረዱ አሰራሮችና መመሪያዎች

ለሙስና ተጋላጭነትን ለመቀነስ ከሚረዱት ዋነኞቹ የተቀዋማት አሰራሮችና መመሪያዎች ናቸው፡፡ አነዚህም የስነምግባር መከታተያ ክፍል፡፡ ስትራቴጂክ እቅድ፤ የብቃት ማጎልበት ስርአት፡፡ የእውቅና

ጥቆማና የተዘረጋ የኦዲት ስርአት ያካትታል። ከዚህ በታች የቀረበው ሰንጠረዥ ምንያህል ጥናቱ በተካሄደባቸው ፍርድ ቤቶች አሰራሮችና መመሪያዎች ሙስናን ለመከላከል መዘርጋታቸውን ያሳያል።

**ሰንጠረዥ 1 ሙስናን ለመከላል የሚረዱ አሰራሮችና መመሪያዎች**

| ተቁ | **አሰራሮችና መመሪያዎች በመቶኛ**(%) | አዎ | በሂደት ላይ | በሂደት ላይ | የለም | አላውቅም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መሰረት ተቋቁሟል | 76.57 | 6.57 | 14 | 12.85 | |
| 2 | የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ በፍርድ ቤቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዉስጥ ተካትቷል፤ | 50.57 | 17.91 | 20.52 | 10.98 | |
| 3 | በፍርድ ቤቱ ለአመራሮችና ስራተኞች በስነምግባር የታነጸ፤ ጥራትና ተገቢነት ያለው የስነ-ምግባር አቅምና ብቃት ማጎልበት የሚያስችል ስልጠና የሚሰጥበት መደበኛ ስርአተት ተዘርግቷል | 69 | 9.64 | 13.45 | 9.64 | |
| 4 | ፍርድ ቤቱ የአመራርና የሰራተኞች የሥነምግባር መመሪያ አለዉ፤ | 72.85 | 9.42 | 4.28 | 13.42 | |
| 5 | ፍርድ ቤቱ የዕቅድና የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሪፖርት ለሕዝብና ለመንግሥት ባለድርሻ አካላት እዉነተኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ ያቀርባል፤ | 64.38% | 15.38% | 10.25 | 9.97% | |
| 6 | ፍርድ ቤቱ ስለአገልግሎቱ ጥራት፤ ተገቢነት፤ ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ግንዛቤ ለማሳደግ የደንበኛ እና የባለድርሻ አካላት እርካታ በየወቅቱ ይለካል፤ | 42.2 | 20.11 | 30.59 | 7.08 | |
| 7 | በፍርድ ቤቱ ተገልጋዮችን በቅንነትና በታማኝነት፤ ከሙስናና ብልሹ ሰራር በጸዳ መልኩ የሚያስተናግዱ እና በመልካም ስነ ምግባር አረአያ የሆኑ አመራሮችና ሰራተኞች እውቅና የሚሰጥበት ስርአት ተዘርግቷል | 73.57 | 12.21 | 10.79 | 3.4 | |
| 8 | በፍርድ ቤቱ የአስተዳደር መዋቅር ሰራተኞች የመንግሥት የሥራ ሰዓት በአግባቡ እንዲጠቀሙ የቁጥጥር አሠራር ሥርዓት ተዘርግቷል፤ | 74.43 | 3610.22 | 6.81 | 8.52 | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 9 | በፍርድ ቤቱ ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበልና ተገቢዉን የእርምት እርምጃ ለመዉሰድ የተዘረጋ አሠራር ሥርዓት አለው፤ | 52.4 | 13.88 | 10.76 | 22.94 |
| 10 | በፍርድ ቤቱ ከሙስናና ብልሹ አሰራር ጋር ግንኙነት ያላቸው የውስጥ እና የዉጭ ኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ የሚወሰድበት እና የባከኑ ሃብቶች የሚመለሱበት አሠራር ሥርዓት ዘርግቷል፤ | 63.61 | 22.06 | 6.3 | 8.02 |

አሰራሮችና መመሪያዎችን በተመለከተ መረጃው በተሰበሰበባቸው ፍርድቤቶች እንደሚያሳየው 76.57% መጠይቁን የሞሉ ግለሰቦች የስነምግባር መከታተያ ክፍል በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 መቀቃወሙን ገልጸዋል፡፡ 6.5% የሚሆኑት መላሾች ደግሞ በተቀዋማቸው የስነ ምግባር መከታተያ ክፍል ምስረታ በሂደት ላይ የሚል ነው፡፡ ሆኖም የመከታተያ ክፍሉ መኖሩንና አለመኖሩን አለማወቃቸውን የገለጹት 12.85% ናቸው፡፡ ከጠቅላላው መላሾች ውስጥ 14% የሚሆኑት ተቀዋሙ በሚሩበት ተቋም ውስት እሰከ አሁን ድረስ በአዋጁ መሰረት አለመቋቀዋሙን ገልጸዋል፡፡

ሁለተኛው መጠይቅ ያተኮረው ምን ያህል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ በፍርድ ቤቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዉስጥ ተካትቷል፤ነው፡፡ እዚህ ላይ በመመርኮዝ ግማሽ ያህል መላሾች ማለጽም 50.57% የሚኖኑት መካተቱን ሲገልጹ፡፡ 17.91% መላሾች ደግሞ የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ በፍርድ ቤቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዉስጥ በመካጸጽ ላይ ሙኖኑን ገልጸዋል፡፡፤አለመካጸጹን ደግሞ 20.52% መላሶች ናቸው፡፡ ይሄም የሚያሳየው አንድ አምስተኛ የሆኑ መላሾች ባሉበት ፍርድ ቤት እየተተገበረ አለመሆኑ ነው፡፡ የስርአቱን መዘርጋት አላውቅም ብለው የሞሉት 10.98% መላሾች ናቸው፡፡

በፍርድ ቤቱ ለአመራሮችና ስራተኞች በስነምግባር የታነጸ፤ጥራትና ተገቢነት ያለው የስነ-ምግባር አቅምና ብቃት ማጎልበት የሚያስችል ስልጠና የሚሰጥበት መደበኛ ስርአት ተዘርግቷል በሚል በቀረበው መጠይቅ 69% መላሾች መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ 9.64% የሚሆኑ መላሾች በሂደት ላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡የነዚህ አዎና በሂደት ላይ የሚሉ መላሾች በጠቅላላው ወደ 80%ይጠጋሉ፡፡ ይሄ ውጤት የሚያሳየው በጉዳዩ ላይ የተሻለ ስርአት ዝርጋታ መኖሩ ነው፡፡ ሆኖም 13.45% መላሾች የሚኖኑ ስርአቱ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡ የስርአቱ መኖር አለማወቃቸውን የገለጹጵ 9.64% መላሾች ናቸው፡፡

ሌላኛው ለመጠይቅ ሞዪዎች የተነሳው ጥያቄ ደግሞ ፍርድ ቤቱ የአመራርና የሰራተኞች የሥነምግባር መመሪያ አለዉ ወይ የሚል ነበር፡፡ ከሰንጠረዡ ማየት እንደሚቻለው 72.85% የሚሆኑ መላሾች መመሪያ መኖሩን ነው፡፡ በሂደት ላይ መሆኑን ደግሞ የገለጹት 9.42 % መጠይቅ ሞዪዎች ናቸው፡፡ የሁለቱ መላሾች ስንደምረው ከ82% በላይ ይሄዳል፡፡ ይሄም ውጤት የሚያሳየው በአብዛኛው ፍርድ ቤቶች የአመራርና የሰራተኞች የሥነምግባር መመሪያ መኖሩን ወይም በሂደት ላይ መሆኑን ነው፡፡ ይሄም ፍርድ ቤቶች ለሙስና ተጋላጭነታቸውን ከመቀነስ አንጻር ሲታይ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ግን የመመሪያው አለመኖር የገለጹት ወገኖች 4.28 % ሲሆን ፡፡ስለመመሪያው መኖር እውቀት የሌላቸው ደግሞ 13.42% ከጠቅላላው መላሾች ናቸው፡፡

ሌላኛው ከአሰራሮችና መመሪያዎች ጋር የተያያዘው መጠይቅ የሚያተኩረውፍርድ ቤቱ የዕቅድና የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሪፖርት ለሕዝብና ለመንግሥት ባለድርሻአካላት እዉነተኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ ያቀርባል የሚል ነው፡፡ ይህንን መጠይቅ በተመለከተ 64.38% መላሾች አውንታዊ መልስ ሰተዋል፡፡ በሂደት ላይ ያሉት መላሾች ደግሞ 15.38% መላሾች ሲሆኑ 10.25% መጠይቁን የሞሉት መላሾች ደግሞ አሰራሩ አለመኖሩን ነው፡፡ ስለ አሰራሩ አለማወቃቸውን የገለጹት ደግሞ 9.97% መጠይቁን የሞሉት ናቸው፡፡

ስለ ባለድርሻ እና ደንበኛ አካላት እርካታ በየወቅቱ መለካት በተመለከተ ከጠቅላላው ከግማሽ በታች የሚሆኑ መላሾች (42.2%) መኖሩን አውንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በሂደት ላይ መሆኑን ደግሞ 20.11 % መላሾች መልስ ሰጥተዋል፡፡ አሰራሩን አለመኖሩን በፍርድ ቤቶች የገለጹጽ ደግሞ 30.59% ሲሆኑ ስለጉዳዩ ምንም እውቀት አለመኖራቸውን ደግሞ 7.08% መልሰዋል፡፡

አሰራሮችና መመሪያዎችን በተመለከተ ሌላኛው መጠይቅ ያተኮረው በፍርድ ቤቱ ተገልጋዮችን በቅንነትና በታማኝነት፤ ከሙስናና ብልሹ ሰራር በጸዳ መልኩ የሚያስተናግዱ እና በመልካም ስነ ምግባር አረአያ የሆኑ አመራሮችና ሰራተኞች እውቅና የሚሰጥበት ስርአት ስለመዘርጋቱ ነው፡፡ ይሄንን መጠይቅ በተመለከተ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መላሾች (73.57%) ስርአቱ ስለመዘርጋቱ አውንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ስርአቱን ለመዘርጋት በሂደት ላይ ስለመሆኑ የገለጹት 12.21% መላሾች ናቸው፡፡ የሁለቱ መላሾች ውጤት የሚያሳየው በፍርድ ቤቶች ውስጥ የተሻለ ለሰራተኞች እውቅና አሰጣጥ ትግበራ መዘርጋቱንና ለመዘርጋት በሂደት ላይ መሆኑን ያሳያል፡፡ ሆኖም ግን 10.79% መላሾች ስርአቱ አለመዘርጋቱን ገልጸዋል፡፡ ከጠቅላላው መላሾች ውስጥ አነስተኛው መላሾች የስርአቱን መዘርጋት የማያውቁ ናቸው፡፡ እነዚህም ከጠቅላላው 3.4% ይይዛሉ፡፡

የስራ ሰአት ቁጥጥር በተመለከተ ከፍተኛ የሆኑ መላሾች (74.43%) በሚሰሩበት ፍርድ ቤቶች ውስጥ የአስተዳደር መዋቅር ሰራተኞች የመንግሥት የሥራ ሰዓት በአግባቡ እንዲጠቀሙ የቁጥጥር አሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን ገልጸዋል፡፡ የስርአቱ መዘርጋት በሂደት ላይ ስለመሆኑ ደግሞ 10.22% መላሾች አረጋግጠዋል፡፡ የቁጥጥር ስርአቱ አለመኖሩን ደግሞ 6.81% የሚሆኑ መላሾች መጠይቁን ሞልተዋል፡፡ የስርአቱ መኖር አለማወቃቸውን የገለጹ ደግሞ 8.52% መላሾች ናቸው፡፡

በፍርድ ቤቱ ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበልና ተገቢዉን የእርምት እርምጃ ለመዉሰድ የተዘረጋ አሠራር ሥርዓት ስለመኖሩ በተነሳው መጠይቅ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ መላሾች ማለትም 52.4% መኖሩን አረጋግጠዋል፡፡ የአሰራር ስርአቱን ለመዘርጋት በሂደት ላይ ስመሆኑ የጽሁፍ መጠይቁን የሞሉት ደግሞ 13.88% ሲሆኑ ስርአቱ ስለአለመዘርጋቱ ደግሞ ምላሽ የሰጡት ሞዪዎች 10.76% ናቸው፡፡ ሆኖም ስለ አሰራር ስርአት መዘርጋት ምንም እውቀት ያለመኖራቸውን የገለጹት 22.94% ናቸው፡፡

የመጨረሻው ስለ አሰራርና መመሪያ የሚያጠነጥነው መጠይቅ ያተኮረውበፍርድ ቤቱ ከሙስናና ብልሹ አሰራር ጋር ግንኙነት ያላቸው የውስጥ እና የዉጭ ኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ የሚወሰድበት እና የባከኑ ሃብቶች የሚመለሱበት አሠራር ሥርዓት ስለመዘርጋቱ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ 63.61% የሚሆኑ መላሾች አውንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የአሰራር ስርአቱ እየተዘረጋ መሆኑን ደግሞ 22.06% መላሾች መልስ ሰጥተዋል፡፡ የሁለቱን ወገን መላሾች ድምር ውጤት ስናይ ከ85% በላይ የሚሆኑ ቃለመጠይቁን የሞሉት ግለሰቦች በፍርድ ቤት የተሻለ አሰራር መኖሩን ነው፡፡ ሆኖም 6.3% የሚሆኑ መላሾች የስርአቱ አለመዘርጋት ሲገልጹ ፤አላውቅም በማለት የመለሱት ደግሞ 8.02 % ናቸው፡፡

### 3.4.2 **የመረጃ ግልጽነት ደረጃ ስጋት**

**የ**መረጃ ግልጽነት ደረጃ ስጋት በተመለከተ መጠይቁ የሚያተነጥነው ስትራቴጂክ እቅድ የመንግሥት ዓመታዊ መደበኛና ካፒታል በጀት አጠቃቀምየፕሮጀክቶች አይነትና የበጀት የመረጃ ግልጽነትዕቅድ አፈጻጸምየበጀት አፈጻጸምግዥ አፈጻጸም ንብረት ቆጠራየተመዘነ ዓመታዊ የደንበኛ እርካታ ሪፖርት፡፡ ከዚህ በታች የተቀመጠው ሰንጠረዥ ምን ያህል የጽሁፍ መጠይቁን የሞሉት ግለሰቦች በፍ/ቤት የመረጃ ግልጽነት ስለመኖሩ የሚያመላክት ነው፡፡

**ሰንጠረዥ** 2 **የመረጃ ግልጽነት ስጋት ደረጃ**

| ተ.ቁ | **የመረጃ ግልጽነት ደረጃ ስጋት** | እስማማለሁ | በመጠኑ እስማማ | አልስማማም | አላውቅም |
|---|---|---|---|---|---|

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ለሁ | | |
| 1 | ፍርድ ቤቱ ፖሊሲና ስትራቴጂክ ዕቅድ የመረጃ ግልጽነት አለው | 55.3 | 23.2 | 10.6 | 10.88 |
| 2 | የመንግሥት ዓመታዊ መደበኛና ካፒታል በጀት አጠቃቀም የመረጃ ግልጽነት አለው | 52.7 | 19.94 | 12.25 | 15.09 |
| 3 | በፍርድ ቤቱ የፕሮጀክቶች አይነትና የበጀት የመረጃ ግልጽነት አላቸው | 71.14 | 18.28 | 5.14 | 5.42 |
| 4 | ወቅታዊና ዓመታዊ የፍርድ ቤቱ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት አለው | 64.18 | 22.06 | 7.16 | 6.59 |
| 5 | ወቅታዊና ዓመታዊ የፍርድ ቤቱ የበጀት አፈጻጸም ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት አለው | 49.85 | 22.79 | 13.67 | 13.67 |
| 6 | ወቅታዊና ዓመታዊ የፍርድ ቤቱ ግዥ አፈጻጸም ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት አለው | 43.3 | 25.35 | 15.66 | 15.66 |
| 7 | ዓመታዊ የፍርድ ቤቱ ን ንብረት ቆጠራ የሚያሳይ ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት አለው | 32.56 | 21.03 | 17 | 29.39 |
| 8 | የፍርድ ቤቱ የሚያስወግደዉ ንብረት የመረጃ ግልጽነት አለው | 28.85 | 21.42 | 19.71 | 30 |
| 9 | በገለልተኛ አካል የተመዘነ ዓመታዊ የደንበኛ እርካታ ሪፖርት ግልጽነት አለው | 36.28 | 29.42 | 12 | 22.28 |

**የ**መረጃ ግልጽነት ደረጃን በተመለከተ ለጽሁፍ መጠይቅ ለሞሉት ግለሰቦች የቀረበው ጥያቄ የሚያጠነጥነው ምን ያህል በፍ/ቤቱፖሊሲና ስትራቴጂክ ዕቅድ የመረጃ ግልጽነት ስለመኖሩ ነው፡፡ በዚህ መሰረት 55.3% የሚሆኑ መላሾች በፍርድ ቤት ግልጽነት ስለመኖሩ ይስማማሉ፡፡ በመጠኑ የሚስማሙት 23.2% የሚሆኑ መላሾች ናቸው፡፡ ስለሁኔታው አለመስማማታቸውን የገለጹት 10.6% መላሾች ሲሆኑ በጉዳዩ ላይ እውቀት አለመኖራቸውን ደግሞ 10.88% የሚሆኑ መልሰዋል፡፡

የመንግሥት ዓመታዊ መደበኛና ካፒታል በጀት አጠቃቀም የመረጃ ግልጽነት በተመለከተ 52.7% ከጠቅላላው የሚሆኑ ግለሰቦች ስለመኖሩ ተስማምተዋል፡፡ በመጠኑ መስማማታቸውን የገለጹጽ ደግሞ 19.94% የሚሆኑ ሲሆኑ አለመስማማታቸውን ደግሞ የገለጹት 12.25% ናቸው፡፡ ከጠቅላላው መጠይቁን ከሞሉት ግለሰቦች 15.09% የሚሆኑ ስላለው ዓመታዊ መደበኛና ካፒታል በጀት አጠቃቀም የመረጃ ግልጽነት አለማወቃቸውን ገልጸዋል፡፡

የፕሮጀክት አይነትና የበጀት መረጃ ግልጽነት በተመለከተ ከፍተኛ የሚሆን ቁጥር ያለው ማለትም 71.14% የሚሆኑ ስላለው ሁኔታ መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ 18.28% የሚሆኑ ሞዴዎች ደግሞ በመጠኑ መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ስላለው የመረጃ ግልጽነት አለመስማማታቸውን የገለጹት 7.16 % ሲሆኑ በመጠይቁ ላይ አለማወቀቸውን የገለጹጽ ደግሞ 5.42% ናቸው፡፡

ሌላኛው የመረጃ ግልጽነት ጥያቄ ያተከረው ወቅታዊና ዓመታዊ የፍርድ ቤቱ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት ላይ ነው፡፡ ይሄንን መጠይቅ በተመለከተ 64.18% የሚሆኑ መላሾች በፍ/ቤት መኖሩን ይስማማሉ፡፡ በመጠኑ የሚስማሙት 22.06% ናቸው፡፡ ይሄ የሁለቱ ውጤት የሚያሳየው የተሻለ የመረጃ ግልጽነት መኖሩ ነው፡፡ ሆኖም ግን 7.16% የሚሆኑት ግልጽነት ስለመኖሩ አይስማሙም፡፡ በጉዳዩ ላይ አለማወቃቸውን የገለጹት 6.59% ናቸው፡፡

የግዥ አፈጻጸም ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት በተመለከተ ከግማሽ በታች የሆኑ መላሾች (43.3%) ስለመኖሩ መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ 25.35% መላሾች ደግሞ በመጠኑ መስማማታቸውን ሲገልጹ በጉዳዩ ላይ አለመስማማታቸውና አላውቅም በማለት በተመሳሳይ እያንዳንዳቸው 15.66% የሚሆን ይይዛል፡፡ ንብረት ቆጠራን በተመለከት ያለውን የመረጃ ግልጽነት መስማማታቸውን የገለጹት 32.56% የሚሆኑ ሲሆን በመጠኑ መስማማታቸውን ደግሞ የገለጹት 21.03% ናቸው፡፡ አለመስማማታቸውን የገለጹት 17% ሲሆኑ በመጠይቁ ላይ አላውቅም በማለት የመለሱት 29.39% ነው፡፡

ሌላኛው የመረጃ ግልጽነት በተመለከተ ያተኮረው ጥያቄ ፍርድ ቤቱ በሚያስወግደዉ ንብረት የመረጃ ግልጽነት ላይ ነው፡፡ 28.85% የሚሆኑ መላሾች መስማማታቸውን ሲገልጹ 21.42% የሚሆኑት ደግሞ በመጠኑ መስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ አልስማማም በማለት የመለሱት 19.71% ሲሆን ስለጉዳዩ አላውቅም በማለት የመሱት ደግሞ 30% ናቸው፡፡ የመጨረሻው የመረጃ ግልጽነት ጥያቄ ትኩረቱን የሰጠው በገለልተኛ አካል የተመዘነ ዓመታዊ የደንበኛ እርካታ ሪፖርት ግልጽነት ስለመኖሩ ነው፡፡ በዚህም መሰረት 36.28% የሚሆኑ መጠይቁን የሞሉት መስማማታቸውን ሲገልጹ በመጠኑ መስማማታቸውን የገለጹት ደግሞ 29.42% ናቸው፡፡ እዚህ ላይ ስለመኖሩ አለመስማማታቸውን የሞሉት 12% ናቸው፡፡ 22.28% የሚሆኑ ደግሞ ስለ አመታዊ የደንበና እርካታ ሪፖርት ግልጽነት አላውቅም በማለት መልሰዋል፡፡

### 3.4.3 የተቋሙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አቅምና ብቃት ስለማሳደግና ማጎልበት

የተቋሙ የስነምግባርና መከታተያ ክፍል አቅምና ብቃት ስለማሳደግና ማጎልበት በተመለከተ ስድስት መጠይቆች ቀርበዋል፡፡ እነዚህም መጠይቆች ትኩረት የሚሰጡትስለክፍሉ አሰራ ስርአት ግልጽነት ማሻሻል፤ የማስተባበርና የመምራት አቅምና ብቃት፤ከሌሎች ክፍሎች ጋር ያለው ትስስር፤ትብብርና ቅንጅትና

የክፍሉ ሙስናን እንዲቀንስ ለማድረግ የዘረጋው ስርአትና አቅም ያካትታል፡፡ በዚህም መሰረት ከታች በሰንጠረዡ መጠይቁን የሞሉት ግለሰቦች እስማማለው፤ በመጠኑ እስማማለው፤ አልስማማምና አላውቅም በማለት መልሰዋል፡፡

**ሰንጠረዥ 3 የተቋሙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አቅምና ብቃት ስለማሳደግና ማጎልበት**

| ተ.ቁ | **የተቋሙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አቅምና ብቃት ስለማሳደግና ማጎልበት፤** | እስማማለሁ | በመጠኑ እስማማለሁ | አልስማማም | አላውቅም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የፍርድ ቤቱ የበላይ አመራር የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ምክረ-ሐሳቦችን መነሻ በማድረግ ተቋማዊ አሠራር ሥርዓት ግልጽነትን አሻሽሏል | 48.71 | 26.93 | 12.6 | 11.74 |
| 2. | የፍርድ ቤቱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ተልዕኮ ለማስተባበር አቅምና ብቃት አለዉ፤ | 53.56 | 24.78 | 11.1 | 10.54 |
| 3. | የፍርድ ቤቱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ የመምራት አቅምና ብቃት አለዉ/አላት፤ | 43.96 | 31.03 | 11.78 | 13.21 |
| 4. | የፍርድ ቤቱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ባለሙያዎች ተልዕኳቸዉን ለማከናወን በቂ አቅምናብቃት አላቸዉ፤ | 45.5 | 27.79 | 13.46 | 13.18 |
| 5. | የፍርድ ቤቱ ሥነምግባር መከታተያ ክፍል ከተቋሙ ሥራ ክፍሎች ጋር ትስስር፤ ትብብርና ቅንጅት በመፍጠር የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ተልዕኮ ይወጣል፤ | 41.54 | 30.65 | 14.61 | 13.18 |
| 6. | የፍርድ ቤቱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በተቋሙ ሙስና እንዲቀንስና ሥነምግባር ጉድለትእንዲታረም አሠራር ሥርዓት፤አቅምና ብቃት አጎልብቷል፤ | 47.7 | 31.53 | 13.06% | 7.67 |

የፍርድ ቤቱ የበላይ አመራር የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ምክረ-ሐሳቦችን መነሻበማድረግ ተቋማዊ አሠራር ሥርዓት ግልጽነትን አሻሽሏል ለሚለው ጥያቄ፤ 48.71% የሚሆኑ መላሾች መስማማታቸውን ሲገልጹ፤ በመጠኑ መስማማታቸውን የገለጹት ደግሞ 26.93% ናቸው፡፡ አልስማማም እና አላውቅም በማለት የመለሱት ደግሞ እያንዳንዳቸው 12.6% እና 11.74% ናቸው፡፡ የስነምግባር ክፍሉ ተልእኮውን ለማስተባበር ያለው አቅምና ብቃት በተመለከተ 53.56% የሚሆኑት መስማማታቸውን ሲገልጹ በመጠኑ መስማማታቸውን የገለጹት

ደግሞ 24.78% የሚሆኑ ናቸው። በክፍሉ አቅምና ብቃት ተልእኮውን ከማስፈጸም አንጻር 11.1% አልስማማም በማለት ገልጸዋል። በጉዳዩ ላይ ምንም እንደማያውቁ የገለጹት 10.54% መላሾች ናቸው።

የክፍሉ ሃላፊ የመምራት አቅም በተመለከተ ከግማሽ በታች መላሾች (42.96%) እስማማለሁ በማለት ሲመልሱ በመጠኑ መስማማታቸውን የገለጹት ደግሞ 31.03% ናቸው። በመጠይቁ ላይ አለመስማማታቸውን የገለጹት 11.78% ሲሆን ስለሁኔታው አላውቅም ብለው የመለሱት 13.21% ናቸው። የመከታተያ ክፍሉ ባለሙያዎች አቅምና ብቃት በተመለከተ 45.5% መላሾች መስማማታቸውን ሲገልጹ በመጠኑ መስማማታቸውን የገለጹት ደግሞ 27.79% መላሾች ናቸው። የስነ ምግባር ክፍሉ ሰራተኞች በቂ አቅምና ብቃት እንደሌላቸው የሚያምኑት 13.46% ሲሆኑ ስለጉዳዩ አለማወቃቸውን የገለጹት 13.18% ናቸው።

አምስተኛው መጠይቅ የሚያተኩረው የቅንጅትና የትብብር አሰራር በፍ/ቤቱ የስነምግባርና ጸረ-ሙስና ክፍል ከሌሎች የስራ ክፍሎች ጋር ተልእኮውን ለመወጣት ይሰራል የሚል ነበር። መስማማታቸውን የገለጹት መላሾች 41.54% ሲሆኑ በመጠኑ ስለሁኔታው መስማማታቸውን የገለጹት ደግሞ 30.65% ናቸው። ሆኖም አሉታዊ መልስ የሰጡት 14.61% ሲሆኑ ስላለው ትብብርና ቅንጅት አለማወቃቸውን የገለጹት 13.18% ናቸው። ሌላኛው ጥያቄ ትኩረት ያደረገው የስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና መከታተያ ክፍሉ ሙስና በፍ/ቤቱ እንዲቀንስ የአሰራር ስርአትና አቅም ዘርግቷል የሚል ነው። ለዚህም የጽኑፍ መጠይቅ አውንታዊ መልሳቸውን የሰጡት 47.7% ናቸው። 31.53% የሚሆኑ መላሾች ስለተነሳው ጉዳይ በመጠኑ መስማማታቸውን ገልጸዋል። በተቃራኒው አለመስማማታቸውን የገለጹት 13.06% ናቸው። 7.67% የሚሆኑ ከጠቅላላው መላሾች ስለተነሳው ጉዳይ አለማወቃቸውን ገልጸዋል።

### 3.4.4 **የተቋሙ የሙስና ተጋላጭነት ሥጋት የመቀነስና የግልጽነት ዕድገት ደረጃ፤**

በፍርድ ቤት ውስጥ የአሰራር ግልጽነትን ማስፈን የተቀሙ የሙስና ተጋላጭነትን የመቀነስ እድልን ከፍ ያደርገዋል። ይህም እንዲሳካ ተቀማት አመራሮቻውና ሰራተኞቻቸው ግንዛቤና ተነሳሽነት የሙያ ስነምግባርና የስነምግባር ልቀት ዋነኛ ጉዳዮች ናቸው።።። ከዚኅ በታች የሰፈረው ሰንጠረዥ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት የመቀነስ ግልጽነት እድገት ደረጃ ያሳያል።

**ሰንጠረዥ 4 የተቋሙ የሙስና ሥጋት ተጋላጭነት የመቀነስና የግልጽነት ዕድገት ደረጃ፤**

| ተ.ቁ | **የተቋሙ የሙስና ተጋላጭነት ሥጋት የመቀነስና የግልጽነት ዕድገት ደረጃ፤** | እስማማለሁ | በመጠኑ እስማማለሁ | አልስማማም | አላውቅም |
|---|---|---|---|---|---|

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የአመራርና የሰራተኞችን የሥነምግባር ጉድለት ለመቆጣጠርና ለማረም የተቋሙአመራር በቂ ግንዛቤና ተነሳሽነት አለዉ፤ | 45.04 | 34.84 | 11.04 | 9.06 |
| 2. | ፍርድ ቤቱ ፖሊሲ፤ ስትራቴጂ፤ ዕቅዶችንና ፕሮጀክቶችን ከሰነድነት ወደተግባር የመቀየርአቅምና ብቃት አለዉ ፤ | 41.04 | 35.83 | 15.60 | 7.51 |
| 3. | የተቋሙ ሁሉም አመራሮችና ሰራተኞች በተልዕኮና ርዕይ የጋራ ግንዛቤ አላቸዉ | 49.56 | 37.17 | 8.35 | 4.89 |
| 4. | በተቋሙ ያሉ ባለሙያዎች የሥራና የሙያ ሥነምግባር ያከብራሉ፤ | 40.57 | 32 | 13.42 | 14 |
| 5. | በተቋሙ ፆታዊ ትንኮሳዎችና ብልሹ ሥነምግባር ተጋላጭነት ለመከላከል የተዘረጋጸዋነለበተ የአሠራር ሥርዓት አለ፤ | 42.57 | 32.85 | 12.28 | 12.28 |
| 6. | የበላይ አመራር የሥነምግባር ልህቀት ምጣኔና ሙስናን የመከላከል አቅምና ብቃት አለው፤ | 39.48 | 42.07 | 10.37 | 8.06 |
| 7. | የተቋሙ የመካከለኛ አመራሮች የሥነምግባር ልህቀት ምጣኔና ሙስና የመከላከልአቅምና ብቃት አላቸው፤ | 40.57 | 40.28 | 9.42% | 9.71 |
| 8. | የተቋሙ የመጀመሪያ ደረጃ አመራሮች የሥነምግባር ልህቀት ምጣኔና ሙስና የመከላከልአቅምና ብቃት አላቸው፤ | 33.91 | 44.34 | 12.17 | 9.56 |
| 9. | የተቋሙ ሰራተኞች የሥነምግባር ልህቀት ምጣኔና ሙስና የመከላከል አቅምና ብቃት አላቸው፤ | 36.38 | 41.83 | 10.88 | 10.88 |
| 10. | በተቋሙ አገልግሎት አማካይ የደንበኛና የባለድርሻ የእርካታ ዕድገት ምጣኔ አሳይቷል ፤ | 61.20 | 26.14 | 8.62 | 4.02 |
| 11. | ፍርድ ቤቱ አገልግሎት የደንበኛና የባለድርሻ ቅሬታና አቤቱታ ማቅረቢያ ስርዓት ተዘርግቷ፤ | 52.33 | 27.48 | 9.94 | 10.23 |
| 12. | ፍርድ ቤቱ የአመራሩና የሰራተኛዉ የብልሹ ተግባራት መገምገሚያ ስርዓት ዘርግቷል፤ | 53.25 | 30.31 | 8.78 | 7.64 |

የተቀዋሙ አመራር የስነምግባር ጉድለት ለመቆጣጠር ያለው ግንዛቤና ተነሳሽነት 45.04% ነው። ከዚህ መጠይቅ ጋር በከፊል የሚመሳሰል መልስ የሰጡት ወገኖች በመጠኑ መስማማታቸውን (34.84%) ገልጸዋል። 11.04% የሚሆኑ መላሾች በመጠይቁላይ አለመስማማታቸውን ሲገልጹ ስለአመራሩ ግንዛቤና ተነሳሽነት አለማወቃቸውን የገለጹት 9.06% ናቸው። ሌላኛው የሙስና ተጋላጭነትን ለመቀነስ ከሚረዱ ነገሮች አንዱ በፍ/ቤት ያሉ ፖሊሲ።ስትራቴጂና

እቅዶች ወደተግባር የመቀየር አቅም ነው። በዚህም መሰረት 41.04% የሚሆኑ መጠይቁን የሞሉት ተሳታፊዎች አውንታዊ መልስ ሰጥተዋል። የሰነዶች ወደ ተግባር የመቀየር አቅምን በከፊል መኖሩን በመጠኑ መስማማታቸውን የገለጹት 35.83% ናቸው። ከጠቅላላው መላሾች 15.60% ፍርድ ቤቱ የሙስና ተጋላጭነት ለመቀነስ ወደ ተግባር የመቀየር አቅምና ብቃት አለመኖሩን አመላክተዋል። ስላለው ሁኔታ አለማወቃቸውን የገለጹት 7.51% ናቸው።

ግማሽ ያህል የጽሁፍ መጠይቅ ሞዩዎች የሚስማሙት የተቀዋሙ አመራሮችና ሰራተኞች በተልእኮና ርዕይ የጋራ ግንዛቤ እንዳላቸው ነው። 37.17% የሚሆኑ መላሾች በመጠኑ መስማማታቸውን ገልጸዋል። የጋራ ግንዛቤ በፍ/ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ አለመኖሩን የገለጹት 8.35% ሲሆኑ ስለሁኔታው አላውቅም በማለት የመለሱት 4.89% ናቸው።። የፍ/ቤቱ ሰራተኞች የስራና የሙያ ስነምግባር ማክበር በተመለከተ 40.57% እስማማለው በማለት መልሰዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ 32% በመጠኑ መስማማታቸውን ሲገልጹ 13.42% የሆኑ መላሾች አለመስማማታቸውን ገልጸዋል። አላውቅም በማለት የገለጹት ሰዎች 14% ናቸው።

እንደ ጾታዊ ትንኮሳዎች የመሳሰሉ ብልሹ የስነምግባር ተጋላጭነትን ለመከላከል የተዘረጋ ስርአት በተመለከተ ከግማሽ በታች የሆኑ መላሾች (42.57%) መስማማታቸውን ገልጸዋል። በከፊል መስማማታቸውን የገለጹት 32.85% ሲሆኑ 12.28% የብልሹ ተጋላጭነት ለመከላከል የተዘረጋ አሰራር አለመኖሩን ሲገልጹ ተመሳሳይ መጠን ያላቸው መላሾች ስለጉዳዩ አለማወቃቸውን ገልጸዋል።

የስነምግባር ልህቀትና ምጣኔን በአጠቃላይ በበላይ በመካከለኛና የመጀመሪያ ደረጃ አመራሮች በተመለከተ ከግማሽ በታች መላሾች መስማማታቸውን ሲገልጹ። ከመላሾች ውስጥ 42.07% ስለከፍተኛው አመራር 40.28% ስለ መካከለኛው አመራር 44.34% ስለ መጀመሪያ ደረጃ አመራር የስነምግባር ልቀት ምጣኔ መኖሩን በከፊል ተስማምተዋል። ሆኖም ግን ተወሰኑት የመጠይቁ መላሾች ሙስናን መከላከል አቅም ያለው የስነ ምግባር ልህቀት ምጣኔ አለመኖሩን ገልጸዋል። እንደ ደረጃው 8.06% 9.71% እና 9.56% የሚሆኑ መላሾች የስነ ምግባር የልህቀት ምጣኔ በከፍተና።በመካከለኛና በመጀመሪያ ደረጃ አመራሮች ስለመኖሩ እውቀት እንደሌላቸው ገልጸዋል። የሰራተኞች የስነ ምግባር የልህቀት ምጣኔን በተመለከተ 36.38% መላሾች መስማማታቸውን ሲገልጹ 41.83% የሚሆኑ መላሾች ደግሞ በከፊል መስማማታቸውን ገልጸዋል። ንገር ግን ስለመኖሩ አለመስማማታቸውን የገለጹት 10.88% መላሾች ናቸው። በመጠይቁ ላይ አላውቅም በማለት የመለሱት አለመስማማታቸውን ከገለጹት ጋር ተመሳሳይ ነው።

በተቋሙ አገልግሎት አማካይ የደንበኛና የባለድርሻ የእርካታ ዕድገት ምጣኔ ስለማሳየቱ ከተጠየቁት ውስጥ 61.2% መላሾች መስማማታቸውን ሲገልጹ በከፊል መስማማታቸውን ደግሞ 26.14% ተሳታፊዎች ገልጸዋል። በመጠይቁ አለመስማማታቸውን የገለጹት 8.62% ሲሆኑ ስለሁኔታው አላውቅም በማለት ያሰፈሩት ደግሞ 4.02% ናቸው። ስለ ደንበኛና የባለድርሻ ቅሬታና አቤቱታ ማቅረቢያ ስርዓት ዝርጋታ በተመለከተ

ከግማሽ በላይ የሚሆነ መላሾች(52.33%) አውንታዊ መልስ ሲሰጡ በመጠኑ መስማማታቸውን የገለጹት የጽሁፍ መጠይቅ መላሾች የሚሆኑት 27.48% ናቸው፡፡ ስርአቱ አለመዘርጋቱን የገለጹት 9.94% ሲሆኑ ስለ ስርአት መዘርጋት እውቀት የሌላቸው 10.23% ይሆናሉ፡፡ የመጨረሻው የሙስና ተጋላጭነት ስጋት የመቀነስ የግልጽነት እድገት ደረጃ መለኪያ መጠይቅ ትኩረት የሚሰጠው የአመራሩና የሰራተኛዉ የብልሹ ተግባራት መገምገመያ ስርዓት ዝርጋታ ላይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት መስማማታቸውን የገለጹት 53.25% ሲሆኑ በከፊል መስማማታቸውን ያረጋገጡት 30.31% ናቸው፡፡ ሆኖም 8.78% መላሾች ስለመዘርጋቱ አለመስማማታቸውን ገልጸዋል፡፡ ስለ ስርአቱ መዘርጋት እውቀት የሌላቸው 7.64% ናቸው፡፡

### 3.4.5 በተቋሙ የሙስና እና ብልሹ ተግባራትን መረጃ የማመንጨት አቅመና ብቃት

በፍ/ቤት ውስጥ ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ከሚያስፈልጉ ዋናኛው መረጃን የማመንጨት አቅምና ብቃት ነው፡፡ ይሄ እንዲሆን ፍ/ቤቱ ጥቆማዎችን የመቀበል የማደራጀት ውሳኔ መስጠት፡፡ ለጠቆሚዎች ከለላ መስጠት፡፡ በተጨማሪም የሙስና መረጃ ምዝገባና የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ ያጠቃልላል፡፡ ከዚህ አንጻር ከታች የሰፈረው ሰንጠረዥ ይተነተናል፡፡

ሰንጠረዥ 5 **በተቋሙ የሙስና እና ብልሹ ተግባራትን መረጃ የማመንጨት አቅመና ብቃት**

| ተ.ቁ | **በተቋሙ የሙስና እና ብልሹ ተግባራትን መረጃ የማመንጨት አቅመና ብቃት** | እስማማለሁ | በመጠኑ እስማማለሁ | አልስማማም | አላውቅም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የፍርድ ቤቱ የበላይ አመራር ጥቆማዎችን የ መቀበልና ውሳኔ የመስጠት ዝግጁነት፤ተነሳሽነትና ተግባራው የማድረግ አቅም አለው፤ | 46.02 | 29.82 | 10.51 | 13.63 |
| 2. | ፍርድ ቤቱ የሙስናና ብልሹ ተግባራት ጥቆማዎችን በማደራጀት ለኮሚሽኑ የማቅረብአቅም፤ ብቃት አለው ፤ | 42.32 | 29.26 | 8.52 | 19.88 |
| 3. | ፍርድ ቤቱ የሙስናና ብልሹ ተግባራት ጥቆማዎችን እና ምክረ ሃሳቦችን ወስዶ ተግባራዊ አድርጓል | 32.19 | 21.36 | 12.53 | 33.9 |
| 4. | የፍርድ ቤቱ የተመዘበረ ሀብት በመረጃ ላይ በመመስረትና ክትትል በማድረግ ለማስመለስጥረት አድርጓል፤ | 35.79 | 26.13 | 14.48 | 23.57 |
| 5. | የፍርድ ቤቱ ጠቋሚዎች የሙስናና ብልሹ ተግባራት ጥቆማ እንዲያቀርቡ የመፍጠር የማበረታትና የማነሳሳት ስራ ይሰራል፤ | 45.17 | 26.42 | 13.06 | 15.34 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 6. | ተቋሙ ተገልጋይ እና ባለድርሻ አካላት ጥቆማ እንዲያቀርቡ ግንዛቤ የመፍጠር ሰራ ሰርቷል፤ | 21.14 | 21.42 | 17.42 | 40 |
| 7. | የፍርድ ቤቱ ጠቋሚዎች የሥራና የሕይወት ዋስትና ከላለ/ጥበቃ እንዲሰጣቸው ክትትልናድጋፍ ያደርጋል፤ | 19.31 | 25.28 | 25.85 | 29.54 |
| 8. | የፍርድ ቤቱ ተጨባጭ ሁኔታ ሙስናና ብልሹ አሠራር ለመከላከል የሚያግዙ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችን፡ክለቦችንና ንቅናቄዎችን እንዲፈጠሩ ያበረታታል፤ | 42.07 | 26.8 | 15.85 | 15.27 |
| 9. | ፍርድ ቤቱ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት አፈጻጸም ሪፖርት ለሕዝብ ተደራሽ አድርጓል | 56 | 20.57 | 12 | 11.42 |
| 10. | ፍርድ ቤቱ ከሙስና እና ብልሹ ተግባር የጸዱ ስለመሆናቸዉ ጥቆማ የመቀበል የሕዝብና የባለድርሻ አካላት አስተያየት የመሰብሰብ ስርዓት አለው፤ | 38.46 | 30.76 | 13.96 | 16.8 |
| 11. | ፍርድ ቤቱ ሙስና እና ብልሹ ተግባር የመተንተንና ማሻሻያ እርምጃዎችን የመዉሰድ አሠራር ሥርዓት ዘርግቷል | 25.21 | 23.2 | 22.34 | 29.22 |
| 12. | ሙስና እና ብልሹ ተግባራት መረጃ ጥቆማ አቅርቦትና የጠቋሚዎች የማበረታቻ አሠራርሥርዓትና ትግበራ አለው፤ | 39.88 | 24.5 | 13.39 | 22.22 |
| 13. | የሙስና ተግባራት መረጃና ማስረጃ፤ አቅርቦትና የፍትህ ዉሳኔ አሠጣጥ ሰርዓት አለው፤ | 31.32 | 25.28 | 15.8 | 27.58 |
| 14. | በተቋሙ የሙስና መረጃ ጥቆማ በቴክኖሎጂ አማራጮች የማከናወን ስርአት ዘርግቷል | 44.22 | 29.02 | 11.78 | 18.96 |
| 15. | የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ አዋጅ አለማክበር የሚያስከትለዉ ቅጣት ግንዛቤ ደረጃ ጨምሯል | 39.08 | 26.14 | 12.93 | 21.83 |
| 16. | የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ አዋጅ ለጠቋሚዎች የሚያስገኘዉ ጥቅም ግንዛቤ አድጓል | 65.52 | 20.79 | 3.7 | 9.97 |

የፍርድ ቤቱ የበላይ አመራር ጥቆማዎችን የ መቀበልና ውሳኔ የመስጠት ዝግጁነት፤ተነሳሽነትና ተግባራው የማድረግ አቅም በተመለከተ እስማማለው በማለት የመለሱት 46.02% ሲሆኑ ከዚህ ጋር በከፊል በተያያዘ በመጠኑ እስማማለው ያሉት 29.82% መላሾች ናቸው፡፡ አለመስማማታቸውን የገለጹት 10.51% መላሾች

ናቸው። ሆኖም ስለሁኔታው አላውቅም ብለው የመለሱት 13.63% ናቸው። ፍ/ቤቱ ጥቆማዎችን በማደራጀት ለኮሚሽኑ የማቅረብ አቅምና ብቃት በተመለከተ 42.32% መላሾች እስማማለው በማለት ሲመልሱ በመጠኑ መስማማታቸውን የገለጹት 29.26% ናቸው። በጥያቄው ላይ አለመስማማታቸውን የገለጹት 8.52% ሲሆኑ አላውቅም በማለት የመለሱት 19.88% ናቸው።

ፍርድ ቤቱ የሙስናና ብልሹ ተግባራት ጥቆማዎችን እና ምክረ ሃሳቦችን ወስዶ ተግባራዊ አድርጓል ለሚለው ጥያቄ አውንታዊ መልስ (32.19%) የሰጡት ዝቅተኛ ናቸው። ስለ ጉዳዩ በመጠኑ እስማማለው በማለት የመለሱት 21.36% ሲሆኑ አለመስማማታቸውን የገለጹት ደግሞ 12.53%። አንጻራዊ የሆነ ከፍተኛ መላሽ ያለው አላውቅም (33.9%) በሚለው ስር ነው። የተመዘበረ ሀብት በመረጃ ላይ በመመስረትና ክትትል በማድረግ ለማስመለስ ጥረት ስለመደረጉ 35.79% መላሾች እስማማለው በማለት ሲመልሱ በመጠኑ መስማማታቸውን የገለጹት 26.13% መላሾች ናቸው። አልስማማም በማለት የመለሱት 14.48% ተሳታፊዎች ሲሆኑ 23.57% የሚሆኑ መላሾች አላውቅም በማለት መልሰዋል።

ሌላኛው ጥያቄ የሚያተኩረው ፍርድ ቤቱ ተገልጋይ እና ባለድርሻ አካላት ጥቆማ እንዲያቀርቡ ግንዛቤ የመፍጠር ሰራ ስለመስራቱ ነው። ከዚህ አንጻር እስማማለው በማለት የመለሱት 45.17% ሲሆኑ በመጠኑ እስማማለው በማለት የመለሱት 26.42% ናቸው። ሆኖም አልስማማም በማለት የመለሱት 13.06% ሲሆኑ አላውቅም በማለት የመለሱት 15.34% ናቸው።

በፍርድ ቤት ተገልጋዩን እና ባለድርሻ አካል ጥቆማ እንዲያቀርብ ግንዛቤ ከመፍጠር አንጻር ዝቀተኛ ነው። ከላይ ከተቀመጠው ሰንጠረዠ መረዳት እንደሚቻለው 21.14% የሚሆኑ የጽሁፍ መጠይቅ የሞሉ ግለሰቦች በፍርድ ቤቱ ጥቆማ እንዲቀርብ ግንዛቤ መፍጠር ስራ መኖሩን ይስማማሉ። በመጠኑ እስማማለሁ በማለት የመለሱት 21.42% ተሳታፊዎች ናቸው። በሁኔታው አለመስማማታቸውን የገለጹት 17.42% ሲሆኑ አላውቅም በማለት የመለሱት 40% ናቸው። ቀደም ብሎ ከሰፈረው መጠይቅ ጋር በተያያዘ ፍርድ ቤቱ ለጠቋሚዎች ከለላ ለመስጠት የዘረጋውን ስርአት በተመለከተ መስማማታቸውን የገለጹት 19.31% ሲሆኑ በመጠኑ መስማማታቸውን የገለጹት ደግሞ 25.28% ናቸው። ከግማሽ በላይ የሆኑት መላሾች ስለተዘረጋው ስርአት አለመስማማታቸውንና አለማወቃቸውን ገልጸዋል።

ብልሹ አሠራር ለመከላከል የሚያግዙ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችን፣ክለቦችንና ንቅናቄዎችን እንዲፈጠሩ ከማበረታታት አንጻር መስማማታቸውን እና በመጠኑ እስማማለሁ በማለት የመለሱት እያንዳንዳቸው 42.07% እና 26.8% ናቸው። ለጥያቄው አለመስማማታቸውን የገለጹት 15.85% ሲሆኑ ስለ አሰራሩ ምንም አለማወቃቸውን የገለጹት 15.27% ናቸው።ዓመታዊ ዕቅድና በጀት አፈጻጸም ሪፖርት ለሕዝብ ተደራሽ ከማድረግ አንጻር 56% የሚሆኑ መጠይቁን የሞሉት ግለሰቦች እስማማለው በማለት ሲመልሱ 20.57%

መላሾች ለጥያቄው በመጠኑ መስማማታቸውን ገልጸዋል። ሆኖም አለመስማማታቸውን የገለጹት 12% ሲሆኑ ስለሁኔታው አለማወቃቸውን የገለጸት ደግሞ 11.42% ናቸው።

በፍ/ቤቱ ጥቆማ የመቀበል የሕዝብና የባለድርሻ አካላት አስተያየት የመሰብሰብ ስርዓት ስለመኖሩ ለቀረበው መጠይቅ 38.46% ተሳታፊዎች እስማማለሁ በማለት ሲመልሱ በመጠኑ መስማማታቸውን የገለጹት 30.76% ናቸው። ስርአት ስለመኖሩ 13.96% ተሳታፊዎች አለመስማማታቸውን ሲገልጹ አላውቅም በማለት የመለሱት 16.8% ናቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ጥቆማ ከመቀበል ባሻገር ሙስና እና ብልሹ ተግባር የመተንተንና ማሻሻያ እርምጃዎችን የመዉሰድ አሠራር ሥርዓት በፍርድ ቤቱ ስለመዘርጋቱ ለቀረበው ጥያቄ ከግማሽ በታች የሆኑ መላሾች በጥምረት እስማማለሁና በመጠኑ እስማማለሁ በማለት ሲመልሱ ከ50% በላይ የሆኑ መላሾች አለመስማታቸውንና ስለ አሰራሩ እውቀት እንደሌላቸው ገልጸዋል።

ሙስና እና ብልሹ ተግባራት መረጃ ጥቆማ አቅርቦትና የጠቋሚዎች የማበረታቻ አሠራርሥርዓትና ትግበራ በተመለከተ እስማማለው በማለት የመለሱት 39.88% ናቸው። 24.5% የሚሆኑ መላሾች በመጠኑ መስማማታቸውን ሲገልጹ ለጥያቄው አሉታዊ መልስ የሰጡት 13.39% ናቸው። ስለ አሰራሩ ስርአት ትግበራ አላውቅም በማለት የመለሱት 22.22% ናቸው። ሌላኛው ጥያቄ ያተኮረው የሙስና ተግባራት መረጃና ማስረጃ፤ አቅርቦትና የፍትህ ዉሳኔ አሠጣጥ ሰርዓት በተመለከተ ነው። ከዚህ አንጻር 31.32% እስማማለሁ በማለት ሲመልሱ በመጠኑ የተስማማሙት 25.28% ናቸው። 15.8% የሆኑት ደግሞ አልስማም በማለት ሲመልሱ ስለ ስርአቱ መኖር እንደማያውቁ የተናገሩት 27.58% ናቸው።የሙስና መረጃ ጥቆማ በቴክኖሎጂ አማራጮች የማከናወን ስርአት ከመዘርጋት አንጻር ለቀረበው ጥያቄ 40.22% መላሾች እስማማለው በማለት ሲመልሱ በመጠኑ መስማማታቸውን የገለጹት 29.02% ናቸው። አማራጮች ስላለመኖራቸው አልስማማም በማለት የመለሱት 11.78% ሲሆን 18.96% የሚሆኑ ስለዚህ ስርአት አለማወቃቸውን ገልጸዋል።

የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ አዋጅ ላይ ሁለት መጠይቆች ለመላሾች ቀርበል። ከላይ ካለው ሰንጠረዥ ማየት እንደሚቻለው የመጀመሪያው ያተኮረው አዋጅ አለማክበር የሚያስከትለዉ ቅጣት ግንዛቤ ደረጃ ጨመር ነው። ከዚህ አንጻር 39.08% መላሾች መስማማታቸውን ሲገልጹ በመጠኑ መስማማታቸውን የገለጹት 26.14% ናቸው። አለመስማማታቸውን የገለጹት 12.93% ሲሆኑ የግንዛቤ ደረጃ ስለመጨመሩ 21.83% አላውቅም በማለት መልሰዋል። በመጨረሻም አዋጅ ለጠቋሚዎች የሚያስገኘዉ ጥቅም ግንዛቤ እድገት በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ ከፍተና የሆኑ መላሾች (65.52%) መስማማታቸውን ሲገልጹ በመጠኑ መስማማታቸውን የገለጹት 20.79% ናቸው። ከጠቅላላው ትንሽ ቁጥር ያላቸው (3.7%) ለጥያቄው መልሳቸው አልስማማም ሲሆን 9.97% ጥየቄውን አላውቅም በማለት መልሰዋል።

### 3.4.6 በዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ዉስጥ የሚሰተዋል የሙስናስጋት ተጋላጭነት

የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጡ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ያለለበት ስለመሆኑ ዋና ዋና መለኪያወች የዳኝነት ክርክሩ አግባብ ባለው የማስረጃ ህግና የስነስርአት ህግ መሰረት መሆኑ መሰረታዊና ሥነ ሥርዓት ህጎችን ተከትሎ ከፖለቲካ ተጽኖ ፤ከሃይማኖት፤ከዘመድ አዝማድ እና ከአከባቢያዊነት የጸዳ ያላድሎ ውሳኔ መስጠት፤ የሚሰጡ ውሳኔወች ወጥና ተገማች መሆን፤ ተከራካሪ ወገኖችን በእኩል አይን ማስተናገድ ፤ ፈጣን የዳኝነት አገልግሎት መኖር ፤ የዳኝነት ስርአቱ በግልጽ ችሎት መደረጉን የሚያካትት ነው። በመሆኑም በዳኝነት አገልግሎቱ ዉስጥ የሚሰተዋሉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት በሚከተለዉ ሰንጠረዥ መሰረት ተገልፃል ።

ሰንጠረዥ 6 በዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ዉስጥ የሚሰተዋሉ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት

| ተ.ቁ | **በዳኝነት** አገልግሎት አሰጣጥ ዉስጥ **የሙስና ተጋላጭነት ስጋት በመቶኛ** (%) | እስማማለሁ | በመጠኑ እስማማለሁ፤ | አልስማማም | አላውቅም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የዳኝነት ክርክሩ አግባብ ባለው የስነስርአት ህግ መሰረት ይካሄዳል፤ | 30.79 | 30.2 | 18.18 | 20.82 |
| 2. | የዋስትና መብት ያላግባብ መከልከል ወይም መፍቀድ ። | 48.86 | 23.86 | 11.93 | 15.34 |
| 3. | ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ ማስረጃውን አግባብ ባለው የስነ ስርአት ህግ ጋር በማገናዘብና፤በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፤ | 60.22 | 25.28 | 2.55 | 11.93 |
| 4. | ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ ማስረጃውን አግባብ ባልው መሰረታዊ ህግ ጋር በማገናዘብና፤በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፤ | 51.42 | 26.28 | 6.28 | 16 |
| 5. | ዳኞች ክርክርን በሚመሩበት ጊዜ፣ ፍርድና ዉሳኔ ሲሰጡ ከሃይማኖት፤ ከዘመድ አዝማድ እና ከአከባቢያዊነት የጸዳ ነው፤ | 39.66 | 32.01 | 10.19 | 18.13 |
| 6. | ዳኞች ከሙስናና ብልሹ አሰራር በጸዳ መልኩ ፍርድ ይሰጣሉ፤ | 42.20 | 30.59 | 9.06 | 18.13 |
| 7. | ዳኞች ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት የጸዳ ብይን፤ውሳኔ እና ፍርድ ይሰጣሉ ፤ | 24.35 | 28.36 | 19.19 | 20.08 |
| 8. | ያላግባብ ተከሳሽን ጥፋተኛ ማለት ወይም ነጻ መልቀቅ ።ቅጣት መጨመር ወይም መቀነሥ ይታያል | 48.11% | 29.27 | 11.30 | 11.30 |
| 9. | የፍትህ ተደራሽነት ለማረጋገጥ ፍርድ ቤቱ በቀላሉ ለተጠቃሚው ሊደርስበት የሚችል ስርአት ዘርግቷል፤ | 52.16 | 23.91 | 10.08 | 13.83 |
| 10. | የፍትህ ተደራሽነቱ የተገልጋዩን የገንዘብ የመክፈል አቅም ባገናዘበ መልኩ ይተገበራል፤ | 44.28 | 31.42 | 7.14 | 17.14 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 11. | በፍርድ ቤት የሚሰጠዉ ብይን፣ዉሳኔና ፍርድ ተገማችነት ይታይበታል፤ | 62.79 | 21.51 | 5.23 | 10.46 |
| 12. | ዳኞች የዳኝነት ስራቸውን በግልጽ ችሎት ያከናውናሉ፤ | 55.84 | 28.20 | 6.83 | 9.11 |
| 13. | ዳኞች ለተገልጋዮች የሚሰጡት አገልግሎት ቅልጥፍና ይታይበታል፡፤ | 50.14 | 27.63 | 5.69 | 16.52 |
| 14. | ዳኞች ለተከራካሪ ወገኖች ጉዳዮችን እንዲያስረዱ ያለአድሎ በቂ ጊዜ ይሰጣሉ፤ የምስክር ቃልን ሳያቆራርጡ ይመዘግባሉ። | 44 | 28 | 7.14 | 20.84 |
| 15. | ዳኞች ለተከራካሪ ወገኖች ትክክለኛ ውሳኔ በህጉ መሰረት ያላድሎ ይሰጣሉ፤ከደላሎችና ጠበቆች ጋር ያላግባብ የሆነ ግንኙነት አይፈጥሩም። | 25.21 | 32.17 | 16.23 | 26.37 |

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚያመለክተው በፍርድ ቤቶች የዳኝነት ክርክሩ አግባብ ባለው የስነስርአት ህግ መሰረት ስለመካሄዱ የጹኅፍ መጠይቅ ከቀረበላቸዉ መልስ ሰጭወች መካከል 30.79% የሚሆኑት እስማማለሁ ፤30.2% በመጠኑ እስማማለሁ፤18.18% አልስማማም 20.82%አላውቅም በማለት መልሰዋል ። አፈፃፀም በመቶኛ ሲታይ 60.99% የዳኝነት ክርክሩ አግባብ ባለው የስነስርአት ህግ መሰረት ስለመካሄዱ የሚገልጥ ቢሆንም የዳኝነት ክርክሩ አግባብ ባለው የስነስርአት ህግ መሰረት እይመራም ያሉት 18.18% ሲሆኑ ስለጉዳዩ መልስ ለመስጠት እንቸገራለን ያሉት ደግሞ 20.82% ናቸዉ። ። በመሆኑም ከ18.18% መልስ ሰችወች የተረዳነዉ የዳኝነት ክርክሩ አግባብ ባለው የስነስርአት ህግ መሰረት አለመካሄዱን ነዉ። በደረጃ ሲታይ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ዝቅተኛ ነዉ።

የዋስትና መብት ያላግባብ መከልከል ወይም መፍቀድ ይታያል በሚለዉ መስፍርት ላይ የጹኅፍ መጠይቅ ከቀረበላቸዉ መልስ ሰጭወች መካከል 48.86% የሚሆኑት እስማማለሁ 23.86% በመጠኑ እስማማለሁ፤ 11.93% አልስማማም 15.34% አላውቅም በማለት መልሰዋል ። በመሆኑም ከ88.07% መልስ ሰጭወች እነደተረዳንዉ በዋስተና ጉዳይ ከፍተኛ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት መኖሩን የሳያል ።

ፍርድ አና ዉሳኔ የሚሰጠዉ ማስረጃውን አግባብ ከአለው የስነ ስርአት ህግ ጋር በማገናዘብና በመመርመር ነዉ መሚለዉ መስፍርት ላይ የተገኘዉ መልስ 60.22% የሚሆኑት እስማማለሁ 25.28% በመጠኑ እስማማለሁ 2.55% አልስማማም 11.93% አላውቅም የሚል ነዉ ። ከዚህ የምንረዳዉ 85.5 % የሚሆኑት ምልስ ሰጭወች የዳኞች ዉሳኔ ማስረጃውን እና የስነ ስርአት ህግን ያገናዘበ ነዉ የሚል ነዉ። ይህ ማለት የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ዝቅተኛ ነዉ።

ፍርድ አና ዉሳኔ የሚሰጠዉ ማስረጃውን አግባብ ከአለው መሰረታዊ ህግ ጋር በማገናዘብና በመመርመር በሚለዉ ነጥብ ላይ የተገኘዉ መልስ 51.42% የሚሆኑት እስማማለሁ 26.28% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 6.28% አልስማማም 16% አላውቅም የሚል ነዉ፡ 77.7 % የሚሆኑት ምልስ ሰጭወች ፍርድ አና ዉሳኔ የሚሰጠዉ ማስረጃውን አግባብ ከአለው መሰረታዊ ህግ ጋር በማገናዘብና በመመርመር መሆኑን ገልጠዋል ። በሌላ አባባል የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ 22.3 ሲሆን ስጋቱ ዝቅተኛ ደረጃ ነዉ።

ዳኞች ክርክርን በሚመሩበት ጊዜ፣ ፍርድና ዉሳኔ ሲሰጡ ከሃይማኖት፤ ከዘመድ አዝማድ እና ከአከባቢያዊነት የጸዳ ነው ለሚለዉ ጥያቄ የተገኘዉ መልስ 39.66% የሚሆኑት እስማማለሁ 32.01% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 10.19% አልስማማም 18.13% አላውቅም የሚል ነዉ፡ 71.67% የሚሆኑት ምልስ ሰጭወች በፍርድ ቤቶች የሚሰጠዉ ፍርድና ዉሳኔ ከሃይማኖት፤ ከዘመድ አዝማድ እና ከአከባቢያዊነት የጸዳ ነው የሚል ነዉ። በሌላ አባባል የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ 28.33 % ሲሆን ስጋቱ ዝቅተኛ ደረጃ ነዉ።

ዳኞች ከሙስናና ብልሹ አሰራር በጸዳ መልኩ ፍርድ ይሰጣሉ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 42.20% የሚሆኑት እስማማለሁ ፤30.59% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 9.06% አልስማማም፤ 18.13% አላውቅም የሚል ነዉ ። ይህ ማለት 72.79% ዳኞች ከሙስናና ብልሹ አሰራር በጸዳ መልኩ ፍርድ የሚሰጡ መሆኑ ነዉ ።ይህ ማለት የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ዝቅተኛ ነዉ።

ዳኞች ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት የጸዳ ብይን፤ውሳኔ እና ፍርድ ይሰጣሉ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 24.35% የሚሆኑት እስማማለሁ ፤ 28.36% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 19.19% አልስማማም፤ 20.08% አላውቅም የሚል ነዉ፡ ይህ ማለት 52.71% በዳኞች ዉሳኔ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት መኖሩ ነዉ ።ይህ ማለት የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ከፍተኛ ነዉ።

ያላግባብ ተከሳሽን ጥፋተኛ ማለት ወይም ነጻ መልቀቅ ቅጣት መጨመር ወይም መቀነሰ ይታያል ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 48.11% የሚሆኑት እስማማለሁ ፤ 29.27% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 11.30% አልስማማም፤ 11.30% አላውቅም የሚል ነዉ፡ ይህ ማለት 77.38% ዳኞች ያላግባብ ተከሳሽን ጥፋተኛ የሚሉ ወይም ነጻ የሚለቁ ፤ቅጣት መጨመር ወይም መቀነሰ ልማድ ያዳበሩ መሆኑ ነዉ።ይህ ማለት የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ከፍተኛ ነዉ።

የፍትህ ተደራሽነት ለማረጋገጥ ፍርድ ቤቱ በቀላሉ ለተጠቃሚው ሊደርስበት የሚችል ስርአት ዘርግቷል ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 52.16% የሚሆኑት እስማማለሁ ፤ 23.91% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 10.08% አልስማማም፤ 13.83% አላውቅም የሚል ነዉ፡ በፍርድ ቤቶች 76.07 የፍትህ ተደራሽነት መኖሩን ያመላክታል ።ይህ ማለት የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ዝቅተኛ ነዉ።

የፍትህ ተደራሽነቱ የተገልጋዩን የገንዘብ የመክፈል አቅም ባገናዘበ መልኩ ይተገበራል ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 44.28% የሚሆኑት እስማማለሁ፤ 31.42% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 7.14% አልስማማም፤ 13.96% አላውቅም የሚል ነዉ።75.07 % የሚሆኑተ መልስ ሰጭወች የፍትህ ተደራሽነት በገንዘብ እጦት ምክነያት የማይደነቀፍ መሆኑን ገልጸዋል ። ።ይህ ማለት የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ዝቅተኛ ነዉ።

በፍርድ ቤት የሚሰጠዉ ብይን፣ዉሳኔና ፍርድ ተገማችነት ይታይበታል ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠመልስ 62.79% የሚሆኑት እስማማለሁ፤ 21.51% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 5.23% አልስማማም፤ 10.46% አላውቅም የሚል ነዉ። 83.86 % የሚሆኑተ መልስ ሰጭወች በፍርድ ቤት የሚሰጠዉ ብይን፣ዉሳኔና ፍርድ ወጥና ተገማች ነዉ ብለዋል ። በሙኆኑም የውሳኔ ወጥነትና ተገማችነት እጦት ችግር ምክክንያት የጎላ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት አለመኖሩን የሳያል።በሌላ አባባል የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ዝቅተኛ ነዉ።

ዳኞች የዳኝነት ስራቸውን በግልጽ ችሎት ያከናውናሉ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 55.84% የሚሆኑት እስማማለሁ ፤ 28.20% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 6.83% አልስማማም፤ 9.11% አላውቅም የሚል ነዉ። አዋ ዳኞች የዳኝነት ስራቸውን በግልጽ ችሎት ያከናውናሉ በማለት 84.04% መልስ ስጥተዋል ። በመሆኑም በግልጽ ችሎት እጦት ምክንት የሚመጣ የሙስና ስጋት ዝቅተኛ ነዉ።

የዳኝነት አገልግሎቱ ቀልጣፋ ነዉ ተብሎ ለቀረበዉ ጥያቄ የተሰጠ መልስ 50.14% የሚሆኑት እስማማለሁ ፤ 27.63% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 5.69% አልስማማም፤ 16.52% አላውቅም የሚል ነዉ። 77.77% የሚሆንት መልስ ሰቸወች አገልግሎቱ ቀልጣፋ ነዉ ብለዋል. በሌላ አባባል በዳኝነት አገልግሎት መዘግየት ምክንት የሚመጣ የሙስና ስጋት ዝቅተኛ ነዉ ።

ዳኞች የምስክር ቃልን ሳያቆራርጡ ይመዘግባሉ፤ለተከራካሪ ወገኖች ጉዳዮችን እንዲያስረዱ ያለአድሎ በቂ ጊዜ ይሰጣሉ ለሚለዉ ጥያቄ የተሰጠ መልስ 44% የሚሆኑት እስማማለሁ ፤ 28% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 7.14% አልስማማም፤ 20.84% አላውቅም የሚል ሲሖን በግጽ ለቀረበዉ ጥያቄ ስምምነተሳቸዉን በአወነታ የሰጡ 72% ነዉ ።ይህ ማለት የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ዝቅተኛ ነዉ።

ዳኞች ለተከራካሪ ወገኖች ትክክለኛ ውሳኔ በህጉ መሰረት ያላድሎ ይሰጣሉ፤ከደላሎችና ጠበቆች ጋር ያላግባብ የሆነ ግንኙነት አይፈጥሩም በሚላዉ መለኪያ የተሰጠዉ መልስ 25.21% የሚሆኑት እስማማለሁ ፤32.17% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 16.23% አልስማማም፤ 26.37% አላውቅም የሚል ሲሖን በግጽ ለቀረበዉ ጥያቄ ስምምነተሳቸዉን በአወነታ የሰጡ 72% ናቸዉ። ይህ ማለት የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ዝቅተኛ ነዉ።

ሲጠቃለል የሙስና ተጋላጭነት ስጋት በተናጠል መለኪያ ሢታይ የሚያሳየዉ ዉጤት የዋስትና መብትን ያላግባብ መከልከል ወይም መፍቀድ 72 .72 % ከፍተኛ ደረጃ ፤ ተከሳሽን ጥፋተኛ ማለት ወይም ነጻ መለቀቅ ፤ቅጣት መጨመር ወይም መቀነሰ ጉዳዮች ላይ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት 77 .38% ከፍተኛ ደረጃ ነዉ። በሌሎቸ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት መለኪያ ሢታይ ዝቅተኛ ነዉ። የሁሉም መለኪያወች በአማካኝ ዉጤት 17.93 ሲሆን ደረጃዉ ዝቅተኛ ነዉ።

### 3.4.6 የፍርድ አፈጻጸም አገልግሎት ዉስጥ የሚሰተዋሉ የሙስና ስጋትተጋላጭነት

የፍርድ አፈጻጸም አገልግሎት አሰጣጡ ከሙስና ተጋላጭነት ስጋት የጸዳ ስለመሆኑ ዋና ዋና መለኪያወች ተብለዉ በዚህ የዳሰሳ ጥናት የታዩት አገልግሎቱ ቀልጣፋ መሆን ወይም ከሚፈለገዉ ጊዜ በላይ አለመዘግየት ፤ የፍርድ ባለዳው ንብረት በጨረታ ሲሸጥ በሂደቱ የባለሙያዎች እና የደላሎች ወይም የገዝወች የጥቅም ግንኙነት አለመፈጠር ናቸዉ።በመሆኑም የፍርድ አፈጻጸም አገልግሎት ዉስጥ የሚሰተዋሉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት በሚከተለዉ ሰንጠረዥ መሰረት ተገልፃል ።

ሰንጠረዥ 7 የፍርድ አፈጻጸም አገልግሎት ዉስጥ የሚሰተዋሉ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት

| ተ.ቁ | **በፍርድ አፈጻጸም እገልግሎት የሙስና ስጋት ተጋላጭነት በመቶኛ** (%) | እስማማለሁ | በመጠኑ እስማማለሁ | አልስማማም | አላውቅም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የፍርድ ባለዳውን ንብረት ለማገድና ለመሸጥ አላስፈላጊ የሆነ መዘግየት ይታያል፤ | 18.95 | 25.94 | 25.94 | 29.15 |
| 2. | የፍርድ ባለዳውን ንብረት ተሸጦ የተገኘውን ገንዝብ ለፍርድ ባለመብቱ ለመስጠት መዘግየት ይታያል፤ | 19.29 | 22.80 | 21.34 | 36.54 |
| 3. | የጨረታ ሂደት ባለሙያዎች እና ደላሎች የፍርድ ባለዳውን ንብረት በጨረታ ሲሸጡ የጥቅም ግንኙነት ሲፈጥሩ ይታያል፤ | 34.77 | 30.45 | 13.5 | 21.26 |

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚያመለክተው የፍርድ ባለዳውን ንብረት ለማገድና ለመሸጥ አላስፈላጊ የሆነ መዘግየት ይታያል ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 18.95% የሚሆኑት እስማማለሁ ፤ 25.94% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 25.94% አልስማማም፤ 29.15% አላውቅም የሚል ነዉ። 44.89 % የሚሆኑት የፍረድ የአፈጻጸም መዘግየት መኖሩን ሲገልጹ 25.94% መልስ ሰጭወች ደግሞ ፍርድ በተገቢዉ ጊዜ እየተፈጸመ መኖኑን ነዉ ። በሌላ አባባል የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ 44.89 % በመኖኑ ዝቅተኛ ነዉ።

የፍርድ ባለዳውን ንብረት ተሸጦ የተገኘውን ገንዝብ ለፍርድ ባለመብቱ ለመስጠት መዘግየት ይታያል ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 19.29% የሚሆኑት እስማማለሁ ፤ 22.80% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 21.34% አልስማማም፤ 36.54% አላውቅም የሚል ነዉ። 42.09 % የሚሆኑት የፍረድ የአፈጻጸም መዘግየት መኖሩን ገለጸዋል ይህ ማለት የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ዝቅተኛ ነዉ።

የፍርድ ባለዳው ንብረት በጨረታ ሲሸጥ በሂደቱ የባለሙያዎች እና የደላሎች ወይም የገዝወች የጥቅም ግንኙነት አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 34.77% የሚሆኑት እስማማለሁ ፤30.45% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 13.5% አልስማማም፤ 21.26% አላውቅም የሚል ነዉ። 65.22 % የሚሆኑት መልስ ሰጭወች የፍርድ ባለዳው ንብረት ሲሸጥ የደላሎች ጣልቃ ገብነት እና የጥቅም ግንኙነት መኖሩን ገለጸዋል ። ስለሆነም የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ከፍተኛ ነዉ።

ሲጠቃለል **የሙስና ተጋላጭነት ስጋት በተናጠል መለኪያ ሢታይ የሚያሳየዉ ዉጤት በፍረድ አፈጻጸም የጥቅም ግጭት መፍጠር** 65.22 % ከፍተኛ ደረጃ ፤ በሌሎቸ **የሙስና ስጋት ተጋላጭነት መለኪያ ሢታይ** ዝቅተኛ ነዉ። ነገር ገን **የሁሉም መለኪያወች በአማካኝ ዉጤት 51 %ሲሆን ደረጃዉ ከፍተ**ኛ ነዉ።

### 3.4.7 የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት

የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የስራ ክፍል ከሙስና ተጋላጭነት ስጋት የጸዳ ስለመሆኑ ዋና ዋና መለኪያወች ተብለዉ በዚህ የዳሰሳ ጥናት የታዩት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የዳኞች ሹመት፤እድገት፡ በሙያ ብቃትና በላቀ አፈፃፀም ላይ የተመሠረተ መሆኑን እንድሁም የዳኞች ነጻነትና ተጠያቂነት ማረጋጋጥ መቻሉ ናዉ።ናቸዉ።በመሆኑም በዚህ ክፍል ዉስጥ የሚሰተዋሉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት በሚከተለዉ ሰንጠረዥ መሰረት ተገልፃል ።

**ሰንጠረዥ 8** በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሙስና ሥጋት ተጋላጭነት

| ተ. ቁ | የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት በመቶኛ (%) | እስማማ | በመጠ | አልስማ | አላውቅ |
|---|---|---|---|---|---|

| | | ለሁ | ኑ እስማ ማለሁ | ማም | ም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ዳኞች ያለአድሎ፤በሀቀኝነትና የሙያ ነጻነታቸውን መሠረት በማድረግ ስራቸውን ማከናወናቸዉን ይከታተላል፤ | 36.18 | 33.61 | 8.83 | 21.36 |
| 2. | የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዳኞች የድስፐሊን ጥሰት ምክንያት ለጉባኤዉ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በአፋጣኝ ይመልሳል፤ | 37.17 | 30.54 | 10.95 | 21.32 |
| 3. | የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ዳኞች ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ሥልጣናቸዉን ከተገለገሉበት አፋጣኝ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ | 36.57 | 27.42 | 14.57 | 21.42 |
| 4. | የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የዳኞች ሹመት በሙያ ብቃትና በላቀ አፈፃፀም ላይ የተመሠረተ መሆኑን በተገቢው ሁኔታ ያረጋግጣል ፤ | 33.44 | 25.59 | 16.04 | 24.91 |
| 5. | የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የዳኞች ደረጃ ዕድገት በሙያ ብቃትና አፈፃፀም ላይ የተመሠረተ መሆኑን ስርአት ዘርግቶ ያረጋግጣል፤ | 28.94 | 26.31 | 23.97 | 20.76 |

የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ዳኞች ያለአድሎ፤በሀቀኝነትና የሙያ ነጻነታቸውን መሠረት በማድረግ ስራቸውን ማከናወናቸዉን ይከታተላል ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 36.18% የሚሆኑት እስማማለሁ ፤30.54% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 8.83% አልስማማም 21.36% አላውቅም የሚል ነዉ። 66.72 % የሚሆኑት መልስ ሰጭወች የዳኞች ሹመት፤እድገት፡ በሙያ ብቃትና በላቀ አፈፃፀም ላይ የተመሠረተ መሆኑን እንድሁም የዳኞች ነጻነትና ተጠያቂነት መኖሩን ገለጸዋል ።8.83 % ጉዳዩን በአሉታዊ መልሰዋል ይህ አሀዝ የሚያመላክተዉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ዝቅተኛ ነዉ።

የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዳኞች የድስፐሊን ጥሰት ምክንያት ለጉባኤዉ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በአፋጣኝ ይመልሳል ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 37.17% የሚሆኑት እስማማለሁ ፤ 30.54% በመጠኑ እስማማለሁ ፤ 10.95% አልስማማም 21.32% አላውቅም የሚል ነዉ። 67.71 % የሚሆኑት መልስ ሰጭወች በአወንታ ሲመልሱ 10.95% በአሉታዊ መልሰዋል ። ይህ አሀዝ የሚያመላክተዉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ዝቅተኛ ነዉ።

የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ዳኞች ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ሥልጣናቸዉን ከተገለገሉበት አፋጣኝ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 36.57% የሚሆኑት እስማማለሁ ፤ 27.42% በመጠኑ እስማማለሁ፤ 14.57% አልስማማም 21.42% አላውቅም የሚል ነዉ። 63. 99 % የሚሆኑት መልስ ሰጭወች በአወንታ ሲመልሱ 14.57% በአሉታዊ መልሰዋል ። ይህ አሀዝ የሚያመላክተዉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ዝቅተኛ ነዉ።

የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የዳኞች ሹመት በሙያ ብቃትና በላቀ አፈፃፀም ላይ የተመሠረተ መሆኑን በተገቢው ሁኔታ ያረጋግጣል ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 33.44% የሚሆኑት እስማማለሁ፤ 25.59% በመጠኑ እስማማለሁ፤ 16.04% አልስማማም 24.91% አላውቅም የሚል ነዉ። 59.03 % የሚሆኑት መልስ ሰጭወች በአወንታ መልሰዋል ፤ 16.04 % በአሉታዊ መልሰዋል ። ይህ አሀዝ የሚያመላክተዉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ከፍተኛ ነዉ።

የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የዳኞች ሹመት በሙያ ብቃትና በላቀ አፈፃፀም ላይ የተመሠረተ መሆኑን በተገቢው ሁኔታ ያረጋግጣል ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 28.94% የሚሆኑት እስማማለሁ፤ 26.31% በመጠኑ እስማማለሁ፤ 23.97% አልስማማም 20.76% አላውቅም የሚል ነዉ። 55.25 % የሚሆኑት መልስ ሰጭወች በአወንታ መልሰዋል ፤ 23.97% በአሉታዊ መልሰዋል ። ይህ አሀዝ የሚያመላክተዉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ከፍተኛ ነዉ።

ጉዳዩን ለማጠቃለል **በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አገልግሎት ዉስጥ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት በሁሉም መለኪያወች በአማካኝ ዉጤት 14.87 %ሲሆን ደረጃዉ ዝቅተ**ኛ ነዉ።

### 3.4.8 በሬጂስትረር ዳይሬክቶሬት የሙስና ተጋላጭነት ስጋት

የሬጂስትረር ዳይሬክቶሬት የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ያለለበት ስለመሆኑ ዋና ዋና መለኪያዎች በሚከተለዉ ሰንጠረዥ መሰረት ተገልፃል ።

**ሰንጠረዥ 9 የሬጂስትረር ዳይሬክቶሬት** የሙስና ሥጋት ተጋላጭነት

| ተ.ቁ | የሬጂስትረር ዳይሬክቶሬት የሙስና ስጋት ተጋላጭነት በመቶኛ (%) | እስማማለሁ | በመጠኑ እስማማለሁ | አልስማማም | አላውቅም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | መዝገቦችን መደበቅ። ማጥፋትና የመፈለጊያ ክፍያ መጠየቅ ይታያል | 43.39 | 25.28 | 17.24 | 14.08 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 2. | የሚቀርቡ መዝገቦች በቀጠሮ ቀን መረጃዉን በትክክል የተሟላ መሆኑን አረጋግጦ ያቀርባል፤ | 53.84% | 25.35% | 7.97% | 12.82% |
| 3. | ለፍርድ ቤት የቀረቡ የክስ ማመልከቻወችን በሥነስርዓት ሕጉ መሠረት የቀረቡ መሆኑን ያረጋግጣል፤ | 30.08 | 23.49 | 26.07 | 20.34 |
| 4. | የሥነስርዓት ሕጉን አሟልቶ ለፍርድ ቤት የቀረበ የክስ ማመልከቻወችን የሥነስርዓት ሕጉን አላሟላም በሚል ሰበብ ባለጉዳዮችን ክሱን አስተካክሉ በማለት አላግባብ ያጉላላል፤ | 43.82 | 24.41 | 17.64 | 14.11 |
| 5. | በቀጠሮ ላይ ያሉ መዝገቦች በግልጽ ማቀፍ በማስቀመጥ በቀላሉ በቀጠሮ ቀን በሚገኙበት ሁኔታ ያስቀምጣል፡፤ | 23.76 | 23.76 | 26.08 | 26.37 |

መዝገቦችን መደበቅ ማጥፋትና የመፈለጊያ ክፍያ መጠየቅ ይታያል ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 43.39% የሚሆኑት እስማማለሁ፤ 25.28% በመጠኑ እስማማለሁ፤ 17.24% አልስማማም 14.08% አላውቅም የሚል ነዉ፡ ፡ 68.67 % የሚሆኑት መልስ ሰጭወች መዝገቦችን መደበቅ። ማጥፋትና የመፈለጊያ ክፍያ መጠየቅ ይታያል ብለዋል ። ይህ አሀዝ የሚያመላክተዉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ከፍተኛ ነዉ።

የሚቀርቡ መዝገቦች በቀጠሮ ቀን መረጃዉን በትክክል የተሟላ መሆኑን አረጋግጦ ያቀርባል ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 53.84% የሚሆኑት እስማማለሁ፤ 25.35% በመጠኑ እስማማለሁ፤ 7.97% አልስማማም 12.82% አላውቅም የሚል ነዉ። 79.19 % የሚሆኑት መልስ ሰጭወች በአወንታ መልሰዋል፤ 7.97% በኡሉታዊ መለሰዋል ። ይህ አሀዝ የሚያመላክተዉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ዝቅተኛ ነዉ።

ለፍርድ ቤት የቀረቡ የክስ ማመልከቻወችን በሥነስርዓት ሕጉ መሠረት የቀረቡ መሆኑን ያረጋግጣል ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 30.08 የሚሆኑት እስማማለሁ፤ 23.49% በመጠኑ እስማማለሁ፤ 26.07% አልስማማም 20.34% አላውቅም የሚል ነዉ። 54.29 % የሚሆኑት መልስ ሰጭወች በአወንታ መልሰዋል፤ 26.07% በኡሉታ መለሰዋል ። ይህ አሀዝ የሚያመላክተዉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ከፍተኛ ነዉ።

የሥነስርዓት ሕጉን አሟልቶ ለፍርድ ቤት የቀረበ የክስ ማመልከቻወችን የሥነስርዓት ሕጉን አላሟላም በሚል ሰበብ ባለጉዳዮችን ክሱን አስተካክሉ በማለት አላግባብ ያጉላላል ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 43.82% የሚሆኑት እስማማለሁ፤ 24.41% በመጠኑ እስማማለሁ፤ 17.64% አልስማማም 14.11% አላውቅም የሚል ነዉ። 68.23

% የሚሆኑት መልስ ሰጭወች የሥራ ክፍሉ ያለበቂ ምክንያት ባለጉዳዮችን ያጉላላል ብለዋል ። ይህ አሀዝ የሚያመላክተዉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ከፍተኛ ነዉ።

በቀጠሮ ላይ ያሉ መዝገቦች በግልጽ ማቀፍ በማስቀመጥ በቀላሉ በቀጠሮ ቀን በሚገኝበት ሁኔታ ያስቀምጣል ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 23.76% የሚሆኑት እስማማለሁ፤ 23.76% በመጠኑ እስማማለሁ፤26.08% አልስማማም 26.37% አላውቅም የሚል ነዉ። 47.52 % የሚሆኑት መልስ ሰጭወች በአወንታ መልሰዋል፤ 26.08% በኡለታ መለሰዋል ። ይህ አሀዝ የሚያመላክተዉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቱ ዝቅተኛ ነዉ።

ሲጠቃለል የሙስና ተጋላጭነት ስጋት በተናጠል መለኪያ ሢታይ የሚያሳየዉ ዉጤት መዝገቦችን መደበቅ ማጥፋትና የመፈለጊያ ክፍያ መጠየቅ 68.67 % ፤ያለምክንያት ባለጉዳዮችን ማጉላላት 68.23 % ከፍተኛ ደረጃ ፤ በሌሎቸ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት መለኪያ ሢታይ ዝቅተኛ ነዉ። የሁሉም መለኪያወች በአማካኝ ዉጤት 39.40 %ሲሆን ደረጃዉ ዝቅተኛ ነዉ።

## ክፍል አራት

## የሙስና ስጋት ምዘናና ግምገማ

የዚህ ክፍል ዋና አላማ የሙስና ስጋት ምዘናና ግምገማ ማድረግ ሲሆን። ይሄንንም ለማድረግ በፍርድ ቤቶች የሚፈጸሙ የሙስና ደረጃ ስጋቶች ከፍተኛ፣ *መካከለኛና ዝቅተኛ* **በመባል** *ተመድበዋል* ::**ከዚ*ያም የሙስና ስጋቶቹ የሚያሳድሩት ተጽእኖ ተዳሷል* ::**

### 4.1 በፍርድ ቤቶች ዉስጥ የሚፈጸሙ የሙስና ስጋቶች/ወንጀሎች በደረጃ

**በዚህ ክፍል** *የሙስና ስጋት የመከሰት እድልን ያረጋገጠነዉ.* **በተጨባጭ** *ሙስና* **በፍርድ** *በቶች መከሰቱን* **በማሳየት** *ነዉ*፡ የዚህ ክፍል ዋና **አላማም** **በፍርድ** ቤቶች ውስጥ የሚከሰቱ የሙስና አይነቶችና ያላቸውን ደረጃ መለየት ነው።

**ሰንጠረዥ 4.1** በፍርድ ቤቶች **ዉስጥ** የሚፈጸሙ የሙስና **ስጋቶች /ወንጀሎች** ደረጃ ሲታይ

| ተ. ቁ | **በፍርድ ቤት አሰራር የሚፈጸሙ የሙስና ስጋቶች ደረጃ** በመቶኛ (%) | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | አላውቅም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ስልጣኑንና ሀላፊነቱን ያላአግባብ በመገልገል ለራሱ ጥቅም የሚያገኝ ወይም | 9.14 | 18.85 | 36.28 | 35.71 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለሌላ ሰዉ ጥቅም የሚያስገኝ ወይም ሌላ ሰዉ የጎዳ ፤ | | | | |
| 2. | ጉቦ መቀበል፤ | 6.03 | 16.37 | 32.18 | 45.4 |
| 3. | ሀላፊነቱን በመጠቀም የማይገባ ጥቅም መቀበል፤ | 7.03 | 14.07 | 35.77 | 43.69 |
| 4. | የ ፍ/ ቤቱን ጥቅም በሚጎዳ መንገድ መስራት፤ | 8.4 | 18.91 | 36.33 | 36.33 |
| 5. | በፍ/ ቤቱ እቃ ያለአግባብ ማዘዝ ፤ | 5.78 | 11.56 | 27.45 | 55.20 |
| 6. | የማይገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በብርበራ ወይም በመያዝ ፤ በዉርስ ስርአት በሀራጅ ሽያጭ ፤በፍርዱ አፈጸም የተያዘዉን ንብረት ፤ ጥሬ ገንዘቦችን ፤እቃወችን ፤ ሰነዶችን መዉስድ ወይም ማስወስድ፤ | 5.45 | 18.1 | 35.34 | 41.09 |
| 7. | በስልጣን አላግባበብ መገልገል፤ | 7.24 | 20 | 38.55 | 34.2 |
| 8. | ያለግባብ ጉዳይን ማጓትት፤ | 3.17 | 11.81 | 32.27 | 52.73 |
| 9. | ዋጋ ያልዉን ነገር ያለከፍያ ከክፍያዉ በታች መቀበል፤ | 4.85 | 9.42 | 27.71 | 58 |
| 10. | ምንጩ ያልታወቀ ገንዘብ ወይም ንብረት መሰብሰብ፤ | 7.16 | 16.33 | 32.09 | 44.41 |
| 11. | የስራ ሚስጥርን መግለጽ፤ | 6 | 11.42 | 31.14 | 51.42 |
| 12. | ለራሱ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም ለማስገኘት ወይም ሌላ ሰዉ ለመጉዳት በማሰብ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘገጀት ፤ ወደሀሰት መቀየር ወይም በሀሰተኛ ሰነዶች መገለገል፤ | 4.87 | 12.6 | 29.51 | 53 |
| 13. | ለራሱ ጥቅም ለማገኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም ለማስገኘት ወይም ሌላ ሰዉ ለመጉዳት በማሰብ ሰነዶችን ማጥፋት ወይም መቅደድ፤ | 3.15 | 5.15 | 26.64 | 64.13 |
| 14. | ከስልጣኑ ከታገደ ወይም ከተሻረ ፤ከስራዉ ከተዛወረ በኋላ በማስመሰል በሰራዉ መገለገል፤ | 4.87 | 8.3 | 26.07 | 60.74 |
| 15. | ለራሱ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም ለማስገኘት በፍ/ቤቱ በአደራ የተሰጠዉ ንብረት ወይም ጥሬ ገንዘብ መዉሰደ ወይም ማስወሰድ፤ | 4.84 | 9.11 | 30.19 | 55.84 |
| 16. | ለራሱ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም ለማስገኘት ተበዳዩን | 4.88 | 7.18 | 24.42 | 63.5 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በማታለል የተበዳዩንን ሰዉ ጥቅም መጉዳት፤ | | | | |
| 17. | የሙስና ወንጀል ፈጽሞ ያገኘዉን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ፤ | 3.79 | | 21.51 | 74.68 |

በስልጣናን ያላአግባብ መገልገል አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 9.14% ከፍተኛ 18.85% መካከለኛ፤ 36.28% ዝቅተኛ፤ 35.71% አላውቅም የሚል ነዉ ።።፡ድጠቅላለ የሙስና ሰጋት ድምር ዉጤት 64.27% ፤ አማካኝ ዉጤት 21.54 % ነዉ። ይህ የሙስና ወንጀል በደረጃ ሲታይ 1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ ደረጃ መካከለኛ 3ኛ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ።። በመሆኑም በፍርደ ቤቶች አሰራር ዉስጥ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆንም ለሙስና ተጋልጠዋል ።

ጉቦ መቀበል አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 6.03% ከፍተኛ 16.37% % መካከለኛ፤ 32.18% ዝቅተኛ፤ 45.4% አላውቅም የሚል መልስ የተሰጠ ሲሆን የሙስና ሰጋት ድምር ዉጤት ጠቅላለ ድምር ዉጤት 54.58 % ፤ አማካኝ ዉጤት 18.19 % ነዉ ። በደረጃ ሲታይ 1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ ደረጃ መካከለኛ 3ኛ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ። በመሆኑም በፍርደ ቤቶች አሰራር ዉስጥ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆን ጉቦ አለ ።

ሀላፊነቱን በመጠቀም የማይገባ ጥቅም መቀበል አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 7.03% ከፍተኛ፤ 14.07% መካከለኛ፤ 35.77% ዝቅተኛ፤ 43.69% አላውቅም የሚል ነዉ ።ድጠቅላለ የሙስና ሰጋት ድምር ዉጤት 58. 87 % ፤ አማካኝ ዉጤት 19.62 % ነዉ ።ይህ የሙስና ወንጀል በደረጃ ሲታይ 1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ ደረጃ መካከለኛ 3ኛ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ።። በመሆኑም በፍርደ ቤቶች አሰራር ዉስጥ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆንም ለሙስና ተጋልጠዋል ።

የፍ/ ቤቱን ጥቅም መጉዳት አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 8.4% ከፍተኛ፤18.91% መካከለኛ፤ 36.33% ዝቅተኛ፤ 36.33% አላውቅም የሚል ነዉ ።ድጠቅላለ የሙስና ሰጋት ድምር ዉጤት 64.64 % ፤ አማካኝ ዉጤት 21.54 % ነዉ። ይህ የሙስና ወንጀል በደረጃ ሲታይ 1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ ደረጃ መካከለኛ 3ኛ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ። በመሆኑም በፍርደ ቤቶች አሰራር ዉስጥ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆንም ለሙስና ተጋልጠዋል ።

በፍ/ ቤቱ እቃ ያለአግባብ ማዘዝ አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 5.78% ከፍተኛ፤ 11.56% መካከለኛ፤ 27.45% ዝቅተኛ፤55.20% አላውቅም የሚል ነዉ ።ድጠቅላለ የሙስና ሰጋት ድምር 44.79% ፤ አማካኝ ዉጤት 14.93% ነዉ ።ይህ የሙስና ወንጀል በደረጃ ሲታይ 1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ ደረጃ መካከለኛ 3ኛ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ። በመሆኑም በፍርደ ቤቶች አሰራር ዉስጥ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆንም ለሙስና ተጋልጠዋል ።

በስራ ተግባረር የሚፈጸም የመዉሰድና የመሰወር ወንጀል  አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ   5.45% ከፍተኛ፤  18.1%  መካከለኛ፤ 35.34%  ዝቅተኛ፤ 41.09% አላውቅም የሚል ነዉ ።ድጠቅላለ  የሙስና ሰጋት ድምር ዉቴት  58.89 % ፤ አማካኝ ዉጤት 19.63 %  ነዉ።  ይህ የሙስና ወንጀል በደረጃ ሲታይ  1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ  ደረጃ  መካከለኛ  3ኛ  ደረጃ  ከፍተኛ  ነዉ  ።  በመሆኑም  በፍርደ  ቤቶች   አሰራር  ዉስጥ በዝቅተኛ  ደረጃም ቢሆንም ለሙስና ተጋልጠዋል ።

በስልጣን አላግባባብ መገልገል አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 7.24%   ከፍተኛ፤ 20%   መካከለኛ፤ 38.55% ዝቅተኛ፤34.2%  አላውቅም የሚል ነዉ ።ድጠቅላለ የሙስና ሰጋት ድምር ዉቴት  65.79 % ነዉ፤ አማካኝ ዉጤት 21. .93 % ነዉ። ይህ የሙስና ወንጀል በደረጃ ሲታይ  1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ ደረጃ መካከለኛ 3ኛ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ። በመሆኑም በፍርደ ቤቶች  አሰራር ዉስጥ በዝቅተኛ  ደረጃም ቢሆንም ለሙስና ተጋልጠዋል ።

ያለግባብ ጉዳይን ማዳትት አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 3.17% ከፍተኛ፤ 11.81%  መካከለኛ፤32.27% ዝቅተኛ፤ 52.73% አላውቅም የሚል ነዉ ።ድጠቅላለ የሙስና ሰጋት ድምር ዉቴት  73.98% ፤ አማካኝ ዉጤት 24.66  % ነዉ።  ይህ የሙስና ወንጀል በደረጃ ሲታይ  1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ ደረጃ መካከለኛ 3ኛ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ። በመሆኑም በፍርደ ቤቶች  አሰራር ዉስጥ በዝቅተኛ  ደረጃም ቢሆንም ለሙስና ተጋልጠዋል  ።

ዋጋ ያልዉን  ነገር ያለከፍያ  ወይም ከክፍያዉ በታች  መቀበል አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 4.85% ከፍተኛ፤9.42%  መካከለኛ፤ 27.71% ዝቅተኛ፤ 58% አላውቅም የሚል ነዉ ።ድጠቅላለ  የሙስና ሰጋት ድምር ዉቴት   41.98%  ነዉ፤ አማካኝ ዉጤት 13.99 % ነዉ  ። ይህ የሙስና ወንጀል በደረጃ ሲታይ  1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ ደረጃ መካከለኛ 3ኛ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ።  በመሆኑም በፍርደ ቤቶች  አሰራር ዉስጥ በዝቅተኛ  ደረጃ ቢሆንም ለሙስና ተጋልጠዋል ።

ምንጩ  ያልታወቀ  ገንዘብ   መሰብሰብ  አለ  ለሚለዉ  መጠይቅ  የተሰጠ  መልስ  7.16%  ከፍተኛ  16.33% መካከለኛ፤ 32.09%ዝቅተኛ፤44.41% አላውቅም የሚል ነዉ ። ድጠቅላለ  የሙስና ሰጋት ድምር ዉቴት   55.58 % ነዉ ፤ አማካኝ ዉጤት 18.53 % ነዉ ።  ይህ የሙስና ወንጀል በደረጃ ሲታይ  1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ ደረጃ መካከለኛ 3ኛ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ። በመሆኑም በፍርደ ቤቶች  አሰራር ዉስጥ በዝቅተኛ  ደረጃም ቢሆንም ለሙስና ተጋልጠዋል ።

የስራ ሚስጥርን መግለጽ አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ  6%  ከፍተኛ 11.42%  መካከለኛ፤  31.14% ዝቅተኛ፤51.42% አላውቅም የሚል ነዉ ። ።ድጠቅላለ  የሙስና ሰጋት ድምር ዉቴት  48.56 %  ነዉ፤ አማካኝ

ዉጤት 16.19 % ነዉ። ይህ የሙስና ወንጀል በደረጃ ሲታይ 1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ ደረጃ መካከለኛ 3ኛ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ። በመሆኑም በፍርደ ቤቶች አሰራር ዉስጥ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆንም ለሙስና ተጋልጠዋል ።

ሰነዶችን አስመስሎ ማዘገጀት ፤ ወደሀሰት መቀየር ወይም በሀሰተኛ ሰነዶች መገለገል አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 4.87% ከፍተኛ12.6% መካከለኛ፤ 29.51% ዝቅተኛ፤53% አላዉቅም የሚል ነዉ ። ።ድጠቅላለ የሙስና ሰጋት ድምር ዉቴት 46.98 ፤ አማካኝ ዉጤት 15.66 % ነዉ። ይህ የሙስና ወንጀል በደረጃ ሲታይ 1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ ደረጃ መካከለኛ 3ኛ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ። በመሆኑም በፍርደ ቤቶች አሰራር ዉስጥ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆንም ለሙስና ተጋልጠዋል ።

ሰነዶችን ማጥፋት ወይም መቅደድ አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 3.15% ከፍተኛ 5.15% መካከለኛ፤ 26.64% ዝቅተኛ፤ 64.13% አላዉቅም የሚል ነዉ ።።።ድጠቅላለ የሙስና ሰጋት ድምር ዉቴት 39.94% ፤ አማካኝ ዉጤት 13.31 % ነዉ። ይህ የሙስና ወንጀል በደረጃ ሲታይ 1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ ደረጃ መካከለኛ 3ኛ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ።በመሆኑም በፍርደ ቤቶች አሰራር ዉስጥ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆንም ለሙስና ተጋልጠዋል ።

በሌለዉ ስልጣን መጠቀም አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 4.87% ከፍተኛ 8.3% መካከለኛ፤ 26.07%ዝቅተኛ፤ 60.74% አላዉቅም የሚል ነዉ ። ።ድጠቅላለ የሙስና ሰጋት ድምር ዉቴት 39.24 % ፤ አማካኝ ዉጤት 13.08 % ነዉ። ይህ የሙስና ወንጀል በደረጃ ሲታይ 1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ ደረጃ መካከለኛ 3ኛ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ። በመሆኑም በፍርደ ቤቶች አሰራር ዉስጥ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆንም ለሙስና ተጋልጠዋል ።

ከባድ ዕምነት ማጉደል አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 4.84% ከፍተኛ 9.11% መካከለኛ፤ 30.19% ዝቅተኛ፤ 55.84% አላዉቅም የሚል ነዉ ።ድጠቅላለ የሙስና ሰጋት ድምር ዉቴት 44.14% ፤አማካኝ ዉጤት 14.71 %ነዉ። ይህ የሙስና ወንጀል በደረጃ ሲታይ 1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ ደረጃ መካከለኛ 3ኛ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ። በመሆኑም በፍርደ ቤቶች አሰራር ዉስጥ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆንም ለሙስና ተጋልጠዋል ።

ከባድ አታላይነት አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 4.88% ከፍተኛ 7.18% መካከለኛ፤ 24.42% ዝቅተኛ፤ 63.5% አላዉቅም የሚል ነዉ ። ። ድጠቅላለ የሙስና ሰጋት ድምር ዉቴት 36.48 % አማካኝ ዉጤት 12.16 % ነዉ። ይህ የሙስና ወንጀል በደረጃ ሲታይ 1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ ደረጃ መካከለኛ 3ኛ ደረጃ ከፍተኛ ነዉ ። በመሆኑም በፍርደ ቤቶች አሰራር ዉስጥ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆንም ለሙስና ተጋልጠዋል ።

የሙስና ወንጀል ፈጽሞ ያገኘዉን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ አለ ለሚለዉ መጠይቅ የተሰጠ መልስ 3.79% ከፍተኛ በመካከለኛ ደረጃ የተሰጠ መልስ የለም ፤ 21.51% ዝቅተኛ፤ 74.68% የሚሆኑተ ደግሞ መልስ ለመስጠት ተቸግረናል ወይም አላውቅም የሚል ነዉ ።ድጠቅላለ የሙስና ሰጋት ድምር ዉቴት 25.3% ነዉ።አማካኝ ዉጤት 8.43 %

ይህ የሙስና ወንጀል በደረጃ ሲታይ 1ኛ ደረጃ ዝቅተኛ ፤2ኛ ደረጃ ደግሞ ከፍተኛ ነዉ ። በመሆኑም በፍርደ ቤቶች አሰራር ዉስጥ በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆንም ለሙስና ተጋልጠዋል ።

## 4.2 ችግሮቹ ሊያመጡ የሚችሉት ተጽእኖ

በዳኝነት ስርአቱ ላይ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት እያደረሰ ያለዉ አሉታዊ ተጽኖ ተገልጋዮች ፍርድ ቤት ላይ እምነት ማጣት ነዉ። በመሆኑም ባለጉዳዮች በህግ መሰረት ፍትህ የሚፈልጉ ሳይሆን በአቃራጭ በፖለቲካ ጣልቃ ገብነት የሚፈልጉተን መፍትሄ ለማግኘት ጥረት ሢያደረጉ ተስተዉሏል ።

በፍርድ ቤት የሙስና ተዳለጭነት ስጋት መኖር እያደረሰ ያለዉ አሉታዊ ተጽኖ ፍትህ እንዲዛባ ማድረጉ ፤የፍትህ አመኔታ መጥፋት ፤ የፍትህ ተገማችነት መጥፋት ፤ ተስፋ መቁረጥ፤ ዜጋዉ በሀገሩ ላይ ባይተዋር እንዲሆን እና መንግስት ላይ አመኔታ እንዳይኖረው በማድረግ ትልቅ ችግር ፈጥሯል።

ቀጠሮ ያለአግባብ መዓተት እያደረሰ ያለዉ አሉታዊ ተጽኖ ባለጉዳዮች በየቀጠሮዉ ቀን ፍረድ ቤት እዲመላለሱ ማድረጉ ወይም የፍትህ መዓተት ማሰከተሉ ፤ ባለጉዳቶች ያላግባብ ወጪ እየአወጡ ነዉ ፤ ስልቹነት አምጥቷል፤ የፍረድ ቤቶችን አመኔታ አሳጥቷል የሚል መልስ ከብዙ መላሽ ተሰጥቷል።

በፍረድ አፈጻጸም በኩል የሚታዩ ችግሮች ያደርሰዉ ተጽእኖ የፍረድ ባለመብትን ጥቅም ብቻ ሣይሆን የፍረድ የባለእዳዉን መብት እያሳጣ እነደሚገኝ ከተሰጠዉ መልስ ተገንዝበናል።

በሬጂስትራር በኩል የሚስተዋሉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ተጽኖዉ ባለጉዳዮቹና ፍትህ ፈላጊው ማህበረሰብ በፍ/ቤቱና በሬጂስትራር ስራው ላይ የነበረዉ እምነት በጣም እንዲሸረሽ አድርጓል በሚል የአገኘነዉ መልስ ብዙ ነዉ።

በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በኩል የሚስተዋሉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቶች ተጽኖ ለሙያዉ ብቁ የሆኑ ባለሙያወች በርቀት በሚያገኙተ መረጃ ተስፋ በመቁረጥ ወደ ፍርድ ቤቶች እነዳይመጡ ትልቅ ተጽኖ ፈጥሯል በሚል የአገኘነዉ መልስ ብዙ ነዉ።

በእኛ እምነት የፍትህ መዘግየት እና /ወይም የፍትህ እጦት በጊዜው ካለተቀጨ የመንግሰትና የግል ስራ በተገቢዉ ጊዜ እና በአግባቡ እንዳይከናውን ያደርጋል በመሆኑም ለሀገር ኢኮኖሚ ትልቅ ጉዳት ያሰከተላል። በተጨማሪም በአገሪቱ የፖለቲካ እና ማህበራዊ ቀውስ ሊያስከትል እነደሚችል እንገምታለን ።

## ክፍል አምስት

**ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳብ**

**5.1 ማጠቃለያ**

በዚህ የዳሰሳ ጥናት ከጹሁፍ መጠይቅ ፤ ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እዲሁም ጥናቱ አግባብነት ያላአቸዉን አዋጆችን፤ ደንቦችን መመሪያወችን እና አግባብነት ያላአቸዉን ልዩ ልዩ የሰነድ መረጃዎችን መርምሯል :: ሆኖም የአገኘነዉ የፖሊሲና የህግና ክፍተት የለም ። በዚህ የዳሰሳ ጥናት የገኘነዉ የአሰራር ወይም የአፈጻጸም ክፍተት ነዉ ።

በዚህ የዳሰሳ ጥናት የገኘነዉ የመጀመሪያዉ ግኝት የበላይ አመራሩ በፍረድ ቤት እሰራር የሙስና ስጋት ሢታይ ለመቅረፍ የቁርጠኝነት ችግር አለበት ፣ የክትትል እና የቁጥጥር ስራዉ የላላ መሆኑ ነዉ።

በዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ዉስጥ የተሰተዋሉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ ቢሆንም የዳኝነት ክርክሩ እና ፍረድ አሰጣጡ ከህግ አግባብ ዉጭ መሆኑ፤ዳኞች ክርክርን በሚመሩበት ጊዜ፣ ፍርድና ዉሳኔ ሲሰጡ ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ከሃይማኖት፤ ከዘመድ አዝማድ እና ከአከባቢያዊነት አሰራር ያልጸዳ መሆኑ፤የፍርድ ተገማችነት ችግር መኖር ፤የፍትህ መዘግየት መኖር ፤ በዝግ ችሎት ማስቻል ተስተዉሏል። የሙስና ተጋላጭነት ስጋት በተናጠል መለኪያ ሢታይ የሚያሳየዉ ዉጤትየዋስትና መብትን ያላግባብ መከልከል ወይም መፍቀድ 72 .72 ከፍተኛ ደረጃ ፤ ተከሳሽን ጥፋተኛ ማለት ወይም ነጻ መለቀቅ ፤ቅጣት መጨመር ወይም መቀነሰ ጉዳዮች ላይ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት 77.38 ከፍተኛ ደረጃ ነዉ። በሌሎች የሙስና ስጋት ተጋላጭነት መለኪያ ሢታይ ዝቅተኛ ነዉ። የሁሉም መለኪያወች በአማካኝ ዉጤት 17.93 ሲሆን ደረጃዉ ዝቅተኛ ነዉ። ይህ ማለት ግን በዳኝነት አገልግሎት በዋናዋና የሙስና ምንጬች ላይ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ከፍተኛ ነዉ።

በፍርድ አፈጻጸም አገልግሎት አሰጣጥ ዉስጥ የተሰተዋሉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት አገልግሎቱን ማዘገየት መካከለኛ ደረጃ ላይ ያለ ፤ የጨረታ ሂደቱን በአሻጥር መፈጸም ፤ የፍርድ ባለዳውን ንብረት በጨረታ ሲሸጥ የጥቅም ግንኙነት መፍተር ይታያል ። የሙስና ስጋት ተጋላጭነትበተናጠል መለኪያ ሢታይ የሚያሳ የዉ ዉጤት በፍረድ አፈጻጸም የጥቅም ግጭት መፍጠር 65.22 % ከፍተኛ ደረጃ ፤ በሌሎች የሙስና ስጋት ተጋላጭነት መለኪያ ሢታይ ዝቅተኛ ነዉ። ነገር ገን የሁሉም መለኪያወች በአማካኝ ዉጤት 51 %ሲሆን ደረጃዉ ከፍተኛ ነዉ።

በዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ ቢሆንም የዳኞች ምልመላ ፤መረጣ ፤ሹመትና እድገት ሜሪት ቤዝድ አለመሆን ፤ ከፖለቲቻ ጣልቃ ገብነት ነጻ ለሞኖን እና የዳኞች ነጻነተንና ተጠያቂነትን ስርአት ማስፍን አልቻለም በሚል ተጠቅሷል።በዚህ የስራ ክፍል የሙስና ስጋት ተጋላጭነት በሁሉም መለኪያወች በአማካኝ ዉጤት 14.87 ሲሆን ደረጃዉ ዝቅተኛ ነዉ።

በሬጂስትረር ወይም በመዝገብ ቤት የሰራ ክፍል ዉስጥ የተሰተዋሉ የሙስና ተጋላጭነት ስጋቶች መዝገቦችን መደበቅ ፤ ማጥፋትና የመፈለጊያ ክፍያ መጠየቅ ይታያል ደረጃዉም ከፈተኛ ነዉ :: መዝገቦች ሲቀርቡ አቃቂር በማውጣት የተሟላ መዝገብ አይደለም በሚል ሰበብ መመለስ እና ጉቦ ተቀብሎ መዝገቡን መክፈት ፤ በቀጠሮ ላይ ያሉ መዝገቦችን በግልጽ ማቀፍ አለማስቀመጥና በቀላሉ ለመለየት መቸገር ። በዚህ አገልግሎት ክፍል የሙስና ስጋት ተጋላጭነት በተናጠል መለኪያ ሢታይ የሚያሳየዉ ዉጤት መዝገቦችን መደበቅ ማጥፋትና የመፈለጊያ ክፍያ መጠየቅ 68.67 % ፤ያለምክንያት ባለጉዳዮችን ማጉላላት 68.23 % ከፍተኛ ደረጃ ፤ በሌሎቸ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት መለኪያ ሢታይ ዝቅተኛ ነዉ። የሁሉም መለኪያወች በአማካኝ ዉጤት 39.40 %ሲሆን ደረጃዉ ዝቅተኛ ነዉ።

በሰዉ ሀብት አስተዳደር በኩል የሚታዩ የሙስና ስጋቶች አልፎ አልፎ የሰራተኛ ቅጥር፤ዝውር፤ የደረጃ እድገት በዝምድና በጓደኝነት መስራት እና የቁጥጥር ስርአት መላላት ነዉ ።በግዥ አስተዳደር በኩል ለሙስና የሚያጋልጡ አሰራሮች አልፎ አልፎ ከግዥ ስርአት ዉጭ የሚገዙ እቃዎች ከደረጃ በታች የመሆን ችግር ታይቷል።

ፍርድን የሚያዛቡ አሰራሮች በአጭሩ ሲታዩ ህግን ተከትሎ ያለመስራት፤የፖለቲካ ጣልቃገብነት፤ ጎጠኝነት፤ ወገንተኝነት ወይም ማዳላት ፤ በዘመድ አዝማድ መስራት፤በጥቅማ ጥቅም ወይም በመደለያ መስራት ያልተገባ ጥቅም በማግኘት ባለጉዳን ማጉላላት ይታያል ፡፡ይሄን ተከተሎም በፍርደ ቤቶች አሰራር ዉስጥ እየተከሰቱ ያሉ ይሙስና ወንጀሎች አማካኝ ዉጤት፡-ስልጣኑንናሀላፊነቱን ያላአግባብ በመገልገል 21.43 %፤ጉቦ መቀበለል 18.19%፤ ሀላፊነቱን በመጠቀም የማይገባ ጥቅም መቀበል 19.62% ፤ የፍ/ ቤቱን ጥቅም መጉዳት 21.54% ፤ በፍ/ ቤቱ እቃ ያለአግባብ ማዘዝ 14.93%፤ በስራ ተግባረር የሚፈጸም የመዉሰድና የመሰወር ወንጀል 19.63% ፤ በስልጣን አላግባባብ መገልገል 21.93%፤ ጉዳይን ማጓት 24.66%፤ ንብረትን ያለከፍያ ወይም ከክፍያዉ በታች መቀበል 13.99 %፤ ምንጩ ያልታወቀ ገንዘብ መሰብሰብ 18.53 %፤ የስራ ሚስጥር መማባክን 16.19% ፤ሰነዶችን ወደሀሰት መቀየር እና መገለገል 15.66% ፤ ሰነዶችን ማጥፋት ወይም መቅደድ13.31%፤በሌለዉ ስልጣን መጠቀም 13.08%፤ ከባድዕምነት ማጉደል 14.71% ፤ ከባድ አታላይነት 12.16%፤የሙሰና ዉጤት ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ 25.3% ናቸዉ ፡፡

የሙስና ስጋት ምክንያቶች /corruption factors/ ደግሞ ፡- ባለሙያወች ለተመደቡበት ሀላፊነት ብቃት ማነስ ፤ አቅምን ለማጎልበት ዘውትር ያለማንበብ ችግር መኖር ፡ ዳኞች ለተመደቡበት ሀላፊነት ብቃት ማነስ ወይም የእውቀት ማነስ ለዚህ ምክንያት ደግሞ የዳኞች ምልመላና ፤መረጣና ሹመት በብሄር ተዋጽ ፤ በፖለቲካ ዉሳኔ እንጂ በጥናት ላይ ያልተመሰረተ ፤ ግልጥነት ዕና ተጠያቂነት በሰፈነበት ስርአት ያለመሆኑ ነዉ ፡፡

ሌላዉ ለችግሮቹ ምክንያት የሆነዉ በአቋራጭ ለመክበር የመፈለግ ዝንባሌ ይዞ ወደ ፍርድ ቤት መምጣት አንዱ ችግር ፤ የስነ ምግባር ችግር መኖር ፤ በስራዉ ላይ የባለቤትነት ስሜት አለመኖር እና የተጣለብን ሀለፊነትን በቅጡ ተግባራዊ ካለማድረግ የመጨ መሆኑ፤ የቁጥጥር ስርአት እና ተጠያቂነት መላላት ሌላዉ ምክንያት ነዉ ፡፡ በዳኝነት ስርአቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያደረሰ ያለዉ ሌላዎ ችግር የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነዉ ፡፡

በተጨማሪም በቂ ደሞዝ እና ጥቅማጥቅም ያለማግኘት፣ ምቹ የስራ ሁኔታን ያለመፍጠር ለምሳሌ በቂ እና ምቹ የትራንስፖርት ሰርቪስ አገልግሎት ያለማግኘት፣ መኖሪያ ቤት ያለመመቻቸት ችግር ነዉ፡፡

በፍርድ ቤት የሙስና ተጋለጭነት ስጋት አሉታዊ ተጽኖዉ ፍትህ እንዲዛባ ማድረጉ ፤የፍትህ አመኔታ መጥፋት ፤ የፍትህ ተገማችነት መጥፋት ፤ ተስፋ መቁረጥ፤ ዜጋዉ በሀገሩ ላይ ባይተዋር እንዲሆን እና

መንግስት ላይ አመኔታ እንዳይኖረው በማድረግ ትልቅ ችግር ነዉ።በመሆኑም ቶሎ መፍተሄ ካለተሰጠዉ ይህ ትልቅ አገራዊ ችግር ለኢኮኖሚ ዉድቀት፤ ፤ለፖለቲካ እና ማህበራዊ አለመረጋጋት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል መገመት ከባድ አይሆንም።

## 4.2 የመፍትሄ ሃሳብ

1. ጠንካራ አመራርና አሰራርን መዘርጋት በተለይም የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አባላት አመራረጥ በፖለቲታ ተሳትፎ የተመሰረተ መሆኑ ቀርቶ ግልጽና አሳታፊ በሆነ መመሪያ መፈጸም አለበት ። እንዲኑም ግልጽነት ያለዉ የቅሬታ አቀራረብ ስርአት መዘርጋትና ተግባረዊ ማግረግ አለበት ።
2. የዘመነ አሰራ ስርአትን በፍ/ቤቶች መዘርጋት፤በቴክኖሎጂ የታገዘ የሬጂስትረር ስርአትን መከተል፤ የፋይል ምዝገባው ኦንሊን እንዲሆን ማድረግ፤ዘመናዊ የፋይል አደረጃጀት ስተርዓት መከተል ፤ በዋና ዋና የፍርድ በቤት አገልግሎቶች ዉስጥ ሲሲቲቪ ካሜራ መጠቀም ፤ በችሎት የተሰጠን የምስክር ቃልን አለመመዝገብ ወይም መቆራረጥ እና ፍርድ ማዛባት ለመቀነስ ይረዳ ዘንድ ሁሉንም ጉዳዮች በመቀረጸ ድምጽ መቅዳት ተገቢ ነዉ እንላለን።
3. ስራዎችን ማዘመን ይቻል ዘንድ በአሁኑ ሰአት በፌደራል በከፍተኛ ፍ/ቤት የተጀመረዉ በስክሪን ላይ ቀጠሮ ማሳየት በሁሉም ፍረድ ቤቶች ተግባራዊ ቢደረግ ተገቢ ነዉ እንላለን።
4. የዳኞች ምልመላ ፤መረጣ ፤ሹመትና እድገት ሜሪት ቤዝድ ወይም በዉድደር ፤ በጥናት ላይ የተመሰረተ ፤ ግልጽነት ዕና ተጠያቂነት በሰፈነበት ስርአት መሆን አለበት ።
5. የአቅም ዉስንነት ላለባቸዉ ዳኖች የሙያ ስልጠና መስጠት በተለይም የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ላይ ለዳኞች ስልጠና መስጠት እንዲሁም የስነምግባር ዉስንነትን ለማሻሻል የሚረዱ ስልጠናዎችን መሰጠት አለበት::
6. የዳኞች ነጻነተንና ተጠያቂነትን ስርአት ማስፍን ፤ክትትል፤ ድጋፍ ማጠናከና የሙያ ግምገማ ማድረግ እና ተጠያቂ የሚሆኑትን ዳኞች ተጠያቂ ማድረግ ለዚህም ይረዳ ዘንድ የፍርድ ምርመራ እነዲኖር ማድረግ ወይም መዝገቦችን ኦዲት የማድረግ ስራዎችን አጠናክሮ መቀጠል፣ከፍተኛ አፈጻጸም ለሚያስመዘግቡ ዳኞች እውቅና እና ማበረታቻ መስጠት ተገቢ ነዉ እንላለን።
7. ለስራዉ ብቁ የሆኑ ሰራተኞች ባግባቡ መመደብ፤ የእውቀት እና የክሎት ክፍተት ላለባቸዉ ሰራተኞች አጫጭር ስልጠናዎች መስጠት፤ የትምህርና የረጅም ጊዜ ስልጠና እድሎችን ለሰራተኛው ማመቻቸት፤የክትትልና ቁጥጥር ግምገማ ስርአትን ማጠናከር፤የተጠያቂነቱን ስርአት

መዘርጋት እንድሁም በየደረጃዉ ለሚሰሩ ሰራተኞች የስነምግባር ግንባታዎችን በየጊዜው መስጠት ፤ የማበረታቻ ስረዓት መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ ጥሩ እንላለን።

8. አፋጣኝ ዉሳኔ መስጠት ልቻል ዘነድ ፍርድ ቤቶች በቂ እና ብቁ የሰው ሃብት መመደብ አለባቸው በተጨማሪም ረዳት ዳኞች በፍ/ቤቶች ቢኖሩ ስራ ይቃለላል ቀልጣፋ አገልግት እንዲኖር ያደርጋል እንላለን።
9. በፍርድ ቤቶች የፍርድ አስፈጻሚ ኣካል እራሱን ችሎ ቢቋቋም ወይም ማስፈጸሚያ የሚሆን በጀት በመንግሰት ቢመደብ ጥሩ እንላለን። ።
10. የሚሰበሰበዉ የዳኝነት ገንዘብ በሳምንት አንድ ጊዜ መሆኑ ቀርቶ በመመሪያው መሰረት በየቀኑ ወደ ባንክ መግባት አለት::
11. በቂ ደሞዝ እና ጥቅማጥቅም ማግኘት፣ ምቹ የስራ ሁኔታን መፍጠር ለምሳሌ በቂ እና ምቹ የትራንስፖርት ሰርቪስ አገልግሎት ያለማግኘት፣ መኖሪያ ቤት ያለመመቻቸት።የጥቅማ ጥቅም ማስተካከያ እርምጃዎችን በፍጥነት መውሰድና ማስተካከል ተገቢ ነዉ እንላለን።
12. የፍትህ ስርአቱ ተገማች የሚሆንበትን የአሰራር ስርአት መዘርጋትና ማሳደግ ተገቢ ነዉ :: በተለይም ግልጽኝነት እና ተጠያቂነትን ለማስፋን ችሎቶት ለህዝብ ግልጽ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ህብረተሰቡን ስለፍርድ ቤት አሰራር ማወያየትና አስተያየቶችን መሰብሰብ ፤የባለጉዳዮችን እርካታ በዳሰሳ ጥናት መለየት፤ ህብረተሰቡ በፍርድ ቤቱ እንዲያምን የግንዘቤ ማስጨበጫ አውታሮችን መጠቀም በተለይም ሬዲዮ፤ቴሌቪዥን ወዘተ መጠቀም ተገቢ ነዉ እንላለን።

## ማጣቀሻ ጽሁፎች

African Union (AU) (2003). African Union Convention on Prevention and Combatting Corruption. Adopted at the Second Ordinary Session of the Assembly of the Union.

Federal Ethics and Anti-Corruption Commission (FEACC). 2012.*Ethiopia- Second Corruption Perception Survey*. Final Report by Kilimanjaro International Corporation.

Gedion Gemora. 2019. *National Study on Prevention of Corrupt Practices in the Mining Sector*. Addis Ababa, Ethiopia: Bencia Printing Press.

Institute of African Economic Studies (IAES). 2008 “Transparency Ethiopia Corruption Diagnostic Baseline Survey.” Final report. Transparency Ethiopia, Addis Ababa.

Transparency International (TI) (2022). Corruption Perception Index 2021. Transparency International.

______________________(2007). *Global Corruption Report 2007: Corruption in Judicial Systems*. Cambridge: Cambridge University Press.

United Nations Office on Drugs and Crime (2020). State of Integrity: A Guide on Conducting Corruption Risk Assessments in Public Organizations.

United Nations. (2003). United Nations Convention Against Corruption. Adopted at the UN General Assembly. Resolution 5814, 31 October 2003.

World Bank (2014). World Bank Global Integrity Report. The World Bank: Washington D.C.

_________________.(2012). *Diagnosing Corruption in Ethiopia: Perceptions, Realities, and the Way Forward for Key Sectors.* Washington D.C.: The World Bank.

የኢትዮጵያ እንባ ጠባቂ (Ethiopian Ombudsman Authority, 2021). የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በዋናው መስሪያ ቤትና በቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ውስጥ የአሰራር ሥርአት ጥናት ለማድረግ የተደረገ የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት። ህዳር 2014.

የኢትዮጵያ ፌደራል ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (1995) ህገመንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1995 *የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ.*

የኢትዮጵያ ፌደራል ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (2013). የፌዴራል የስነ-ምግባርና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 1236/2013. *የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ.*

የኢትዮጵያ ፌደራል ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (1993). የፌዴራል የስነ-ምግባርና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 235/1993. *የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ.*

የኢትዮጵያ ፌደራል ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (2007). የተሻሻለው የጸረ-ሙስና ልዩ-የስነ ስርአትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 882/2007. *የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ.*

የኢትዮጵያ ፌደራል ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (2007). የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007. *የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ.*

የተሻሻለዉ የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች አዋጅ 43 / 1994 ደቡበ ነጋሪት ጋዜጣ

የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 42/1994 ደቡበ ነጋሪት ጋዜጣ

የፌደራል የፍ/ ቤት የዳኛች ስነምግባር ድንብ

የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አሰራር ለማጠናከር የወጣ መመሪያ ቁጥር 2006 አ.ም

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ ቤት የስራ ክፍል ሀላፊወችና የሰራተኞች ስነምግባር መተዳደሪያ ድንብ 2013 ኢ.ም

የኦሮሚ ክልላዌ መንግሰት ፍርድ ቤቶች የዳኛች ስነምግባር ድንብ ቁጥር 2011ኢ.ም

አንደገና የሻሻለዉ የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ዳኞችና በጉባኤ የሚተተዳደሩ ባለሙያወች የተፈላጊ ችሎታ የምልመላና መረጣ ኮሚቴ ማቐቐሚያ ፤የአሰራር ስርአትና የስራ መዘርዘር መመሪየ ቁጥር10/2011 ኢ.ም.

የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች የዳኛች የስነምግባርና ዲሲሊን ድንብ ቁጥር 6/1995

የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤት ሙስና መከላከል ስትራቴጄ ሰነድ 2011 ኢ.ም.

## አባሪዎች

### አባሪ አንድ፡ የድርጊት መርሀ ግብር

### የሙስና ስጋት ጥናት የሚካሄድባቸዉ የፌዴራልና የክልል ፍርድ ቤቶች ዝርዝር፣ የተወሰዱ ናሙናዎች እና የቡድን ክፍፍል

| ተ.ቁ | ቡድኖች ዝርዝር | የቡድን አባላት ብዛት | የተመደቡበት ተቋማት | ሥራ ፍልሎች እና የመጠየቆች ብዛት | | | የቃለመ ጠይቅ ብዛት | ሥራ ዉ የሚወስደዉ ጊዜ | ሱፐርቫይዘር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ስራ ክፍሎ | ናሙና ሰዉ በቁጥር | ድምር | | | |
| 1 | ቡድን 1 | 3 ባላሙያ እና 1 ሹፌር | 1. ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት | 12 | 2 | 24 | 2 | 10 ቀን | 1 |
| | | | 2. ፌዴራል ክፍተኛ ፍርድ ቤት(ልደታ)ና ዳ/አ/ጉ/ጽ/ቤት | 10 | 2 | 20 | 2 | | |
| | | | 3. ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት | 10 | 2 | 20 | 2 | | |
| | | | 4. የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት | 3 | 2 | 6 | 2 | | |
| | ቡድን ሁለት | | 1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት(አዲስ አበባ) | 11 | 2 | 22 | 2 | 12 ቀን | 1 |
| | | | 1. ጅማ ዞን ከፍተኛና ፍ/ቤት (ጅማ) | 10 | 2 | 20 | 2 | | |
| | | | 2. ጅማ ዞን ሰቃ ጨቆርሳ ወረዳ ፍርድ ቤት (ጅማ) | 10 | 2 | 20 | 2 | | |
| **የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች** | | | | | | | | | |
| 2 | ቡድን ሶስት | 3 ባላሙያ | 1. ምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት | 10 | 2 | 20 | 2 | 12 ቀን | 1 |
| | | | 2. ም/አርሲ ዞን ሻሸመነ ወረዳ ፍ/ቤት | 10 | 2 | 20 | 2 | | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | እና 1 ሹፌር | 3. ም/ሸ/ዞን ከፍተኛ ደረጃ ፍርድ ቤት | 10 | 2 | 20 | 2 | | |
| | | | 4. ም/ሸ/ዞን ሞጆ ወረዳ ፍርድ ቤት | 10 | 2 | 20 | 2 | | |
| | | | 3. ጅማ ወረዳ ፍርድ ቤት (ጅማ) | 10 | 2 | 20 | 2 | | |
| **የደቡብ ክልል ፍርድ ቤቶች** | | | | | | | | | |
| 4 | ቡድን 4 | 4 | 1. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት(ሀዋሳ) | 11 | 2 | 22 | 2 | 12 ቀን | 1 |
| | | | 2. የጉራጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት(ወልቂጤ) | 10 | 2 | 20 | 2 | | |
| | | | 3. የጉራጌ ዞን አሸጊ ወረዳ ፍ/ቤት | 10 | 2 | 20 | 2 | | |
| 5 | | 4 | 1. የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት (ሶዶ) | 10 | 2 | 20 | 2 | 12 ቀን | 1 |
| | | | 2. የወላይታ ሶዶ ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት | 10 | 2 | 20 | 2 | | |
| | | | 3. የጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት (አርባ ምንጭ) | 10 | 2 | 20 | 2 | | |
| | | | 4. የጋሞ ዞን ካምባ ወረዳ ፍርድ ቤት(ካምባ) | 10 | 2 | 20 | 2 | | |

**አባሪ ሁለት፡ የጥናት መረጃ ለሚሰበሰቡ ቡድኖች የሚያስፈልግ ግምታዊ ወጪዎች**

| ተ.ቁ | የወጪዎች ዓይነት | ብዛት | የቆይታ ጊዜ | መለኪያ | ያንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ | የበጀት ምንጭ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| *1* | ***የጽህፈት መሳሪያዎች*** | | | | | **97,750.00** | |
| | ወረቀት | 5 | | ደስታ | 300.00 | 1500.00 | |
| | እስክርብቶ(ቡና) | 1 | | ፓኬት | 750.00 | 750.00 | |
| | እርሳስ | 1 | | ፓኬት | 500 | 500 | |
| | ታብሌት ኮምፕዩተር | 3 | | በቁጥር | 30,000.00 | 90,000.00 | |
| | የመረጃ ማሰባሰቢያ የቆዳ ቦርሳ | 5 | | በቁጥር | 1000.00 | 5,000.00 | |
| *2* | ***ዉሎ አበል*** | | | | | **175,500.00** | |
| | የመረጃ ሰብሳቢዎች መስክ ጉዞ/ጅማ | 15 | 10 | ቀን | 3*650*10 | 19,500.00 | |
| | የመረጃ ሰብሳቢዎች መስክ ጉዞ ክልል የሚሄዱ | 24 | 15 | ቀን | 16*650*15 | 156,000.00 | |
| 3 | **በቢሮ ዉስጥ ለሚሰሩ የመስተንግዶ ወጪ** | | | | | **47,250.00** | |
| | የጥናት ቡድን አስተባባሪዎች እና አማካሪዎች | 15 | 30 | ቀን | 15*105*30 | 47,250.00 | |
| 4 | የተሽከርካሪ ነዳጅና ቅባት | | | | | **100,000.00** | |
| | የተሽከርካሪዎች ነዳጅ እና ተያያዥ ጉዳዮች | 5 | | | 5*20000 | 100,000.00 | |
| *5* | ***የሥልጠና ወጪ*** | | | | | **200,000** | |
| | ለአጥኚ ባለሙያዎች | 3 | በዙር | | | 150,000 | |
| | ለመረጃ አጠናቃሪዎች ስልጠና እና የሻይ ቡና፣ ዉሃና ቆሎ | 3 | በዙር | | | 50,000 | |
| *6* | ***የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ማረጋጥ*** | | | | | **200,000.00** | |
| | ተቋማት አመራሮችና የባለድረሻ አካላት መድረክዝግጅት | | | | | 200,000 | |
| | ድምር | | | | | **820,500.00** | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | **መጠባቂያ በጀት 5%** | | | | **820,500*5%** | **41,025.00** | |
| | **ጠቅላላ ድምር** | | | | | **861,525.00** | |

**አባሪ ሶስት፡ የሙስና ስጋት ጥናት የሚካሄድባቸዉ የፌደራል ፍርድ ቤቶች እና በክልሎች ያሉ ፍርድ ቤቶች ዝርዝር እና መረጃ የሚሰበስቡ ቡድኖች**

**ሀ/ የፌደራል ያሉ ፍርድ ቤቶች**

**1. ቡድን አንድ (ሹፌርን ጨምሮ 4) ለ15 ቀናት**

- ✓ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
- ✓ የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት
- ✓ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት (ልደታ )
- ✓ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት (ልደታ )
- ✓ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት (አዲስ አበባ)

***ለ/የክልል ፍርድ ቤቶች***

***በኦሮሚያ ክልል ከ3ቱ ዞኖች የተመረጡ ፍርድ ቤቶች***

**2. ቡድን ሁለት (ሹፌርን ጨምሮ 4) ለ10 ቀናት**

- ✓ ጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት (ጅማ)
- ✓ ጅማ ዞን ሰቃ ጨቆርሳ ወረዳ ፍርድ ቤት (ጅማ)

**3. ቡድን ሶስት (ሹፌርን ጨምሮ 4) ለ15 ቀናት**

5. የምስራቀ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት (አዳማ)
6. የምስራቅ ሸዋ ዞን ሞጆ ወረዳ ፍርድ ቤት(ሞጆ)
7. የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት (ሻሸመኔ)እና
8. የምዕራብ አርሲ ዞን የሻሸመኔ ወረዳ ፍርድ ቤት(ሻሸመኔ)

***በደቡብ ክልል ከ3ቱ ክልሎች የተመረጡ ፍርድ ቤቶች***

**4. ቡድን አራት (ሹፌርን ጨምሮ 4)**

9. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት(ሀዋሳ)
10. የጉራጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት (ወልቂጤ)
11. የጉራጌ ዞን አሸጊ  ወረዳ ፍርድ ቤት(ወልቂጤ)

**5. ቡድን አምስት (ሹፌርን ጨምሮ 4)**

12. የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት (ወላይታ ሶዶ)
13. የወላይታ ሶዶ ዙሪያ ወረዳ ደረጃ ፍርድ ቤት(ወላይታ ሶዶ)
14. የጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት (አርባ ምንጭ)
15. የጋሞ ዞን  ካምባ ወረዳ ፍርድ ቤት (ካምባ)

**በፍርድ ቤቶች መረጃ የሚሰበሰብባቸዉ ሥራ ክፍሎች**

- ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
  1. የወንጀል የስራ ክፍል
  2. የፍትብሔር ሥራ ክፍል
  3. የሥራ ክርክር ሥራ ክፍል
  4. የሰበር ችሎት ሥራ ክፍል
  5. የሪጅስትራሪ ሥራ ክፍል
  6. የሼሪዓ ፍርድ ሥራ ክፍል
  7. የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት
  8. የሴቶችና ህፃናት ፕሮጀክት ሥራ ክፍል
  9. የሰዉ ሀብት አስተዳደር ሥራ ክፍል
  10. የግዥ አስተዳደር ሥራ ክፍል
  11. የፋይናንስ አገልግሎት ሥራ ክፍል
  12. የንብረት አስተዳደር ሥራ ክፍል
- **የፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣**
  1. የወንጀል የስራ ክፍል
  2. የፍትብሔር ሥራ ክፍል
  3. የሥራ ክርክር ሥራ ክፍል
  4. የሪጅስትራሪ ሥራ ክፍል
  5. የሼሪዓ ፍርድ ሥራ ክፍል
  6. የህፃናትና ችሎት ሥራ ክፍል
  7. የሰዉ ሀብት አስተዳደር ሥራ ክፍል
  8. የግዥ አስተዳደር ሥራ ክፍል
  9. የፋይናንስ አገልግሎት ሥራ ክፍል
  10. የንብረት አስተዳደር ሥራ ክፍል
- **የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች**

1. የወንጀል የስራ ክፍል
2. የፍትብሔር ሥራ ክፍል
3. የሥራ ክርክር ሥራ ክፍል

4. የሰበር ችሎት ሥራ ክፍል
5. የሪጅስትራሪ ሥራ ክፍል
6. የሼሪዓ ፍርድ ሥራ ክፍል
7. የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት
8. የሰዉ ሀብት አስተዳደር ሥራ ክፍል
9. የግዥ አስተዳደር ሥራ ክፍል
10. የፋይናንስ አገልግሎት ሥራ ክፍል
11. የንብረት አስተዳደር ሥራ ክፍል

- **የክልል ከፍተኛ፣የመጀመሪያ/የወረዳ ፍርድ ቤቶች**
    1. የወንጀል የስራ ክፍል
    2. የፍትብሔር ሥራ ክፍል
    3. የሥራ ክርክር ሥራ ክፍል
    4. የሪጅስትራሪ ሥራ ክፍል
    5. የሼሪዓ ፍርድ ሥራ ክፍል
    6. የህፃናትና ችሎት ሥራ ክፍል
    7. የሰዉ ሀብት አስተዳደር ሥራ ክፍል
    8. የግዥ አስተዳደር ሥራ ክፍል
    9. የፋይናንስ አገልግሎት ሥራ ክፍል
    10. የንብረት አስተዳደር ሥራ ክፍል

**አባሪ አራት፡ የፍርድ ቤት ቼክ ሊስት**

**የተቋሙ አጠቃላይ መረጃ**

| የተቋሙ አጠቃላይ መረጃ | | | |
|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | ክፍል አንድ፡- የተቋሙ መሰረታዊ መረጃ | ኮድ | |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የተቋሙ ስያሜ፡- | A01 | | | | | | |
| 2 | የተቋሙ ቋሚ አድራሻ፡- | A02 | ድረገጽ (a) | | ተቋማዊ ኢሜይል (b) | | | |
| | | | | | | | | |
| 3 | የተቋሙ የበላይ ኃላፊ አድራሻ፡- | A03 | ስልክ ቁጥር (a) | | ተቋማዊ ኢሜይል (b) | | | |
| | | | | | | | | |
| 4 | የተቋሙ አጠቃላይ የቋሚ ሰራተኛ ብዛት በቁጥር | A04 | ድምር (a) | | ሴት(b) | | ወንድ(c) | |
| 5 | የተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች ብዛት በቁጥር | A05 | ድምር (a) | | ሴት(b) | | ወንድ(c) | |
| 6 | የተቋሙ መካከለኛ አመራሮች ብዛት በቁጥር | A06 | ድምር (a) | | ሴት(b) | | ወንድ(c) | |
| 7 | የተቋሙ መጀመሪያ ደረጃ አመራሮች ብዛት (ቡድን መሪ) | A07 | ድምር (a) | | ሴት(b) | | ወንድ(c) | |
| 8 | የተቋሙ የ2013 በጀት ዓመት አጠቃላይ በጀት መጠን | A08 | በብር፡- | | | | | |
| 9 | የተቋሙ የ2013 በጀት ዓመት በጀት መጠን | A09 | በብር፡- | | | | | |
| 10 | የተቋሙ የ2013 በጀት ዓመት ከድጋፍ/ ፕሮጀክት በጀት መጠን | A10 | በብር፡- | | | | | |
| 11 | የተቋሙ የድጋፍ/ ፕሮጀክት በጀት መጠን እና የአጋሮች ስም፡- | A11 | ዝርዝር ስምና የባንክ ሂሳብ ቁጥር ይጠየቅ፤ | | | | | |
| 12 | አገር ዉስጥ የድጋፍ/ ፕሮጀክት በጀት መጠን | A12 | የተከፈተ ባንክ ሂሳብ ብዛት | | | | | |
| 13 | ዓለምአቀፍ የድጋፍ/ ፕሮጀክት በጀት መጠን | A13 | የተከፈተ ባንክ ሂሳብ ብዛት | | | | | |
| 14 | ሀብት ምዝገባና ማሳወቅ ያከናወነ የበላይ አመራር ብዛት | A14 | | | | | | |
| 15 | ሀብት ምዝገባና ማሳወቅ ያከናወነ የመካከለኛ አመራር ብዛት | A15 | | | | | | |
| 16. | ሀብት ምዝገባና ማሳወቅ ያከናወነ መጀመሪያ ደረጃ አመራር ብዛት | A16 | | | | | | |
| 17. | የተቋሙ የ2013 በጀት ዓመት አጠቃላይ የግዥ በጀት መጠን | A17 | | | | | | |
| 18. | በተቋሙ የሚከናወኑ የ2013 በጀት ዓመት ፕሮጀክቶች ብዛት | A18 | | | | | | |
| 19. | የሥነምግባር ሥልጠና በማጠናቀቅ ምዘናና ብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ያገኙ አመራሮችና ሰራተኞች ብዛት | A19 | | | | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | በባለፉት አምስት አመታት፤ | | |
| 20. | ባለፉት አምስት ዓመታት የሙስና ጥቆማ ብዛት | A20 | |
| 21. | ባለፉት አምስት ዓመታት የሙስና ጥቆማ ብክነት/ምላሽ ያላገኙ/ ብዛት | A21 | |
| 22. | ባለፉት አምስት አመታት ከስር ፍ/ቤት ወደ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በይግባኝ የሄዱ የጉዳዮች ብዛት | A22 | |
| 23. | ባለፉት አምስት አመታት በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በይግባኝ የተሻረ የጉዳዮች ብዛት | A23 | |
| 24 | ባለፉት አምስት አመታ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በይግባኝ የጸና የጉዳዮች ብዛት | A24 | |

የተቋሙ አጠቃላይ መረጃ የሞላው ስም፡ ------------------------------

ፊርማ፡ ------------------------------

**አባሪ አምስት፡ የጽሁፍ መጠይቅ**

የፍ/ቤቱ ስያሜ _______________________________________________

የፍ/ቤቱ አድራሻ _______________________________________________

የስራ ክፍሉ ወይም ችሎት ስያሜ _____________________________

የመጠይቁ ቁጥር__________________________

የጠየቀው ሰው ስም________________________

የተጠያቂው ጾታ_____________

የት/ት ደረጃ________________

የስራ ልምድ________________

የስራ ሃላፊነት________________

የመጠይቁ ቦታ________________

መጠይቁ የተሞላበት ቀን____________________

የጀመረበት ሰዓትና_____________________ የማገባደጃ ሰአት _________________________

የሥራ ክፍሉ ወይም ችሎት አድራሻ _______________________________

የመጠይቁ አቅራቢ ፊርማ--------------

**ዉድ የዚህ መጠይቅ መላሾች፡-**

እንደምን አደሩ/ዋሉ/አመሹ! እኔ ዶ/ር/አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት ----------------------- እባላለሁ።

ይህ መጠይቅ በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን በፍርድ ቤቶች ላይ የሙስና ሥጋት ጥናት ለማድረግ ጠቃሚ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ይህ ጥናት በዋናነት የሚያተኩረው በፍትህ ዘርፍ ባሉ ፍርድ ቤቶች ላይ ዋና ዋና የስራ ሂደትና(የፌደራል ፍርድ ቤቶች፤ ሼሪአ ፍርድ ቤቶች፤ በደቡብና በኦሮሚያ ክልሎች ያሉ

ጠቅላይ እና የከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና የወረዳ ፍርድቤቶች በተጨማሪም ለፍርድ ቤት ሬጅስትራር፤ ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤና ለፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ያጠቃልላል፡፡) እና አጋዥ የስራ ክፍሎች ሲሆን የዚህ ጥናት ዓላማዎች፡- በፍርድ ቤቶች የሚስተዋሉ የሙስና ስጋት ዝርዝር መለየት፤ በፍርድ ቤቶች የሙስና ሥጋት ምክንያቶችን መለየትና መተንተን፤የሙስና ስጋት መገምገምና ደረጃ መስጠት እና በፍርድ ቤቶች በተሰጠዉ የደረጃ ቅደም ተከተል መሰረት የሙስና መከላከል ምክረሀሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡

ይህ የሙስና ስጋት ጥናት የሚካሄደው ሙሰኞችን የሚፈልግ ሳይሆን የተቋሙን የሙስና ስጋት ለመቀነስ ታስቦ የሚሰራ፤ ውጤታማ የመከላከያ መሳሪያ መሆኑንና ለተቋሙ ታማኝነት፣ በመልካም ስምና የዜጎች እምነት እንዲጨምር ነው፡፡

ስለሆነም መጠይቁን በቅንነት በመሙላት እንድትተባበሩ እና ጠቃሚ አስተያየት እንድትሰጡን እንጠይቃለን። የእናንተ ምላሽ የሙስና ስጋት ለመለየት እና ለማወቅ ትልቅ እገዛ ያደርጋል።

እባክዎ ጥቂት ደቂቃዎችን ወስደው ጥያቄዎችን መመለስ ይችላሉ? በዚህ መጠይቅ ውስጥ የእርስዎ ስም እና ማንነት የማይጠቀስ፣ የሚሰጡት ምላሽም ለታለመለት አላማ ብቻ የሚውል እና ሚስጥራዊነቱም የሚጠበቅ መሆኑን እየገለጸኩ ጊዜዎንና ጉልበቶን ሰውተው ለሚያደርጉልኝ ትብብር ከወዲሁ አመሰግናለሁ፡፡

| | **ክፍል 1 ሙስናን ለመከላከል የሚረዱ አሰራሮችና መመሪያዎች ስጋትበሚከተሉት የጽሁፍ መጠይቆች አዎ፤ በሂደት ላይ፤ የለም ፤አላውቅም በሚል ይሙሉ፡፡** | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 4 አዎ፣ 3 በሂደት ላይ፣ 2 የለም ፣ 1 አላውቅም | | 4 አዎ | 3 በሂደት ላይ | 2 የለም | 1 አላውቅም |
| 7. | የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 ወይም ክልሉ ባወጣው አዋጅ መሰረት ተቋቁሟል | B01 | | | | |
| 8. | የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ሥራ በፍርድ ቤቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ዉስጥ ተካትቷል፤ | B02 | | | | |
| 9. | በፍርድ ቤቱ ለአመራሮችና ስራተኞች በስነምግባር የታነጸ፤ ጥራትና ተገቢነት ያለው የስነ-ምግባር አቅምና ብቃት ማጎልበት የሚያስችል ስልጠና የሚሰጥበት መደበኛ ስርአት ተዘርግቷል | B03 | | | | |
| 10. | ፍርድ ቤቱ የአመራርና የሰራተኞች የሥነምግባር መመሪያ አለዉ፤ | B04 | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 11. | ፍርድ ቤቱ የዕቅድና የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሪፖርት ለሕዝብና ለመንግሥት ባለድርሻ አካላት እዉነተኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ ያቀርባል፤ | B05 | | | | |
| 12. | ፍርድ ቤቱ ስለአገልግሎቱ ጥራት፤ ተገቢነት፤ ተደራሽነተና ፍትሐዊነት ግንዛቤ ለማሳደግ የደንበኛ እና የባለድርሻ አካላት እርካታ በየወቅቱ ይለካል፤ | B06 | | | | |
| 13. | ፍርድ ቤቱ ተገልጋዮችን በቅንነትና በታማኝነት፤ ከሙስናና ብልሹ ሰራር በጸዳ መልኩ የሚያስተናግዱ እና በመልካም ስነ ምግባር አረአያ የሆኑ አመራሮችና ሰራተኞች እውቅና የሚሰጥበት ስርአት ተዘርግቷል | B07 | | | | |
| 14. | በፍርድ ቤቱ የአስተዳደር መዋቅር ሰራተኞች የመንግሥት የሥራ ሰዓት በአግባቡ እንዲጠቀሙ የቁጥጥር አሠራር ሥርዓት ተዘርግቷል፤ | B08 | | | | |
| 15. | ፍርድ ቤቱ ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበልና ተገቢዉን የእርምት እርምጃ ለመዉሰድ የተዘረጋ አሠራር ሥርዓት አለው፤ | B09 | | | | |
| 16. | በፍርድ ቤቱ ከሙስናና ብልሹ አሰራር ጋር ግንኙነት ያላቸው የውስጥ እና የዉጭ ኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ የሚወሰድበት እና የባከኑ ሃብቶች የሚመለሱበት አሠራር ሥርዓት ዘርግቷል፤ | B10 | | | | |
| | **ክፍል 2 የመረጃ ግልጽነት ደረጃ ስጋትበሚከተሉት የጽሁፍ መጠይቆች እስማማለው፤ በመጠኑ እስማማለው፤ አልስማማም እና አላውቅም በሚል ይሙሉ።** | | | | | |
| | 4 እስማማለሁ፣ 3 በመጠኑ እስማማለሁ፤ 2 አልስማማም፡ 1 አላውቅም | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 17. | ፍርድ ቤቱ ፖሊሲና ስትራቴጂክ ዕቅድ የመረጃ ግልጽነት አለው | C01 | | | | |
| 18. | ፍርድ ቤቱ አዋጅ፤ ደንብ፤ መመሪያና ስታንዳርድ የመረጃ ግልጽነት አለው | C02 | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 19. | የመንግሥት ዓመታዊ መደበኛና ካፒታል በጀት አጠቃቀም የመረጃ ግልጽነት አለው | C03 | | | | |
| 20. | በፍርድ ቤቱ የፕሮጀክቶች አይነትና የበጀት የመረጃ ግልጽነት አላቸው | C04 | | | | |
| 21. | ወቅታዊና ዓመታዊ የፍርድ ቤቱ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት አለው | C06 | | | | |
| 22. | ወቅታዊና ዓመታዊ የፍርድ ቤቱ የበጀት አፈጻጸም ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት አለው | C07 | | | | |
| 23. | ወቅታዊና ዓመታዊ የፍርድ ቤቱ ግዥ አፈጻጸም ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት አለው | C08 | | | | |
| 24. | ዓመታዊ የፍርድ ቤቱ ን ንብረት ቆጠራ የሚያሳይ ሪፖርት የመረጃ ግልጽነት አለው | C09 | | | | |
| 25. | ፍርድ ቤቱ የሚያስወግደዉ ንብረት የመረጃ ግልጽነት አለው | C10 | | | | |
| 20. | በገለልተኛ አካል የተመዘነ ዓመታዊ የደንበኛ እርካታ ሪፖርት ግልጽነት አለው | C11 | | | | |

ክፍል ሶስት፡-ተቋሙ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አቅምና ብቃት ስለማሳደግና ማጎልበት፤**ስጋትበሚከተሉት የጽሁፍ መጠይቆች እስማማለው፤ በመጠኑ እስማማለው፤ አልስማማም እና አላውቅም በሚል ይሙሉ፡፡**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 4 እስማማለሁ፣ 3 በመጠኑ እስማማለሁ፤ 2 አልስማማም፡ 1 አላውቅም | | 4 | 2 | 1 |
| 21. | የየፍርድ ቤቱ የበላይ አመራር የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ምክረ-ሐሳቦችን መነሻበማድረግ ተቋማዊ አሠራር ሥርዓት ግልጽነትን አሻሽሏል | D01 | | | |
| 22. | የፍርድ ቤቱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ተልዕኮ ለማስተባበር አቅምና ብቃት አለዉ፤ | D02 | | | |
| 23. | የፍርድ ቤቱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊ የመምራት አቅምና ብቃት አለዉ/አላት፤ | D03 | | | |
| 24. | የፍርድ ቤቱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ባለሙያዎች ተልዕኳቸዉን ለማከናወን በቂ አቅምናብቃት አላቸዉ፤ | D04 | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 25. | የፍርድ ቤቱ ሥነምግባር መከታተያ ክፍል ከተቋሙ ሥራ ክፍሎች ጋር ትስስር፤ ትብብርና ቅንጅት በመፍጠር የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ተልዕኮ ይወጣል፤ | D05 | | | | |
| 26. | የፍርድ ቤቱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል በተቋሙ ሙስና እንዲቀንስና ሥነምግባር ጉድለትእንዲታረም አሠራር ሥርዓት፤አቅምና ብቃት አጎልብቷል፤ | D06 | | | | |
| ክፍል አራት፡- የተቋሙ የሙስና ተጋላጭነት ሥጋት የመቀነስና የግልጽነት ዕድገት ደረጃ **በሚከተሉት የጽሁፍ መጠይቆች እስማማለው፤ በመጠኑ እስማማለው፤ አልስማማም እና አላውቅም በሚል ይሙሉ፡፡** | | | | | | |
| | 4 እስማማለሁ፣ 3 በመጠኑ እስማማለሁ፤ 2 አልስማማም፡ 1 አላውቅም | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 27. | የአመራርና የሰራተኞችን የሥነምግባር ጉድለት ለመቆጣጠርና ለማረም የተቋሙአመራር በቂ ግንዛቤና ተነሳሽነት አለዉ፤ | E01 | | | | |
| 28. | ፍርድ ቤቱ ፖሊሲ፤ ስትራቴጂ፤ ዕቅዶችንና ፕሮጀክቶችን ከሰነድነት ወደተግባር የመቀየርአቅምና ብቃት አለዉ ፤ | E02 | | | | |
| 29. | የተቋሙ ሁሉም አመራሮችና ሰራተኞች በተልዕኮና ርዕይ የጋራ ግንዛቤ አላቸዉ | E03 | | | | |
| 30. | በተቋሙ ያሉ ባለሙያዎች የሥራና የሙያ ሥነምግባር ያከብራሉ፤ | E04 | | | | |
| 31. | በተቋሙ ፆታዊ ትንኮሳዎችና ብልሹ ሥነምግባር ተጋላጭነት ለመከላከል የተዘረጋእጽየጎለበተ የአሠራር ሥርዓት አለ፤ | E05 | | | | |
| 32. | የበላይ አመራር የሥነምግባር ልህቀት ምጣኔና ሙስናን የመከላከል አቅምና ብቃት አለው፤ | E06 | | | | |
| 33. | የተቋሙ የመካከለኛ አመራሮች የሥነምግባር ልህቀትና ሙስና የመከላከል አቅምና ብቃት አላቸው፤ | E07 | | | | |
| 34. | የተቋሙ የመጀመሪያ ደረጃ አመራሮች የሥነምግባር ልህቀትና ሙስና የመከላከል አቅምና ብቃት አላቸው፤ | E08 | | | | |
| 35. | የተቋሙ ሰራተኞች የሥነምግባር ልህቀትና ሙስና የመከላከል አቅምና ብቃት አላቸው፤ | E09 | | | | |
| 36. | በተቋሙ አገልግሎት አማካይ የደንበኛና የባለድርሻ የእርካታ ዕድገት አሳይቷል ፤ | E10 | | | | |
| 37. | ፍርድ ቤቱ አገልግሎት የደንበኛና የባለድርሻ ቅሬታና አቤቱታ ማቅረቢያ | E11 | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ስርዓት ተዘርግቷ፤ | | | | | |
| 38. | ፍርድ ቤቱ የአመራሩና የሰራተኛዉ የብልሹ ተግባራት መገምገሚያ ስርዓት ዘርግቷል፤ | E12 | | | | |
| | **ክፍል አምስት ፡- በተቋሙ የሙስና እና ብልሹ ተግባራትን መረጃ የማመንጨት አቅመና** ብቃት **በሚከተሉት የጽሁፍ መጠይቆች እስማማለው፤ በመጠኑ እስማማለው፤ አልስማማም እና አላውቅም በሚል ይሙሉ፡፡** | | | | | |
| | 4 እስማማለሁ፣ 3 በመጠኑ እስማማለሁ፤ 2 አልስማማም፡ 1 አላውቅም | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 39. | የፍርድ ቤቱ የበላይ አመራር ጥቆማዎችን የ መቀበልና ውሳኔ የመስጠት ዝግጁነት፤ ተነሳሽነትና ተግባራዊ የማድረግ አቅም አለው፤ | F01 | | | | |
| 40. | ፍርድ ቤቱ የሙስናና ብልሹ ተግባራት ጥቆማዎችን በማደራጀት ለኮሚሽኑ የማቅረብአቅም፤ ብቃት አለው ፤ | F02 | | | | |
| 41. | ፍርድ ቤቱ የሙስናና ብልሹ ተግባራት ጥቆማዎችን እና ምክረ ሃሳቦችን ወስዶ ተግባራዊ አድርጓል | F03 | | | | |
| 42. | የፍርድ ቤቱ የተመዘበረ ሀብት በመረጃ ላይ በመመስረትና ክትትል በማድረግ ለማስመለስጥረት አድርጓል፤ | F04 | | | | |
| 43. | የፍርድ ቤቱ ጠቋሚዎች የሙስናና ብልሹ ተግባራት ጥቆማ እንዲያቀርቡ የመፍጠር የማበረታታትና የማነሳሳት ስራ ይሰራል፤ | F05 | | | | |
| 44. | ተቋሙ ተገልጋይ እና ባለድርሻ አካላት ጥቆማ እንዲያቀርቡ ግንዛቤ የመፍጠር ሰራ ሰርቷል፤ | F06 | | | | |
| 45. | የፍርድ ቤቱ ጠቋሚዎች የሥራና የሕይወት ዋስትና ከላለ/ጥበቃ እንዲሰጣቸው ክትትልናድጋፍ ያደርጋል፤ | F07 | | | | |
| 46. | የፍርድ ቤቱ ተጨባጭ ሁኔታ ሙስናና ብልሹ አሠራር ለመከላከል የሚያግዙ ልዩ ልዩአደረጃጀቶችን፡ክለቦችንና ንቅናቄዎችን እንዲፈጠሩ ያበረታታል፤ | F08 | | | | |
| 47. | ፍርድ ቤቱ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት አፈጻጸም ሪፖርት ለሕዝብ ተደራሽ አድርጓል | F09 | | | | |
| 48. | ፍርድ ቤቱ ከሙስና እና ብልሹ ተግባር የጸዳ ስለመሆኑ ጥቆማ የመቀበል የሕዝብና የባለድርሻ አካላት አስተያየት የመሰብሰብ ስርዓት አለው፤ | F10 | | | | |
| 49. | ፍርድ ቤቱ ሙስና እና ብልሹ ተግባር የመተንተንና ማሻሻያ እርምጃዎችን የመዉሰድ | F11 | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አሠራር ሥርዓት ዘርግቷል | | | | | |
| 50. | ሙስና እና ብልሹ ተግባራት መረጃ ጥቆማ አቅርቦትና የጠቋሚዎች የማበረታቻ አሠራርሥርዓትና ትግበራ አለው፤ | F12 | | | | |
| 51. | የሙስና ተግባራት መረጃና ማስረጃ፤ አቅርቦትና የፍትሀ ዉሳኔ አሠጣጥ ሰርዓት አለው፤ | F13 | | | | |
| 52. | በተቋሙ የሙስና መረጃ ጥቆማ በቴክኖሎጂ አማራጮች የማከናወን ስርአት ዘርግቷል | F14 | | | | |
| 53. | የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ አዋጅ አለማክበር የሚያስከትለዉ ቅጣት ግንዘቤ ደረጃ ጨምሯል | F15 | | | | |
| 54. | የሀብት ምዝገባና ማሳወቅ አዋጅ ለጠቋሚዎች የሚያስገኘዉ ጥቅም ግንዘቤ አድጓል | F16 | | | | |
| **ክፍል ስድስት፡ በዳኝነት ስርአት የሙስና ስጋት በሚከተሉት የጽሁፍ መጠይቆች እስማማለው፤ በመጠኑ እስማማለው፤ አልስማማም እና አላውቅም በሚል ይሙሉ፡፡** | | | | | | |
| | 4 እስማማለሁ፣ 3 በመጠኑ እስማማለሁ፤ 2 አልስማማም፡ 1 አላውቅም | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 55. | የዳኝነት ክርክሩ አግባብ ባለው የስነስርአት ህግ መሰረት ይካሄዳል፤ | G01 | | | | |
| 56. | ዋስትና ያላግባብ መከልከል ወይም መፍቀድ ይታያል፤ | G02 | | | | |
| 57. | ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ ማስረጃውን አግባብነት ባለው የስነ ስርአት ህግ ጋር በማገናዘብና፤በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፤ | G03 | | | | |
| 58. | ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ ማስረጃውን አግባብ ባልው መሰረታዊ ህግ ጋር በማገናዘብና፤ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፤ | G04 | | | | |
| 59. | ዳኞች ክርክርን በሚመሩበት ጊዜ፣ ፍርድና ዉሳኔ ሲሰጡ ከሃይማኖት፤ ከዘመድ አዝማድ እና ከአከባቢያዊነት የጸዳ ነው፤ | G05 | | | | |
| 60. | ዳኞች ከሙስናና ብልሹ አሰራር በጸዳ መልኩ ፍርድ ይሰጣሉ፤ | G06 | | | | |
| 61. | ዳኞች ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት የጸዳ ብይን፤ውሳኔ እና ፍርድ ይሰጣሉ ፤ | G07 | | | | |
| 62. | ያላግባብ ተከሳሽን ጥፋተኛ ማለት ወይም ነጻ መልቀቅ፤ ቅጣት መጨመር ወይም መቀነስ ይታያል፤ | G08 | | | | |
| 63. | የፍትሀ ተደራሽነት ለማረጋገጥ ፍርድ ቤቱ በቀላሉ ለተጠቃሚው ሊደርስበት የሚችል ስርአት ዘርግቷል፤ | G09 | | | | |
| 64. | የፍትሀ ተደራሽነቱ የተገልጋዩን ገንዘብ የመክፈል አቅም ባገናዘበ መልኩ ይተገበራል፤ | G10 | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 65. | በፍርድ ቤት የሚሰጠዉ ብይን፣ዉሳኔና ፍርድ ተገማችነት ይታይበታል ፤ | G11 | | | | |
| 66. | ዳኞች የዳኝነት ስራቸውን በግልጽ ችሎት ያከናውናሉ፤ | G12 | | | | |
| 67. | ዳኞች ለተገልጋዮች የሚሰጡት አገልግሎት ቅልጥፍና ይታይበታል፡፤ | G13 | | | | |
| 68. | ዳኞች ለተከራካሪ ወገኖች ጉዳዮችን እንዲያስረዱ ያለአድሎ በቂ ጊዜ ይሰጣሉ፤ የምስክር ቃልን ሳያቆራርጡ ይመዘግባሉ። | G14 | | | | |
| 69. | ዳኞች ለተከራካሪ ወገኖች ትክክለኛ ውሳኔ በህጉ መሰረት ያላድሎ ይሰጣሉ፤ከደላሎችና ጠበቆች ጋር አላግባብ የሆነ ግንኙነት አይፈጥሩም። | G15 | | | | |
| **ክፍል ሰባት፡ የፌደራል የፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም የሙስና ስጋት ተጋላጭነት በሚከተሉት የጽሁፍ መጠይቆች እስማማለው፤ በመጠኑ እስማማለው፤ አልስማማም እና አላውቅም በሚል ይሙሉ።** | | | | | | |
| | 4 እስማማለሁ፣ 3 በመጠኑ እስማማለሁ፤ 2 አልስማማም፡ 1 አላውቅም | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 70. | የፍርድ ባለዳውን ንብረት ለማገድና ለመሸጥ አላስፈላጊ የሆነ መዘግየት ይታያል፤ | H01 | | | | |
| 71. | የፍርድ ባለዳውን ንብረት ተሸጦ የተገኘውን ገንዝብ ለፍርድ ባለመብቱ ለመስጠት መዘግየት ይታያል፤ | H02 | | | | |
| 72. | የጨረታ ሂደት ባለሙያዎች እና በህግ ያልታወቁ ግለሰቦች (ደላሎች) የፍርድ ባለዳውን ንብረት በጨረታ ሲሸጡ የጥቅም ግንኙነት ሲፈጥሩ ይታያል፤ | H03 | | | | |
| **ክፍል ስምንት፡ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሙስና** ስጋት **በሚከተሉት የጽሁፍ መጠይቆች እስማማለው፤ በመጠኑ እስማማለው፤ አልስማማም እና አላውቅም በሚል ይሙሉ።** | | | | | | |
| | **4 እስማማለሁ፣ 3 በመጠኑ እስማማለሁ፤ 2 አልስማማም፡ 1 አላውቅም** | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 73. | ዳኞች ያለአድሎ፤በሀቀኝነትና የሙያ ነጻነታቸውን መሠረት በማድረግ ስራቸውን ማከናወናቸዉን ይከታተላል፤ | I01 | | | | |
| 74. | በዳኞች የድስፕሊን ጥሰት ምክንያት ለጉባኤዉ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በአፋጣኝ ይመልሳል፤ | I02 | | | | |
| 75. | ዳኞች በሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ሥልጣናቸዉን ከተገለገሉበት አፋጣኝ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ | I03 | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 76. | የዳኞች ሹመት በሙያ ብቃትና በላቀ አፈፃፀም ላይ የተመሠረተ መሆኑን በተገቢው ሁኔታ ያረጋግጣል ፤ | I04 | | | | |
| 77. | የዳኞች ደረጃ ዕድገት በሙያ ብቃትና አፈፃፀም ላይ የተመሠረተ መሆኑን ስርአት ዘርግቶ ያረጋግጣል፤ | I05 | | | | |
| | **ክፍል ዘጠኝ፡ የሬጂስትረር ዳይሬክቶሬት ሙስና ስጋትበሚከተሉት የጽሁፍ መጠይቆች እስማማለው፤ በመጠኑ እስማማለው፤ አልስማማም እና አላውቅም በሚል ይሙሉ፡፡** | | | | | |
| | **4 እስማማለሁ፣ 3 በመጠኑ እስማማለሁ፤ 2 አልስማማም፡ 1 አላውቅም** | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 78. | መዝገቦችን መደበቅ፤ማጥፋትና የመፈለጊያ ክፍያ መጠየቅ ይታያል | J01 | | | | |
| 79. | የሚቀርቡ መዝገቦች በቀጠሮ ቀን መረጃዉን በትክክል የተሟላ መሆኑን አረጋግጦ ያቀርባል፤ | J02 | | | | |
| 80. | ለፍርድ ቤት የቀረቡ የክስ ማመልከቻወችን በሥነስርዓት ሕጉ በተቀመጠዉ መስፈርት መሠረት የቀረቡ መሆኑን ያረጋግጣል፤ | J03 | | | | |
| 81. | የሥነስርዓት ሕጉን አሟልቶ ለፍርድ ቤት የቀረበ የክስ ማመልከቻወችን የሥነስርዓት ሕጉን አላሟላም በሚል ሰበብ ባለጉዳዮችን ክሱን አስተካክሉ በማለት አላግባብ ያጉላላል፤ | J04 | | | | |
| 82. | በቀጠሮ ላይ ያሉ መዝገቦች በግልጽ ማቀፍ በማስቀመጥ በቀላሉ በቀጠሮ ቀን በሚገኝበት ሁኔታ ያስቀምጣል፡፤ | J05 | | | | |
| **ክፍል አስር፡ በፍርድ ቤቱ ሰራተኞች የሚፈጸሙ የሙስና ደረጃ ስጋቶችን ለማሳየት በሚከተሉት የጽሁፍ መጠይቆች ከፍተኛ፤ መካከለኛ፤ ዝቅተኛ እና አላውቅም በሚል ይሙሉ፡፡** | | | | | | |
| | **4 ከፍተኛ፣ 3 መካከለኛ፤ 2 ዝቅተኛ፡ 1 አላውቅም** | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 83. | ስልጣኑንና ሀላፊነቱን ያላአግባብ በመገልገል ለራሱ ጥቅም የሚያገኝ ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም የሚያስገኝ ወይም ሌላ ሰዉን መጉዳት ፤ | K01 | | | | |
| 84. | ጉቦ መቀበል ድርጊት፤ | K02 | | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 85. | ሀላፊነቱን በመጠቀም የማይገባ ጥቅም መቀበል፤ | K03 | | | | | |
| 86. | የ ፍ/ ቤቱን ጥቅም በሚጎዳ መንገድ መስራት፤ | K04 | | | | | |
| 87. | በፍ/ ቤቱ እቃ ያለአግባብ መያዝ ፤ | K05 | | | | | |
| 88. | የማይገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በብርበራ ወይም በመያዝ ፤ በዉርስ ስርአት በሀራጅ ሽያጭ ፤በፍርዱ አፈጸም የተያዘዉን ንብረት ፤ ጥሬ ገንዘቦችን ፤እቃወችን ፤ ሰነዶችን መዉሰድ ወይም ማስወስድ፤ | K06 | | | | | |
| 89. | በስልጣኑ አላግባባብ መገለገል፤ | K07 | | | | | |
| 90. | ያለግባብ ጉዳይን ማጓትት፤ | K08 | | | | | |
| 91. | ዋጋ ያልዉን ነገር ያለከፍያ ከክፍያዉ በታች የሚቀበል፤ | K09 | | | | | |
| 92. | ምንጩ ያልታወቀ ገንዘብ ወይም ንብረት መሰብሰብ፤ | K10 | | | | | |
| 93. | የስራ ሚስጥርን መግለጽ፤ | K11 | | | | | |
| 94. | ለራሱ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም ለማስገኘት ወይም ሌላ ሰዉ ለመጉዳት በማሰብ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘገጀት ፤ ወደሀሰት መቀየር ወይም በሀሰተኛ ሰነዶች መገለገል፤ | K12 | | | | | |
| 95. | ለራሱ ጥቅም ለማገኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም ለማስገኘት ወይም ሌላ ሰዉ ለመጉዳት በማሰብ ሰነዶችን ማጥፋት ወይም መቅደድ፤ | K13 | | | | | |
| 96. | ከስልጣኑ ከታገደ ወይም ከተሻረ ፤ከስራዉ ከተዛወረ በኋላ በማስመሰል በሰራዉ መገለገል፤ | K14 | | | | | |
| 97. | ለራሱ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም ለማስገኘት በፍ/ቤቱ በአደራ | K15 | | | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተሰጠዉ ንብረት ወይም ጥሬ ገንዘብ የወሰደ ወይም ያስወሰድ፤ | | | | | | |
| 98. | ለራሱ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም ለማስገኘት ተበዳዩን በማታለል የተበዳዩንን ሰዉ ጥቅም መጉዳት፤ | K16 | | | | | |
| 99. | የሙስና ወንጀል ፈጽሞ ያገኘዉን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ፤ | K17 | | | | | |

**አባሪ ስድስት፡ ቃለ-መጠይቅ**

የቃለ መጠይቅ ቸክሊስት

<u>ክፍል I፡ መግቢያ</u>

እንደምን አደሩ/ዋሉ/አመሹ! እኔ ዶ/ር/አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት _____________________ እባላለሁ።

ይህ ቃለ-መጠይቅ በፌደራል የስነ ምግባር እና የጸረ ሙስና ኮሚሽን በፍርድ ቤቶች ላይ የሙስና ሥጋት ጥናት ለማደረግ ጠቃሚ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ይህ ጥናት በዋናነት የሚያተኩረው በፍርድ ቤቶች ላይ ዋና ዋና የስራ ሂደትና(የፌደራል ፍርድ ቤቶች፤ ሼሪአ ፍርድ ቤቶች፤ በደቡብና በኦሮሚያ ያሉ ጠቅላይ እና የከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና በተጨማሪም ለፍርድ ቤት ሬጂስትረር፤ ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤና ለፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ያጠቃልላል።) እና አጋዥ የስራ ክፍሎች ሲሆን የዚህ ጥናት ዓላማዎች፡- በፍርድ ቤቶች የሚስተዋሉ የሙስና ስጋት ዝርዝር መለየት፤ በፍርድ ቤቶች የሙስና አደጋ ምክንያቶችን መለየትና መተንተን፤የሙስና ስጋት መገምገምና ደረጃ መስጠት እና በፍርድ ቤቶች በተሰጠዉ የደረጃ ቅደም ተከተል መሰረት የሙስና መከላከል ምክረሀሳቦችን ማቅረብ ነው።

ይህ የሙስና ስጋት ጥናት የሚካሄደው ሙሰኞችን የሚፈልግ ሳይሆን የተቋሙን የሙስና ስጋት ለመቀነስ ታስቦ የሚሰራ፤ ውጤታማ የመከላከያ መሳሪያ መሆኑንና ተቋሙን በመልካም ታማኝነት፣ በመልካም ስምና የዜጎች እምነት እንዲጨምር ነው።

ስለሆነም መጠይቁን በቅንነት በመሙላት እንድትተባበሩ እና ጠቃሚ አስተያየት እንድትሰጡን እንጠይቃለን። የእናንተ ምላሽ የሙስና ተጋላጭነት ሥጋት ለመለየት እና ለማወቅ ትልቅ እገዛ ያደርጋል።

እባክዎ ጥቂት ደቂቃዎችን ወስደው ጥያቄዎችን መመለስ ይችላሉ? በዚህ መጠይቅ ውስጥ የእርስዎ ስም እና ማንነት የማይጠቀስ፣ የሚሰጡት ምላሽም ለታለመለት አላማ ብቻ የሚውል እና ሚስጥራዊነቱም የሚጠበቅ መሆኑን እየገለጽኩ ለሚያደርጉልኝ ትብብር ከወዲሁ አመሰግናለሁ።

ሀ. ቃለ መጠይቁን የሚሞላው ሰዉ ስም_____________________________ ቀን______________

ለ. ይሄን ቃለመጠይቅ ለማካሄድ ፈቃደኛ ስለሆኑ በኮሚሽኑ ስም አመሰግናሉ

ሐ. ለሥራ ክፍል ሀላፊ /ባለሙያ የቃለ መጠይቅ መርሃ ግብር

መ. መጠይቁ አላማ : በዚህ ፍ/ቤት ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን እና በሙስና ስጋት ላይ አስተያየቶችን ለመሰብሰብ ነው፤

ሰ. ቃለ መጠይቁ ጥቂት ደቂቃ ያህል ሊወስድ ይችላል ።

የፍ/ቤቱ ስያሜ ____________________________________________

የፍ/ቤቱ አድራሻ ____________________________________________

የስራ ክፍሉ ወይም ችሎት ስያሜ _____________________________

የስራ ክፍሉ ወይም ችሎት አድራሻ_________________________________

የመልስ ሰጭ  የስራ ሀላፊ ወይም ባለሙያ ስም(ፍቃደኛነቱን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ይሁን)

___________________________

<u>ክፍል II : ጥያቄዎች</u>

2. 1.የፍርድ ቤቱ የበላይ አመራር ጥቆማዎችን የ መቀበልና ውሳኔ የመስጠት ዝግጁነት፤ተነሳሽነትና ተግባራዊ የማድረግ አቅም ምን ይመስላል ? ሙሰናን ለመቅርፍ ምን ችገሮች ይታያሉ ? ፍርድ ቤቱ የአመራሩና የሰራተኛዉ የብልሹ ተግባራት መገምገሚያ ስርዓት አለ ወይ ? የሙስና ስጋት አለባቸዉ ተብሎ በተገመቱ የስራ ሂደቶች ላይ የቁጥር እና ክትትል ስራ ይደረጋል ?
3. ለዳኝነት አገልግሎት ስረአት የሚቀርብ ቃለ መጠይቅ

3.1 በዚህ ፍ/ቤት (ችሎቶት) የፍትህ ተደራሽነት እና የፍርድ ተገማችነት አሰራር ምን ይመስላል? የሚስተዋሉ ችግሮች ምንምን ናቸዉ?

- ምክንያቱ፤ ያስከተለውና ሊያመጣ የሚችለው ተጽእኖ ምንድን ነው?
- ያለውን ችግር ለመቅረፍ ምን አይነት እርምጃ መወሰድ አለበት ብለው ያምናሉ?

3.2 በዚህ ፍ/ቤት (ችሎት) ለተከራካሪ ወገኖች የአለመዘግይት ትክክለኛና ህጋዌ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት እንዴት ይገለጻል? የሚስተዋሉ ችግሮች ምንምን ናቸዉ?

- በእርሶ እምነት ምክንያቱ፤ ያስከተለውና ሊያመጣ የሚችለው ተጽእኖ ምንድን ነው?
- ያለውን ችግር ለመቅረፍ ምን አይነት እርምጃ መወሰድ አለበት ብለው ያምናሉ?

3.3 በዚህ ፍ/ቤት (ችሎት) ለተከራካሪ ወገኖች ያለአድሎ ትክክለኛና ህጋዊ ውሳኔ ይሰጣል ብለዉ ያምናሉ? በተለይም ፡-

- ዳኞች የምስክር ቃልን አለመመዝገብ ወይም መቆራረጥ እና ፍርድ ማዛባት
- በዋስ ሊፈታ የሚገባዉን ሰሰዉ አለመፍታት /የማይገባዉን ሰዉ ደግሞ መፍታት አለ ብለዉ ያምናሉ ?
- ጥፋተኛ ሊባል የማይገባዉን ሰዉ ጥፋተኛ ማለት/ /የሚገባዉን ሰዉ ደግሞ ጥፋተኛ አለማለት ይታያል?
- የጥፋተኛነት ዉሳኔ በተሰጣቸዉ ሰወች ላይ የቅጣት ዉሳኔ ያለአግባብ መጨመር መቀነስ ይታያል ? እና ሎች የሚስተዋሉ ችግሮች ምንድን ናቸዉ?
- በእርሶ እምነት ለችግሮች ምክንያት ፤ ያስከተለውና ሊያመጣ የሚችለው ተጽእኖ ምንድን ነው?
- ያለውን ችግር ለመቅረፍ ምን አይነት እርምጃ መወሰድ አለበት ብለው ያምናሉ?

3.4 በዚህ ፍ/ቤት (ችሎት) ፍርድ የሚያዘቡ የአድሎ አይነቶች ምን ምን ናቸዉ?

- በእርሶ እምነት ለችግሮች ምክንያት፤ ያስከተለውና ሊያመጣ የሚችለው ተጽእኖ ምንድን ነው?
- ያለውን ችግር ለመቅረፍ ምን አይነት እርምጃ መወሰድ አለበት ብለው ያምናሉ?

3.5 በዚህ ፍ/ቤት(ችሎት) ውስጥ በይበልጥ ለሙስና ተጋላጭነት የሚዳርገው አሰራርና የሙስናው አይነት ምንድን ነው?

- በእርሶ እምነት ለችግሮች ምክንያት፤ ያስከተለውና ሊያመጣ የሚችለው ተጽእኖ ምንድን ነው?
- ያለውን ችግር ለመቅረፍ ምን አይነት እርምጃ መወሰድ አለበት ብለው ያምናሉ?

3.6 በዚህ ፍ/ቤት(ችሎት) ውስጥ የዳኞች ነጻነት እና ተጠያቂነት መርህ በትክክል እየተተገበር ነዉ ይላሉ? መልስዎ የለም ከሆነ የዳኞች ነጻነት እና ተጠያቂነት አለመኖር ምክንያቱ፤ ያስከተለውና ሊያመጣ የሚችለው ተጽእኖ ምንድን ነው?

4. ለፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የሚቀርብ ቃለ መጠይቅ

4.1 በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት በኩል የሚስተዋሉ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች ምን ምን ናቸዉ?

- ምክንያቱ፤ ያስከተለውና ሊያመጣ የሚችለው ተጽእኖ ምንድን ነው?
- ያለውን ችግር ለመቅረፍ ምን አይነት እርምጃ መወሰድ አለበት ብለው ያምናሉ?

4.2 በፍርድ አፈጻጸም አገልግሎት በይበልጥ ለሙስና ተጋላጭነት የሚዳርገው አሰራርና የሙስናው አይነት ምንድን ነው?

- ምክንያቱ፤ ያስከተለውና ሊያመጣ የሚችለው ተጽእኖ ምንድን ነው?
- ያለውን ችግር ለመቅረፍ ምን አይነት እርምጃ መወሰድ አለበት ብለው ያምናሉ?

5. ለፍ/ቤት ሪጅስትራር የሚቀርብ ቃለ መጠይቅ

5.1 በዚህ ፍ/ቤት ሪጅስትራር በኩል የሚስተዋሉ የአገልግሎት አሰጣጥ ችገሮች ምን ምን ናቸዉ? በተለይም የጉዳዮችን ቀጠሮ ለባለጉዳዮች አለመግለጽ ፤ መዝገቦችን መጣል ፤ መደበቅ እና የመፈለጊያ ክፍያ መጠየቅ አለ ይላሉ?

- በእርሶ እምነት ለችግሮች ምክንያት፤ ያስከተለውና ሊያመጣ የሚችለው ተጽእኖ ምንድን ነው?
- በእርሶ እምነት ያለውን ችግር ለመቅረፍ ምን አይነት እርምጃ መወሰድ አለበት ብለው ያምናሉ?

5.2 በፍርድ ቤቶች ሬጅስትረር በይበልጥ ለሙስና ተጋላጭነት የሚዳርገው አሰራርና የሙስናው አይነት ምንድን ነው?

- ምክንያቱ፤ ያስከተለውና ሊያመጣ የሚችለው ተጽእኖ ምንድን ነው?
- ያለውን ችግር ለመቅረፍ ምን አይነት እርምጃ መወሰድ አለበት ብለው ያምናሉ?

6. ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሚቀርብ ቃለ መጠይቅ

6.1 የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ስለጣንና ሀላፊነቱን ሲወጣ የሚስተዋሉ አሉታዊ ተግባራት ምንድን ናቸዉ?

- ምክንያቱ፤ ያስከተለውና ሊያስከትል የሚችለው ተጽእኖ ምንድን ነው?
- ያለውን ችግር ለመቅረፍ ምን አይነት እርምጃ መወሰድ አለበት ብለው ያምናሉ?

6.2 በእርሶ እምነት በፍርድ ቤቶች የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በይበልጥ ለሙስና ተጋላጭነት የሚዳርገው አሰራርና የሙስናው አይነት ምንድን ነው?

- በእርሶ እምነት ለችግሮች ምክንያት፤ ያስከተለውና ሊያስከትል የሚችለው ተጽእኖ ምንድን ነው?
- ያለውን ችግር ለመቅረፍ ምን አይነት እርምጃ መወሰድ አለበት ብለው ያምናሉ?

7. ለሰው ሃብት አስተዳደር፤ በግዥና ፋይናንስ አስተዳደር እና የዉስጥ ኦዲት የሚቀርብ ቃለ መጠይቅ

7.1 በሰው ሃብት አስተዳደር በይበልጥ ለሙስና ተጋላጭነት የሚዳርገው አሰራርና የሙስናው አይነት ምንድን ነው?

- ምክንያቱ፤ ያስከተለውና ሊያስከትል የሚችለው ተጽእኖ ምንድን ነው?
- ያለውን ችግር ለመቅረፍ ምን አይነት እርምጃ መወሰድ አለበት ብለው ያምናሉ?

7.2 በግዥና ፋይናንስአስተዳደር በይበልጥ ለሙስና ተጋላጭነት የሚዳርገው አሰራርና የሙስናው አይነት ምንድን ነው?

- ለችግሮች ምክንያት፤ ያስከተለውና ሊያሳድር የሚችለው ተጽእኖ ምንድን ነው?
- ያለውን ችግር ለመቅረፍ ምን አይነት እርምጃ መወሰድ አለበት ብለው ያምናሉ

8. በአለፉት አመታት በፍ/ቱ የዉስጥ ኦዲት ምንይመስላል ? ዋነኛ ግኝት ምን ነበሩ ?
9. የጨረታ ስርአቱ በይበልጥ ለሙስና ተጋላጭነት የሚዳርገው የአፈጻጸም ችግሮች ምንድን ነው?

ለችግሮች ምክንያት፤ ያስከተለውና ሊያሳድር የሚችለው ተጽእኖ ምንድን ነው?

ያለውን ችግር ለመቅረፍ ምን አይነት እርምጃ መወሰድ አለበት ብለው ያምናሉ

መዝጊያ

ለዚህ ቃለ መጠይቅ ዉድ ጊዜዎን ወስደዉ በቂ ስለሰጡን በኮሚሽኑ ሰም ከልብ አመሰግናለሁ ።

የመጠይቁ አቅራቢ ስም__________________ ፊርማ_____________

## ማጣቀሻ ጽሁፎች

African Union (AU) (2003). African Union Convention on Prevention and Combatting Corruption. Adopted at the Second Ordinary Session of the Assembly of the Union.

Federal Ethics and Anti-Corruption Commission (FEACC). 2012.*Ethiopia- Second Corruption Perception Survey*. Final Report by Kilimanjaro International Corporation.

Gedion Gemora. 2019. *National Study on Prevention of Corrupt Practices in the Mining Sector*. Addis Ababa, Ethiopia: Bencia Printing Press.

Institute of African Economic Studies (IAES). 2008 "Transparency Ethiopia Corruption Diagnostic Baseline Survey." Final report. Transparency Ethiopia, Addis Ababa.

Transparency International (TI) (2022). Corruption Perception Index 2021. Transparency International.

_____________________(2007). *Global Corruption Report 2007: Corruption in Judicial Systems*. Cambridge: Cambridge University Press.

United Nations Office on Drugs and Crime (2020). State of Integrity: A Guide on Conducting Corruption Risk Assessments in Public Organizations.

United Nations. (2003). United Nations Convention Against Corruption. Adopted at the UN General Assembly. Resolution 5814, 31 October 2003.

World Bank (2014). World Bank Global Integrity Report. The World Bank: Washington D.C.

________________.(2012). *Diagnosing Corruption in Ethiopia: Perceptions, Realities, and the Way Forward for Key Sectors.* Washington D.C.: The World Bank.

የኢትዮጵያ እንባ ጠባቂ (Ethiopian Ombudsman Authority, 2021). የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በዋናው መስሪያ ቤትና በቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ውስጥ የአሰራር ሥርአት ጥናት ለማድረግ የተደረገ የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት። ህዳር 2014.

የኢትዮጵያ ፌደራል ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኅገመንግስት (1995) አዋጅ ቁጥር 1/1995 *የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ.*

የኢትዮጵያ ፌደራል ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (2013). የፌዴራል የስነ-ምግባርና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 1236/2013. *የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ.*

የኢትዮጵያ ፌደራል ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (1993). የፌዴራል የስነ-ምግባርና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 235/1993. *የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ.*

የኢትዮጵያ ፌደራል ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (2007). የተሻሻለው የጸረ-ሙስና ልዩ-የስነ ስርአትና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 882/2007. *የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ.*

የኢትዮጵያ ፌደራል ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (2007). የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007. *የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ.*

የፌደራል የፍ/ ቤት የዳኛች ስነምግባር ድንብ

የተሻሻለዉ የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች አዋጅ 43 / 1994 ደቡበ ነጋሪት ጋዜጣ

የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 42/1994 ደቡበ ነጋሪት ጋዜጣ

የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አሰራር ለማጠናከር የወጣ መመሪያ ቁጥር 2006 አ.ም

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ ቤት የስራ ክፍል ሀላፊወችና የሰራተኞች ስነምግባር መተዳደሪያ ድንብ 2013 አ.ም

የኦሮሚ ክልላዌ መንግሰት ፍርድ ቤቶች የዳኛች ስነምግባር ድንብ ቁጥር 2011አ.ም

አንደገና የሻሻለዉ የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች ዳኞችና በጉባኤ የሚተተዳደሩ ባለሙያወች የተፈላጊ ችሎታ የምልመላና መረጣ ኮሚቴ ማቋቋሚያ ፤የአሰራር ስርአትና የስራ መዘርዘር መመሪየ ቁጥር10/2011 አ.ም.

የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች የዳኛች የስነምግባርና ዲሲሊን ድንብ ቁጥር 6/1995

የደቡብ ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤት ሙስና መከላከል ስትራቴጂ ሰነድ 2011 አ.ም.